# ሕብረተሰብ ትምህርት

## የሰባተኛ ክፍል የተማሪዎች መጽሐፍ


**አዘጋጆች :**

ጀማል ሙስጠፋ (M.Ed.)
ነጋሽ ሄቦ (M.A.)
ነጌሶ እስሞ (M.Sc.)

**አርታኢዎች:**

በላቸዉ አበራ (M.A)
ግርማ ፀጋየ (M.Ed.)

**ገምጋሚዎች:**

በቀለ ቀነአ
አበራ ከበበዉ
ፍቃዱ ከበደ
ቤኪ ቶለሣ

**ተርጓሚዎች:**

በቀለ ቀነአ
ቤኪ ቶለሣ
አበራ ከበበዉ
ከተማ ፀጋ
ዘዉዴ ረጋሣ

**ግራፊክስ:**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

ማዉጫ ገፅ

**ምዕራፍ 1 ........................................................................................ 1**

**የመሬት አፈጣጠር ....................................................................................... 1**

*1.1 የስርዓተ ፀሀይና የመሬት አፈጣጠር ............................................................. 2*

*1.2 የላይኛው የመሬት አካል ይዘቶችና ውስጣዊው የመሬት መዋቅሮች ......... 10*

*1.3. ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ነገሮች ............................................... 16*

*1.4. የአለቶች ሥርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ..................................... 20*

*ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ............................................................................. 20*

**ምዕራፍ 2 ........................................................................................ 26**

**ዝግመታዊ የሰው ልጅ ለውጥና የዓለም ህዝብ ........................................... 26**

*2.1 የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ ............................................................ 28*

*2.2 የዓለም ህዝብ ................................................................................. 31*

*2.3 የመንንዣ ዕድገት ፅንሰ ሀሳብ ............................................................. 49*

**ምዕራፍ 3 ........................................................................................ 61**

**ሰውና የተፈጥሮ ሀብት ................................................................... 61**

*3.1 በሰዉና ተፈጥሮ አከባቢ መካከል ያለው ግንኙነት ............................. 62*

*3.2 የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች ................................................................. 64*

**ምዕራፍ 4 ........................................................................................ 69**

**ቀደምት የአለም ስልጣኔ ከጥንት እስከ መካከለኛው ክፍለ ዘመን .......... 69**

*4.1.ጥንታዊ የአለም ስልጣኔ ..................................................................... 70*

*4.2. የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአለም ታሪክ ........................................... 86*

**ምዕራፍ 5 ........................................................................................ 97**

**ጥንታዊ የአፍሪካ ታሪክ .................................................................... 97**

*5.1 ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ ...................................................................... 98*

*5.2 ጥንታዊ የኑቢያ ስልጣኔ .................................................................... 103*

*5.3 ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ ......... 106*

**ምዕራፍ 6 ......... 112**

**ጥንታዊና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና ህዝቦች ታሪክ. 112**

*6.1. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ......... 113*

*6.2 የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች ......... 123*

*6.3 የህዝቦች ግንኙነት፣ትስስር እና እንቅስቃሴ ......... 126*

*6.4. የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች ......... 134*

*(ግብርና፣ ንግድ እና ግብር) ......... 134*

**ምዕራፍ 7 ......... 140**

**ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ የዓለም ጉዳዮች ......... 140**

*7.1. የምንኖርበት አከባቢ ......... 141*

*7.2. የህዝብ ቁጥር መጨመር ......... 148*

*7.3. ሽብርተኝነት ......... 149*

*7.4. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ......... 150*

# ምዕራፍ 1

# የመሬት አፈጣጠር

**ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች:**

- የመሬትና የስርዓተ ፀሀይን አፈጣጠር ትገልጻለህ/ሽ
- አራቱ የመሬት ይዘቶችና ግንኙነታቸውን ትገልጻለህ/ሽ
- የመሬት ንብርብሮችና ባህሪያቸውን ትገልጻለህ/ሽ
- ስለመሬት ውስጣዊ ሁኔታ የሚያስረዱ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ የመረጃ ምንጮችን ትለያለህ/ሽ
- ቅርፊተ መሬት የተሰራባቸውን ንጥረ ነገሮች፣ ማዕድናትና አለቶችን ትለያለህ/ሽ
- በኢትዮጵያ የአለቶች ስርጭትና በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ሽ

**መግቢያ**

በ5ኛና በ6ኛ ክፍሎች የአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ስለ ኦሮሚያና ኢትዮጵያ ህዝቦች አሰፋፈርና መገኛ በስፋት ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውስጥ ደግሞ ስለ ሥርዓተ ፀሀይ አፈጣጠር፣ የመሬት አፈጣጠር፣ የሥርዓተ ፀሀይ ክፈሎች፣ ፕላኔቶች፣ ላይኛውና ውስጣዊ የመሬት ክፍል አወቃቀር፣ የአለቶች ስርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያላቸውን ጠቀሜታ ትማራለህ/ሽ፡፡

ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃቶች

- የመሬት አፈጣጠር ሁኔታና ሥርዓተ ፀሀይን ትለያለህ/ሽ
- በላይኛው የመሬት ክፍል የሚገኙትን ሊቶስፌር፣ ባዮስፌር፣ ሀይድሮስፌርና አትሞስፌር ትለያለህ/ሽ
- የተለያዩ የመሬት ንብርብሮች የተሰሩባቸውን ንጥረ ነገሮችን ትለያለህ/ሽ
- ከውጫዊ የመሬት ክፍል ወደ እምብርተ መሬት ሲኬድ ያለው የሙቀት፣ ግፊት፣ ክብደትና ንጥረ ነገሮች ልዩነት ትገመግማለህ/ሽ
- የላይኛው የመሬት ክፍል የተሰራባቸዉን ዋና ዋና ማዕድናት፣ ንጥረ ነገሮችና አለቶች ትለያለህ/ሽ
- በኢትዮጲያ የአለቶች ስርጭትና ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸዉን ጠቀሜታ ትገልፃለህ/ሽ።


## 1.1 የስርዓተ ፀሀይና የመሬት አፈጣጠር

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. ስለ ስርዓተ ፀሀይ ምን ታውቃለህ/ሽ?
2. በስርዓተ ፀሀይ ውስጥ የሚገኙትን አካላት ግለፅ/ጪ።
3. በስርዓተ ፀሀይ ዉስጥ የሚገኙትን ፕላኔቶች ዘርዝር/ሪ።

እንደ ዘመናዊው ሳይንስ መነሻ ሀሳብ ስርዓተ ፀሀይ የተፈጠረዉ በጋዞች፣ በደመናና በተለያዩ ብናኝ አቧራ ሑደት አማካይነት መሆኑ ይገለፃል። በዚህ ሑደት ዉስጥ ውጫዊው አካል ቀስ በቀስ ወደ ፕላኔቶች ሲቀየር ዉስጣዊዉ በጣም የተጠጋጋውና ሞቃታማው አካል ደግሞ ወደ ፀሀይ ተቀይሯል ተብሎ ይታመናል። ፀሀይ በስርዓተ ፀሀይ እምብርት ዉስጥ ትገኛለች። የስርዓተ ፀሀይ እድሜ 4.6 ቢሊዮን አመታት ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

በስርዓተ ፀሀይ ዉስጥ ዘጠኝ ፕላኔቶች በራሳቸዉ መህዋር ላይ ፀሀይን ይዞራሉ፡፡ ፕላኔቶች ከፀሀይ ባላቸዉ ርቀት አማካይነት ከቅርብ ወደ ሩቅ ስንዘረዝራቸው፤ ሜርኩሪ፣ ቬኑስ፣ መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር፣ ሳተርን፣ ዩራኑስ፣ ኔፕቱንና ፕሉቶ ናቸው፡፡ ሌሎች በስርዓተ ፀሀይ ዉስጥ የሚገኙ ነገሮች ደግሞ ሳትላይቶች፣ አስትሮይዶች፣ ኮሜቶች፤ ሜትዮሮችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ሳትላይቶች በስርዓተ ፀሀይ ዉስጥ ፕላኔቶችን የሚዞሩ ሲሆኑ ኮሜቶች፣ አስትሮይዶችና ሜትዮሮች ፀሀይ የሚዞሩ አካላት ናቸው፡፡




ስዕል 1.1 ሥርዓተ - ፀሐይ

**ፀሀይ**

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ፀሀይ ምንድናት? እንዴትስ ተፈጠረች?
2. በፀሀይና መሬት መካከል ያለዉ ርቀት በኪሎሜትር ስንት ይሆናል?
3. ከዉስጣዊውና ውጫዊው የፀሀይ አካል ይበልጥ የሚሞቀዉ የትኛዉ ነዉ?

በስርዓተ ፀሀይ ዉስጥ ካሉት አካላት ፀሀይ በጣም ጠቃሚ ናት፡፡ ምክንያቱም ፀሀይ ሙቀትና ብርሃን የሚትሰጥ በመሆኑዋ ነው፡፡ ፀሀይ ባትኖር ኑሮ ህይወት ያላቸው ነገሮች በሙሉ መሬት ላይ መኖር አይችሉም ነበር፡፡ ከስርዓተ ፀሀይ ውስጥ ፀሓይ በጣም ግዙፍ ናት፡፡ ይህም 99.86 % ትሆናለች፡፡ ፀሀይ ካሉት ከዋክብቶች ሁሉ ለመሬት በጣም ቀርባ የምትገኝ ስትሆን ከመሬት 150,000,000 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች፡፡ ከፀሀይ ቀጥሎ ለመሬት ቀርባ የምትገኘው ከዋክብት አልፋሴንቸሪ ትባላለች፡፡ የፀሀይ ጨረር መሬት ለመድረስ 8 ደቂቃ ያህል ይወስድበታል፡፡

ፀሀይ በውጫዊ አካሏ 6,000°c ያህል ሙቀት የምታመነጭ ስትሆን በዉስጣዊው አካሏ ደግሞ 13,000°c ያህል ታመነጫለች፡፡ ከፀሓይ ውጪ ሌሎች ከዋክብቶች ሌሊት ሌሊት የሚታዩ ሲሆን ቀን ቀን ደግሞ አይታዩም፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች ክዋክብቶች የበለጠ ፀሓይ ለመሬት ስለምትቀርብ ለመሬት የምታመነጨው /የምትሰጠው/ ጨረር ከሌሎች የበለጠ ነው፡፡

## ፕላኔቶች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ፕላኔት ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. ፕላኔቶች ከከዋክብቶች በምን ይለያሉ?
3. ህይወት ያላቸው ነገሮች የሚኖሩት በየኛው ፕላኔት ላይ ነው? ለምን?
4. ፕላኔቶች ሚዛናቸን ጠብቀው በቅደም ተከተል ፀሀይን እንዲዞሩ የሚረዳቸው ምንድነው?

ፕላኔቶች በስርዓተ ፀሓይ ውስጥ ፀሀይን የሚዞሩ ናቸው፡፡ ሁሉም ፕላኔቶች ከፀሀይ በተለያየ ርቀት ላይ የሚገኙ ሲሆን የራሳቸው ምህዋር አላቸው፡፡ ምህዋር ማለት ክብ የእንቁላል ቅርፅ ያለው ፕላኔቶች ፀሀይን የሚዞሩበት የሃሳብ መስመር ወይም መንገድ ነው፡፡ በተጨማሪም ምህዋሮች የማይነካኩ ወይም የማይገናኙ ናቸው፡፡ ፀሀይ የራስዋ የስበት ሀይል ስላላት ፕላኔቶችን ወደራሷ ትስባለች፡፡ ይህ የወደ ውስጥ ስበት/centripetal force/ ይባላል፡፡ በተቃራኒው ፕላኔቶችን እርስ በእርስ ወደ ውጭ የመሳሳብ ሀይል አላቸው፡፡ ይህ ሀይል የወደ ውጪ ሀይል /centrifugal force/ ይባላል፡፡ እነኚህ ሁለቱ የተቃራኒ አቅጣጫ ሀይሎች እርስ በራሳቸው ተመጣጣኝ ስለሆኑ ፕላኔቶች ምህዋራቸውን ሳይለቁ ፀሀይን እንዲዞሩ ይረዳቸዋል፡፡ ፕላኔቶች የራሳቸው የሆነ ብርሃን የላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ከፀሓይ የሚያገኙትን ብርሃን ማንፀባረቅ ይችላሉ፡፡

ከፕላኔቶች ውስጥ ከአጥብያ ኮከብ(ቬነስ) በስተቀር ሌሎቹን በዓይን ብቻ ማየት አይቻልም፡፡ ፕላኔቶችን ከከዋክብቶች ለይቶ ለማየት የምንጠቀምበት መሳሪያ ቴሌስኮፕ ይባላል፡፡ ከሜርኩሪና ከአጥብያ ኮከብ(ቬነስ) በስተቀር ሌሎች ፕላኔቶች የራሳቸው ጨረቃ አላቸው፡፡ ሳተርን ብዙ ጨረቃዎች ያላት ፕላኔት ስትሆን እኛ የምንኖርባት መሬት አንድ ጨረቃ ብቻ አላት፡፡

**ሠንጠረዥ 1.1. የፕላኔቶች መረጃ**

| መስፈርቶች | | ፕላኔቶች | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሜርኩሪ | ቬነስ | መሬት | ማርስ | ጁፒተር | ሳተርን | ኡራኑስ | ኔፕቱን | ፕሉቶ |
| ከፀሃይ ያላቸው ርቀት ኪ..ሜ($10^6$) | | 57.9 | 108.2 | 150 | 227.9 | 778.3 | 1,427 | 2,869 | 4,496 | 5,900 |
| በምህዋር ላይ | ቀን | 88 | 224 | | | | | | | |
| | ዓመት | | | 1 | 1.9 | 11 | 29.5 | 84 | 164.8 | 247.7 |
| በዘቢያ ላይ | ቀን | 59 | 243 | | | | | | | 6 |
| | ሰዓት | | | 23 | 24 | 9 | 10 | 11 | 16 | |
| | ደቂቃ | | | 56 | 37 | 50 | 14 | | | |
| ዲያሜትር(የምድር ወገብ) በኪ..ሜ | | 4,878 | 12,104 | 12,756 | 6,787 | 142,800 | 120,000 | 51,800 | 49,500 | 3,000 |
| የጨረቃ ብዛት | | 0 | 0 | 1 | 2 | 16 | 20 | 15 | 2 | 1 |
| ከባቢ አየር | | He | $CO_2$ | $N_2$,$O_2$ | $CO_2$ | He,$H_2$ | He,$H_2$ | He,H2, CH4 | He,H2, CH4 | - |
| ከፍተኛው ሙቀት በ °C | | 430 | 480 | 60 | 30 | -140 | -17 | -220 | -215 | -220 |

**የመሬት አፈጣጠር**

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የመሬት አፈጣጠር ከሥርዓተ ፀሐይ አፈጣጠር ጋር ይመሳሰላል? እንዴት?
2. የመሬት ቅርፅ ምን ይመስላል? የሚታወቅበት መረጃዎች ምንድናቸው?
3. የመሬት እንቅስቃሴዎች ስንት ናቸው? ምን ምን ናቸው?

የመሬት አፈጣጠር ከሥርዓተ ፀሐይ አፈጣጠር ጋር ተመሳሳይነት አለዉ፡፡ የመሬት ዕድሜ ከሥርዓተ ፀሐይ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መሬት ፀሐይን ከሚዞሩ ፕላነቶች ዉስጥ አንዷ ናት፡፡ በድሮ ጊዜ ሰዎች መሬት ጠፍጣፋ እንደሆነች ያስቡ ነበር፡፡




ሥዕል 1.2 መሬት

ከጊዜ በኂላ ግን የተደረጉት ጥናትና ምርምሮች መሬት ክብ ወይም እንቁላል መሰል ሞላላ ቅርፅ ያላት መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ ይህን የመሬት ቅርፅ ካረጋገጡት ምሁራን ውስጥ ፓይታጎረስ፣ ፕላቶና አርስቶትል ዋናቹ ናቸው፡፡ የመሬት ቅርፅ ክብ መሆኗን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች፤

- የፀሓይ መውጣትና መጥለቅ


- የመሬት ጥላ በጨረቃ ገፅታ ላይ መታየት፤
- ከሰማይ የተነሳ የመሬት ፎቶ፤
- አንድ ሰው ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ኋላ ሳይመለስ ከጊዜ በኋላ የተነሳበት ቦታ መመለስ፤
- ሁለት መርከቦች ተከታትለዉ ሲጓዙ እየተራራቁ ሲሄዱ እርስ በራሳቸው አለመተያየት፡፡

አብዛኞቹ ፕላኔቶች በምኅዋራቸው ላይ ፀሐይን ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይዞራሉ፡፡ መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ አንድ ጊዜ ዞራ ለመጨረስ 23 ሰዓት ከ56 ደቂቃ /አንድ ቀን/ ይፈጅበታል፡፡ መሬት በራሷ ዛቢያ የምታደርገው እንቅስቃሴ የመሬት መሽከርከር ይባላል፡፡ መሬት በራሷ ዛቢያ ላይ በሚታደርገው እንቅስቃሴ ቀንና ሌሊት ይፈጠራል፡፡ መሬት  አንድ ጊዜ በምኅዋሯ ላይ  ፀሐይን ዞራ ለመጨረስ 365¼  ቀናቶች ይወስድባታል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የመሬት በፀሐይ ዙሪያ መዞር ይባላል፡፡  መሬት በፀሐይ ዙሪያ በምታደርገው እንቅስቃሴ የወቅቶች መፈራረቅ እንዲሁም የቀንና የሌሊት ሪዝማኔ ልዩነት ይፈጠራል፡፡




ሥዕል 1.3 የመሬት እንቅስቃሴዎች

የመሬት መጠነ ዙሪያ 40000 ኪሎ ሜትር መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ትልቁ የሃሳብ መስመር መሬትን ሰንጥቆ የሰሜንና የደቡብ ዋልታዎችን የሚያገናኝ ትልቁ ሜሪዲያን የሚባል ሲሆን መሬትን ወደ ምስራቅና ምዕራብ ንፍቀ ክበብ ይከፍላል፡፡ የዚህ ሃሳብ መስመር ርዝመት 12640 ኪ.ሜ. ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ መሬትን እኩል የሚከፍል የሃሳብ መስመር የምድር ወገብ ይባላል፡፡ ይህ የሃሳብ መስመር መሬትን ወደ ሰሜንና ደቡብ ንፍቀ ክበብ ይከፍላል፡፡ የዚህ ሃሳብ መስመር ርዝመት 12756 ኪ.ሜ. ይሆናል፡፡ የትልቁ ሜሪዲያንና የምድር ወገብ ርዝመት እኩል አለመሆናቸው መሬት ትክክለኛ ክብ አለመሆኑዋን ያረጋግጣል፡፡




**ሥዕል 1.4 የምድር ወገብና ትልቁ ሜሪዲያን የሃሳብ መስመሮች**

## የተግባር ጥያቄዎች

1. የሥርዓተ ፀሐይን ሥዕል በማዘጋጀት የፕላኔቶችን ስም ፃፍ/ፊ፡፡ በተጨማሪም ስለፕላኔቶቹ የምታውቀውን/ቂውን ፃፍ/ፊ፡፡
2. በወረቀት ላይ የመሬትን ቅርፅና የትልቁ ሜሪዲያን እንዲሁም የምድር ወገብ የሃሳብ መስመሮችን በማንሳት ያላቸውን የርዝመት

ልዩነት ለክፍል ተማሪዎችህ/ሽ አብራራ/ሪ፡፡

**መልመጃ 1.1**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. የሥርዓተ ፀሐይን አፈጣጠር አብራራ/ሪ፡፡ ለምን ሥርዐተ ፀሐይ ተባለ?
2. ከፀሐይ ባላቸው ርቀት መሰረት ዘጠኙን ኘላኔቶች በቅደም ተከተላቸው ከሩቅ ወደ ቅርብ ዘርዝር/ሪ፡፡
3. ስለ ኘላኔታችን በአጭሩ አብራራ/ሪ፡፡
4. መሬት ክብ መሆኗን ከሚያረጋግጡ መረጃዎች ውስጥ ሶስቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
5. መሬት ፀሐይን አንድ ጊዜ ዞራ ለመጨረስ የሚወስድባት ጊዜ ምን ያህል ይሆናል? በዚህ ምክንያት የሚፈጠሩ ክስተቶች ምን ምን ናቸው?

## 1.2 የላይኛው የመሬት አካል ይዘቶችና ውስጣዊው የመሬት መዋቅሮች


### 1.2.1. የላይኛው የመሬት አካል ይዘቶች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. በላይኛው የመሬት አካል ላይ የሚገኙ ነገሮችን ምን ምን ናቸው? ዘርዝር/ሪ፡፡
2. ለሚከተሉት ቃላቶች ፍቺ ስጥ/ጪ
   ከባቢ አየር፣ ሊቶስፌር፤ ባዮስፌርና ሃይድሮስፌር
3. በአብዘኛዉ ከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ጋሶችን ዘርዝር/ሪ፡፡

ውጫዊው የመሬት ክፍል በአራት ዋና ዋና አካላት ይመደባል፡፡

እነዚህንም አካላት ቀጥሎ ከተሰጠው ዲያግራም ተመልከት/ቺ፡፡




ሥ ዕል 1.5 የላይ ኛው የመ ሬ ት አካል ይዘቶች

ሀ. ሊ ቶ ስፌ ር

ይህ የላይኛው ደረቁ የመሬት ክፍል ሲሆን አህጉራትንና በባህር እንዲሁም በውቅያኖስ ሥር የሚገኙ አለቶችን ያጠቃልላል፡፡

ለ. ሃድ ሮ ስፌ ር

ሃይድሮስፌር ዉሃማ የመሬት አካል ሲሆን በመሬት ገፅ ላይ የሚገኙ እንደ ባህሮች ውቅያኖሶች ሐይቆችና ወንዞች ናቸው፡፡


## ሐ. ከባቢ አየር

ከባቢ አየር የብዙ አይነት ጋዞች ፣ አቧራና የውሃ ትነት ጥርቅም ሆኖ

መሬትን እንደ ብርድልብስ ሸፍኖ የሚገኝ ነው፡፡ በብዛት ከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ጋዞች ናይትሮጅን፤ ኦክስጅን፤አርጎንና ካርቦንዳይ ኦክሳይድ ናቸው፡፡

መ. ባዮስፌር

በላይኛው የመሬት አካል ላይ ያሉት ህይወት ያላቸው አካላት ሁሉ አንድ ላይ ባዮስፌር ይባላሉ፡፡ ባዮስፌር በአይን የማይታዩ ከጥቃቅን ነፍሳቶች ጀምሮ እስከ ትላልቅ እንስሳትና ዕፅዋትን ያጠቃልላል፡፡ እነሱም የሚገኙት በአየር፤ በውሃና በየብስ ውስጥ ነው፡፡




**ሥዕል 1.6 የላይኛው የመሬት አካል ይዘቶች**

## 1.2.2. የመሬት መረጃና ውስጣዊ መዋቅሮች

### 1.2.2.1 የመ ሬ ት ው ስጣ ዊ አካል መ ረጃ ም ንጮ ች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

የመሬት ውስጣዊ አካል መረጃ ምንጮች ምንድናቸው?

የመሬት ውስጣዊ አካል መረጃ ምንጮች በስንት ይከፈላሉ?

ስለ ውስጣዊው የመሬት አካል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሸሻለ ስለ መጣ በአሁኑ ጊዜ ስለ ውስጣዊው የመሬት አካል ማወቅ ተችሏል፡፡ ስለ ውስጣዊው የመሬት አካል ለማወቅ የሚጠቅሙን የመረጃ ምንጮች በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ቀጥተኛ ዘዴዎች፤ ቀጥተኛ ዘዴዎች የሚባሉት እንደ እሳተ ገሞራ ፍንዳታ፤ ማዕድናትን ለማውጣት ወደ መሬት ውሰጥ መቆፈርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለ. ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች፤ ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎች የሚባሉት ደግሞ አፈጣጠራቸው ከመሬት ጋር ግንኙነት ያላቸውን አካላት እንደ ጨረቃ፤ ማርስና ሌሎች ላይ ጥናት በማድረግ ስለ መሬት መረጃ ማግኘትን ያጠቃልላል፡፡ መሬትን በመቆፈር ስለ ውስጣዊው የመሬት ክፍል የሚያጠነው ሳይንስ ጅኦሎጂ ይባላል፡፡

### 1.2.2.2 ዉስጣዊው የመሬት ንብርብሮች

የግምገማ ጥያቄዎች

1. ዉስጣዊው የመሬት ንብርብሮች ማለት ምን ማለት ነው?
2. ዉስጣዊው የመሬት ንብርብሮችን ዘርዝር/ሪ

ዉስጣዊው የመሬት ንብርብሮች ማለት ካላይኛው የመሬት አካል አስከ ውስጣዊው የመሬት አካል ያለው ክፍፍል ማለት ነው፡፡ ውስጣዊውን የመሬት አካል በተለያዩ መመዘኛዎች መክፈል ይቻላል፡፡ ከእነዚህ መመዘኛዎች መካከል ውስጣዊው የመሬት አካል ባለው ይዘት፤ ጠጣርነት ወይም ፈሳሽነት ባህርይ አማካይነት በሶስት ይከፈላል፡፡ እነሱም፤


1. ቅርፊተ መሬት: ቅርፊተ መሬት የላይኛው የመሬት አካል ነው። የቅርፊተ መሬት ጥልቀት ከቦታ ቦታ ልዩነት አለው። ቅርፊተ መሬት ከ30- 40 ኪ.ሜ. ጥልቀት አለው።

ከፍተኛ ተራረዎች አካባቢ 40 ኪ.ሜ. ያለው ሲሆን በሰው ልጅ ዘንድ በጥሩ ሁኔታ የሚታወቅ ነው። ይህ የመሬት አካል የሰው ልጅም መኖሪያ ቦታ ነው።

እንድሁም በመሬት ውስጥና በላይኛው የመሬት ኃይሎች የሚቀያየር ንብርብር ነው። ቅርፊተ መሬት በሁለት ይከፈላል። እነሱም፤

ሀ. የየብስ ቅርፊተ መሬት፤ ይህ የመሬት ንብርብር ሲያል(sial) ሲልከንና አሉሚኒየም የተፈጠረ ሲሆን ክብደት የሌላቸው ወይም ቀላል ማዕድናት ናቸው።

ለ. የባህር ሥር ቅርፊተ መሬት፤ ይህ ንብርብር የተፈጠረው ሲማ/Sima (ሲሊከንና ማግኒዚየም) ከሚባሉት ማዕድናት ነው።





ሥዕል 1.7 ቅርፊተ መሬት

2. **ማዕከለ መሬት**፤ ይህ የመሬት ንብርብር በቅርፊተ መሬትና በእምብርተ መሬት መካከል ይገኛል። እንደ ጂኦሎጂስቶች ገለፃ የዚህ የመሬት ንብርብር ጥልቀት እስከ 2900 ኪ.ሜ. የሚድረስ ነው። የዚህ የመሬት ንብርብር ባህርይ፤ የላይኛው ክፍል ይዘት ፈሳሽም ጠንካራም ያልሆነና መካከለኛ ባህርይ ሲኖረው፤ የታችኛው ክፍል ግን ጠንካራ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ስለሆነ የመጠንከር ባህርይ አለው።

3. **እምብርተ መሬት፤** መካከለኛው ውስጣዊ የመሬት ንብርብር ሲሆን በአማካይ እስከ 3470 ኪ.ሜ. ጥልቀት አለው፡፡ እምብርተ መሬት በአብዛኛው ክብደት ያላቸው ማዕድናት እንደ ብረትና ኒኬል በውስጡ የያዘ ነው፡፡ እምብርተ መሬት በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፤

**ሀ. ውጫዊው እምብርተ መሬት፤** የሚገኘውም በፈሳሽ መልክ ነው፡፡

**ለ.ውስጣዊው እምብርተ መሬት፤** ጠንካራው እምብርተ መሬት ክፍል ነው፡፡




ሥዕል 1.8 የመሬት ንብርብሮች

## መ ልመ ጃ 1.2

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. ዋና ዋና የቅርፊተ መሬት ይዘቶችን ዘርዝር/ሪ፡፡
2. ሃይድሮስፌርን በአጭሩ ግለፅ/ጪ፡፡
3. ወስጣዊው የመሬት አካል መረጃ እንዴት ይገኛል?
4. አምብርተ መሬት በስንት ይከፈላል? ባህርያቸውን ግለፅ/ጪ፡፡

## 1.3. ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ነገሮች

**ግምገማ ጥያቄዎች**

1. ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ንጥረ ነገሮች ምንድናቸው?
2. ማዕድናት ምንድናቸው?
3. ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ማዕድናት ዘርዝር/ሪ፡፡
4. መሬት የተፈጠረችው ከየትኞቹ አለቶች  ነው?.

ቅርፊተ መሬት የተሠራው ከአለቶች ነው፡፡ አለቶች ደግሞ የተሠሩት ከንጥረ ነገሮች ነው፡፡ ቅርፊተ መሬት የላይኛው የመሬት ክፍል ሲሆን ጠንካራው የመሬት ክፍል (ሊቶስፌር) ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ቅርፊተ መሬት ያለው ጥልቀት  ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡

### 1.3.1 ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ዋና ዋና ንጥረ ነገሮች

ቅርፊተ መሬት የተሠራው ከስምንት ትላልቅ ንጥረ ነገሮች  ነው፡፡ እነሱም ኦክስጅን፤ ሲልከን፤ አልሚኒየም፤ ብረት፤ ካልሲየም፤ ሶድየም ፖታሲየምና ማግኒዚየም ናቸው፡፡ የእነዚህን ንጥረ ነገሮች  ዝርዝር ከሚከተለው ሠንጠረዥ ተመልከት/ቺ፡፡

**ሠንጠረዥ 1.2  ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ንጥረ ነገሮች**

| ተ.ቁ | ንጥረ ነገሮች | መጠን በ% |
|---|---|---|
| 1 | ኦክስጅን | 47 |
| 2 | ሲልከን | 28 |
| 3 | አልሙኒየም | 8 |
| 4 | ብረት | 5 |
| 5 | ካልሲየም | 35 |
| 6 | ሶድየም | 3 |

| | | |
|---|---|---|
| 7 | ፖታሲየም | 2.5 |
| 8 | መግኒዝየም | 2 |

### 1.3.2 ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ዋና ዋና ማዕድናት

ማዕድናት የተፈጠሩት ከንጥረ ነገሮች ነው፡፡ ዋና ዋና ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ማዕድናት ውስጥ የተወሰኑት፤ ወርቅ፤ አልማዝ፤ መዳብ፤ ኳርትዝ፤ ፖታሽ፤ ግራናይትና የነዳጅ ማዕድናት ናቸው፡፡ አብዛኛው ማዕድናት በጠጣር መልክ የሚገኙ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በፈሳሽ መልክ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ጠጣር ማዕድናት የሚባሉት እንደ የከሰል ድንጋይ፤ ግራናይትና የመሳሰሉት ሲሆኑ በፈሳሽ መልክ የሚገኙት ደግሞ እንደ ነዳጅ ዘይት ያሉ ናቸው፡፡





**ሥዕል 1.9 የተለያዩ ማዕድናት**

### 1.3.3 ቅርፊተ መሬት የተሠራባቸው ትላልቅ አለቶች

አለቶች ከተለያዩ ማዕድናት የተሠሩ ናቸው፡፡ አለቶች ከተሠሩባቸው ማዕድናት ዓይነት ለይ ተሞርክዞ የተላያዩ ባህርይ አለቸው፡፡ አንዳንድ አለቶች ጠንካራ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ጠንካራ ያልሆኑ ናቸው፡፡ ይህ ልዩነት በይዘታቸውና በአፈጣጠራቸው ላይ ይወሰናል፡፡ በዚህ መሠረት አለቶች በሦስት ይከፈላሉ፡፡

#### ሀ) ቅልጠተ አለት

በመሬት ውስጥ ከፍተኛ ሙቀት የለበት ቦታ ያሉ ነገሮች ሁሉ በመቅለጥ ወደ ፈሳሽነት ይቀየራሉ፡፡ በዚህ መልክ ያለው ፈሳሽ ነገር ማግማ ይባላል፡፡ ይህ ማግማ በእሳተ ጎሞራ አማካይነት ወደ ውጫዊው የመሬት ክፍል ይወጣል፡፡ ማግማ ወደ ቅርፊተ ማሬት በመውጣት ስፈስ **ለቫ** ይባላል፡፡ ይህ ላቫ ቀስ በቀስ እየቀዘቀዘ ሲሄድ አለት ይፈጥራል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው አለት ቅልጠተ አለት ይባላል፡፡ ለምሳሌ ግራናይትና ባልጩት ይጠቀሳሉ፡፡




**ሥዕል 1.10 ቅልጠተ አለቶች**

#### ለ) ዝቅጠተ አለት

ይህ አለት ከተለያዩ ነገሮች ስብርባሪ፤ በውሃ፤ በንፋስና በበረዶ

መንሸራተት አማካይነት ተወስደው አንድ ቦታ ላይ ከተጠራቀመው ክምችት በመጠንከር የሚፈጠር አለት ነው፡፡ ይህ ክምችት የድንጋይ ስብርባሪ፤ አፈር፤ የዕፅዋት ብስባሽና የእንስሳት ቅሪተ አካልን የያዘ ነው፡፡ በየአመቱ አዳዲስ ጥርቅሞች እየተደራረበ ይሄዳሉ፡፡ የላይኛው ጥርቅም የታችኛው ላይ ክብደቱ እየጨመረ ወደታች በመጫን ወደ ጠንካራ አለት ይቀይረዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈጠረው አለት ዝቅጠተ አለት ይባላል፡፡ ለምሳሌ፤የአሸዋ ድንጋይ፤የኖራ ድንጋይና የድንጋይ ከሰል ናቸው፡፡



**ሥዕል 1.11 ዝቅጠተ አለት**

ሐ) **ለውጥ አለት**

ይህ አለት በከፍተኛ ሙቀትና ግፊት አማካይነት ከነበሩት ከቅልጠተ አለትና ዝቅጠተ አለት የተፈጠረ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ኬሚካላዊና ፍዚካላዊ ለውጦች ይፈጠራሉ፡፡



**ሥዕል 1፡12 ለውጥ አለት**

## 1.4. የአለቶች ሥርጭትና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ

**የግምገማ ጥያቄዎች**


1. በኢትዮጵያ ውስጥ የአለቶች ሥርጭት ምን ይመስላል?
2. በኢትዮጵያ ውስጥ በብዛት የሚገኙት አለቶች የትኞቹ ናቸው?
3. የአለቶች ጥቅም ምንድን ነው?

**የአለቶች ሥርጭት**

ኢትዮጵያ ውስጥ አለቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ተሰራጭተው አይገኙም፡፡ በብዛት ተሰራጭተው የሚገኙት ቅልጠተ አለቶች ሲሆኑ የሚገኙበትም በመካከለኛው ከፍተኛ አካባቢዎችና በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው፡፡

ዝቅጠተ አለቶች የሚገኙባቸው ቦታዎች ደግሞ በሱማሌ ክልላዊ መንግስት፣ በኦሞና በአዋሽ ወንዞች ሸለቆ በማካከለኛው የአበይ ወንዝ አከባቢ በስፋት ተከማችቶ ይገኛል፡፡

**በሌላ በኩል ለውጥ አለቶች የሚገኙባቸው አከባቢዎች** ከመቀሌ ከተማ አካባቢ ተነስቶ ወደ ምዕራብ የተከዜን ወንዝ ሸለቆ በመከተል እስከ ሱዳን ይደርሳል፡፡ በተጨማሪም በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምዕራብ ወለጋ፣ የባሮ ወንዝ ሸለቆ፣ ከሐረር ከተማ አንስቶ እስከ ጅግጅጋ ከተማ ይደርሳል፡፡




ሥዕል 1.12. የአለቶች ሥርጭት

**የአለቶች ጥቅም**

አለቶች ብዙ ጥቅም አላቸው፡፡ አለቶች የተለያዩ ማዕድናት በውስጣቸው ስለያዙ በአገር ኢኮኖሚ ውስጥ የተለያዩ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይህንን የአለቶችን ጠቀሜታ ከሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልከት/ቺ፡

**ሠንጠረዥ1.3. አለቶች በኢኮኖሚ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ**

| የአለት ዓይነቶች | የማዕድናቱ ምሳሌ | በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ |
|---|---|---|
| ቅልጠተ አለት | ባልጩት፤ግራናይትና የአሸዋ ድንጋይ | ለህንፃና ለመንገድ ግንባታ |
| ዝቅጠተ አለት | የድንጋይ ከሰል፤ ነዳጅ ዘይት፤ የተፈጥሮ ጋዝ አሞሌ ጨውና የኖራ ድንጋይ | ለግንባታ፤ ለሐይል ምንጭ፤ ለፅሕፈት፤ ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃነትና ለምግብነት |
| ለውጥ አለት | እብነ በረድ፤ ዕንቁ (አልማዝ) ዩራኒየምና ወርቅ | ለግንባታ፤ ለጌጣጌጥ፤ ለፋብሪካና ለውጭ ምንዛሪ |

መልመጃ 1.3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ፡፡

1. ዋና ዋና ቅርፍተ መሬት የተሰራባቸውን ንጥረ ነገሮች ዘርዝር/ሪ፡፡
2. ማዕድን ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ/ጪ፡፡
3. ሶስቱን ዋና ዋና አለቶችን ዘርዝር/ሪ፡፡
4. በኢትዮጵያ ውስጥ የሶስቱ ዋና ዋና አለቶች መገኛ ቦታዎች ፃፍ/ፊ፡፡
   ሀ. ቅልጠተ አለት
   ለ. ዝቅጠተ አለት
   ሐ. ለውጥ አለት

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

በሥርዓተ ፀሐይ ውስጥ የሚገኙ ነገሮች ፀሐይ፤ ኘላኔቶች፤ ጨረቃዎች፤ አስተሮይዶች፤ ከሜቶች፤ ሜትሮይቶችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በሥርአተ ፀሐይ ውስጥ ከሚገኙ ነገሮች ፀሐይ 99.86 % ትሸፍናለች፡፡ ፀሐይ የራሷ የሆነ ብርሃንና ሙቀት ያላት ስትሆን ከመሬት ያላት ረቀት 150,000,000 ኪ.ሜ ይሆናል፡፡

ኘላኔቶች በራሳቸው ምህዋር ላይ ፀሐይን ይዞራሉ፡፡ የመሬት ውጫዊ አካሎች፤ ደረቁ የመሬት ክፍል፤ ውሃማ የመሬት ክፍል፤ ከባቢ አየርና ህይወት ያላቸው የመሬት ክፍል ናቸው፡፡

ውስጣዊው የመሬት አካል በሶስት ታላላቅ ንብርብሮች ይከፈላል፡፡ እነሱም ቅርፊተ መሬት፤ መዕከለ መሬትና ዕምብርተ መሬት ናቸው፡፡

የውስጣዊውን የመሬት ክፍል መረጃ ለማግኘት ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ዘዴዎችን እንጠቀማለን፡፡

የአለቶች አፈጣጠር ሁኔታ መለያየት የተለያየ ጥቅሞች እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ክፍል 1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ/ሽ**

1. ሁለም ፕላኔቶች በተመሰሳይ አቅጣጫ ፀሐይን ይዞራሉ፡፡
2. የትልቁ ሜራዲያን/ Green which meridian/ ርዝመት ከምድር ወገብ (Equator) ርዝመት ይበልጣል፡፡
3. እኛ የምንኖርባት መሬት ከ8 ንጥረ ነገሮች የተሠራ ነዉ፡፡
4. ማዕድናት በአፈጣጠራቸው ሁኔታ በጥንካሬአቸው ይለያያሉ፡፡
5. ቅልጠተ አለት ከማግማ የተፈጠረ ዓለት ነው፡፡

**ክፍል 2. በ "ለ "ሥር የዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ከተሰጡት ጋር አዛምድ/ጅ**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 6. በሥርአተ ፀሐይ እምብርት የሚትገኝ | ሀ. ሜርኩር |
| 7. ጧትና ማታ የምትታይ ኘላኔት | ለ. ቨኔስ |
| 8. ብዙ ጨረቃዎች ያላት ኘላኔት | ሐ. ሳተርን |
| 9. ለፀሐይ ቀርባ የሚትገኝ ፕላኔት | መ. ዝቅጠተ አለት |
| 10. በፊት ከነበሩት አለቶች የተፈጠረ | ሠ. ቅልጠተ አለት |
| 11. ከላቫ የተፈጠረ አለት | ረ. ፀሐይ |
| 12. በተለያዩ ምክንያት ከተከማቸ የተፈጠረ አለት | ሰ. ለውጥ አለት |

**ክፍል 3. ከሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘው ፊደል በመምረጥ ፃፍ/ፊ**

13. በፀሐይና በመሬት መካከል ያለው ርቀት ምን ያህል ነው፡፡

ሀ. 150,000 ኪ.ሜ ሐ. 150. ኪ.ሜ

ለ. 150,000,000 ኪ.ሜ መ. 1500 ኪ.ሜ

14. ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትንሹ ኘላኔት የትኛው ነው?

ሀ. መሬት ሐ. ጁኘቴር

ለ. ሳተርን መ. ኡራኑስ

15.ከሚከተሉት ማዕድናት ውስጥ የበለጠ ጥንካሬ ያለው የቱ ነው?

ሀ. ጅብሰም ሐ. ዕንቁ /ዲያመንድ/

ለ. ኳርቲዝ መ. ካልሳይት

16. በዝቅጠተ አለት ሥር የማይመደብ የቱ ነው?

ሀ. የአሸዋ ድንጋይ ሐ. የኖራ ድንጋይ

ለ. ባዛልት መ. የድንጋይ ከሰል

**ክፍል 4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታውን በመሙላት መልስ/ሽ**

17.በሥርዓተ ፀሐይ ውስጥ የሚገኝ ትልቁ ኘላኔት ---------- ይባላል

18.የመሬት የጨረቃ ብዛት ---------- ስሆን ከመሬት ጋር እኩል የጨረቃ ብዛት ያላት ኘላኔት ደግሞ ------- ትባላለች

**ክፍል 5. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ**

19.የመሬት ንብርብሮች በስንት ይከፈላሉ? ስማቸውን ዘርዝር/ሪ።

20.ከመሬት ንብርብሮች ውስጥ ወፍራሙ ንብርብር የትኛው ነው?

# ምዕራፍ 2

# ዝግመታዊ የሰው ልጅ ለውጥና የዓለም ህዝብ

ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች

- ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር ሁኔታ ትገልፃለህ/ሽ
- የሰው ልጅ አፈጣጠር ምንጭ የሆኑ የአርክኦሎጂ ምርምር ቦታዎችን በካርታ ላይ ታሳያለህ/ሽ
- የህዝብ ቁጥር መጨመርና ስርጭት ሁኔታ ትገልፃለህ/ሽ
- የሰው ልጅ ቁጥር መቀያየር/በውልደት፣ በሞትና ስደት/ ምክንያቶች የሚከሰተውን ሒሳባዊ ስሌት ታሰላለህ/ሽ
- የመጓጓዣ ዓይነቶችና  ጥቅማቸውን ትገመግማለህ/ሽ
- በመንገዶች ላይ የሚገኙትን መሠረታዊ የትራፊክ ምልክቶችን በመለየት ታሳያለህ/ሽ

## መግቢያ

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ሥርዓተ ፀሐይን፣ የመሬት አፈጣጠርና ፊዝካላዊ ባህሪያትን ተምረሃል/ሻል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ አለምና ኢትዮጵያ ህዝብ ትማራለህ/ሽ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስለ ሰዎች ቁጥር

መጨመርና የአሰፋፈር ሁኔታ፣ የህዝብ ቁጥር መቀየር፣ የህዝቦች ሥርጭትና የከተሞች መስፋፋትን ትማራለህ/ሽ፡፡ በተጨማሪም ስለ መጓጓዣ፣ የመጓጓዣ ዓይነቶች፣ የትራፍክ ህጐችን፣ የመንገድ አጠቃቀምን፣ የትራፍክ አደጋንና መንገድን ስናቋርጥ መወሰድ የሚገባንን ጥንቃቄዎችን ትማራለህ/ሽ፡፡

**ተማሪዎች ብያንስ ሊደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃቶች፤**

- የሰው ልጆች የአርክዎሎጂ ጥናት ምንጭ የሆኑ ቦታዎችን ትለያለህ/ሽ
- በተለያዩ ጊዜያት የሰው ልጅ ያሳየው ታሪካዊ ለውጦችን ትገነዘባለህ/ሽ
- ካለፉትና አሁን ባለው መረጃዎች መሰረት በማድረግ የወደፊቱን የህዝብ ቁጥር ሁኔታን ትገነዘባለህ/ሽ
- የህዝብ ቁጥር የሚቀይሩ ኩነቶች /ውልደት፣ ሞትና ስደት/ ወዘተ ታሰላለህ/ሽ
- የህዝብ ስደት ዓይነቶችና የስደት ምክንያቶችን ትለያለህ/ሽ
- በአለም ላይ ህዝብ ተጠጋግተውና ተበታትነው የሚገኙባቸውን አከባቢዎች በካርታ ላይ ታሳያለህ/ሽ
- የኢትዮጵያንና ከአለም ህዝብ ቁጥር መጨመር ታመዛዝናለህ/ሽ
- የትራንስፖርት ታሪካዊ ዕድገትና አስተዋፅዖ ትገልፃለህ/ሽ
- ጥቅማቸውን መሠረት በማድረግ የትራንስፖርት ዓይነቶችን ታወዳድራለህ/ሽ
- መሠረታዊ የሆኑ የመንገድ ላይ የትራፊክ ምልክቶችን ትለያለህ/ሽ
- የትራፊክ ደህንነትን ለመጠበቅ መሠረታዊ የሆኑ የትራፊክ ህጐችን ትገልፃለህ/ሽ

# 2.1 የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ


## 2.1.1 አርኪዮሎጂና የአርኪዮሎጂ ምርምር

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ቀደምትና አሁን ያለው የሰው ልጅ ተመሳሳይነት አላቸው? እንዴት?
2. አርክኦሎጂ ስለ ምን ያጠናል?
3. የሰው ልጅ መገኛ ናቸው ተብለው ከሚገመቱ ቦታዎች ውስጥ የሚታወቀው/ቂውን ተናገር/ሪ?

ስለ ሰው ልጆች አመጣጥ ሁለት የተለያዩ ሃሳቦች አሉ። እነሱም ሃይማኖታዊና ሳይንሳዊ ሃሳቦች ናቸው። ሃይማኖታዊው አስተሳሰብ ሰውን የፈጠረው እግዚአብሔር ነው ተብሎ ይታመናል። በዚህ አስተሳሰብ ሁሉም ሃይማኖቶች ተመሳሳይ የሆነ ግምት አላቸው።

በሳይንሳዊ አመለካከት ግን የሰው ልጅ በዝግመታዊ ለውጥ ሂደት አማካይነት በብዙ ሚሊዮን አመታት ውስጥ የተለወጠ ነው ተብሎ ይታመናል። ይህንን ሂደት ለመረዳት ቀጥለው ያለው ሥዕል ተመልከት/ቺ



**ሥዕል 2.1 የሰው ልጅ ዝግምታዊ ለውጥ**

በሰው ልጅ ታርክ ውስጥ ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ የሰው ልጅ መገኛ መሆናቸውን ከፍተኛ ግምት ተሰቶዋቸዋል። የተለያዩ የምርምር መረጃዎች እንደሚያሳዩት ምግብን ማዘጋጀትና የተለያዩ መሣሪያዎችን መስራት

የተጀመረበት አከባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህ ዕድገት ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓላቲከዊ ለውጦች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

ቻርለስ ዳርዊንና ሌሎች ምሁራን የሰውና የዝንጀሮ ዝርያ የተገኙት ከአንድ ዘር ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ በእነዚህ ምሁራን አገላለፅ የሰውና የዝንጀሮ ዘር ከጋራ ቤተሰብ የተገኙ ሆኖ ከጊዜ በኃላ ግን የሰው ዝሪየ ሆሚኒድ ሲባል የዝንጀሮ ዝርያ ደግሞ ፖንጁዴ ተባለ፡፡

አርኪዮሎጅ ማለት ቅሪተ አካልና ሲጠቀሙባቸው የነበሩትን መሣሪያዎችን በማጥናት የሰው ልጅ አኗኗር የሚያጠና ሳይንስ ነው፡፡ አርኪዮሎጅስቶች የሰው ልጅ ማገኛ በኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

## 2.1.2 የመጀመሪያ የሰው ልጅ መገኛና በተለያዩ ጊዜያት ያሳለፋቸው ለውጦች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታውቀውን የሰው ልጅ ቅሪተ አካል ለክፍል ተማሪዎች ተናገር/ሪ
2. ሉሲ ምንድነው? ለክፍል ተማሪዎች ተናገር/ሪ

ከዘመናዊው የሰው ልጅ በፊት የተለያዩ የሰው ዝርያዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፤

- **አውስትራሎፒቲከስ፤** ይህ የሰው ዘር በፖንጁዴና በሆሚኒድ ከተከፈለ በኃላ የተገኘ ነው፡፡ ይህ የሰው ዘር ከሁለት ሚሊዮን ዓመታት በፊት በምስራቅና ደቡብ አፍርካ ውስጥ ይኖር እንደነበር ይነገራል፡፡ አውስትራሎፒቲከስ ዘርያ ዝንጀሮ ቢመስልም ይበልጥ ሰውን የሚመስል ስለሆነ በሁለት እግሩ ቆሞ የሚሄድ ነበር፡፡ ይህ ዘርያ በዝግመታዊ ለውጥ ቀስ በቀስ ወደ ሆሞ ተቀየረ፡፡ የሆሞ ዘርያ በዕድገት ደረጃው በሶስት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡-
- **ሆሞ ሐቢሊስ፤** ከሁለት ሚሊዮን አመታት በፊት የኖረና በእጁም

ሥራ መሥራት የጀመረ ነበር፡፡ ቅሪተ አካሉም ኢትዮጵያ ውስጥ በኦሞ ሸለቆ ተገኘ ፡፡ ይህ ዝርያ መሳሪያዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ መሥራት የጀመረ ነው፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች ከድንጋይ የተሰሩ ናቸው፡፡ እነዝህ መሣሪያዎች እንስሳት ለማረድና ቆዳቸውን ለመግፈፍ ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡

- **ሆሞ እሬክተስ፤** ከአንድ ሚሊዮን አመታት በፊት ይኖር የነበረ ሲሆን በሁለት እግሮቹ ቆሞ መሄድ የጀመረ ዝርያ ነው፡፡ ቅሪተ አካሉም በኢትዮጵያ መልካ ቁንጡሬና በኦሞ ሸለቆ ውስጥ የተገኘ ነው፡፡ ሆሞ እሬክተስ በሁለት በኩል ስለት ያለው መሳሪያ መስራት ችሏል፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች ለእርድ፣ ቆዳ ለመግፈፍ፣ ሥራሰሮችን ቆፍሮ ለማውጣትና እንጨት ለመቁረጥ ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ እነዚህም መሳሪያዎች ቅርስ በአብዛኛው በኢትዮጵያና በሌሎች ምሥራቅ አፍሪካ ተገኝቷል፡፡
- **ኦሞ ሳፒያንስ ፤** አሁን ካለው የሰው ዘርያ ጋር በጣም ተቀራራቢና፣ ከ100,000 አመታት በፊት የኖረ ነው፡፡ ቅሪተ አካሉም ኢትዮጵያ ውስጥ በኦሞ ሸለቆ ፣በአዋሽ ወንዝና በድሬዳዋ አከባቢ የተገኘ ነው፡፡ ይህ ዝርያ መሳሪያዎችን አሻሽሎ ከድንጋይ እንደ ምላጭና መያዣ ያለው ጦር በብዛት መስራት ችሏል፡፡

በአጠቃላይ አሁን ካለው ዘመናዊው የሰው ዘር በፊት ሰው የተለያዩ ዝግመታዊ ለውጥ ውስጥ አልፏል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ ከዚህ በታች ያለውን ሠንጠረዥ ተመለከት/ቺ፡፡

**ሠንጠረዥ 2.1 የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ**

| ተ.ቁ | የሰው ዝርያ ሥም | ዕድሜ | የሚገኝበት ቦታ |
|---|---|---|---|
| 1. | ሆሚነድ | ከ6 - 8 ሚሉዮን አመታት | ደቡብ አፍሪካና ቻድ ሐይቅ |
| 2 | አውስትራሎፒትከስ ራማድስ | 4.5 ሚሊዮን አመታት | አራሚስ፣አፋር |
| 3 | የሉሲ አጥንት | 3.18 ሚሊዮን አመታት | ሀዳር፣ አፋር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | አውስትራሎፒትከስ ጋሃሪ፣ ኢትጵከስ | | አዋሽና ኦሞ ወንዞች አካባቢ |
| 5 | ሆሞ ሐቢሊስ | ከ2.5 እስከ 1.9 ሚሊዮ አመታት | ጐና፣ሹንጉራና በታችኛው ኦሞ |
| 6 | ሆሞ ኢሬክተስ | 1.5 ሚሊዮን አመታት | መልካ ቁንጡሬ፣ ጋርዱላና ጋዴቢ |
| 7 | ሆሞ ሳፒያንስ | 100000 አመታት | ባዶ፣ ፓርክ ኢፒክና ኪኚሽ |

መልመጃ 2.1

1. ስለ ሰው ልጆች አፈጣጠር የሚገልፁ ሀሳቦች ምንድናቸው?
2. ጥንታዊ የሰው ዘርያን በቅደም ተከተል ጻፍ/ፊ፡፡
3. ቅርሶችን በማጥናት ስለ ሰው ዘር አመጣጥ የሚያጠና ሳይንስ ምን ይባላል?
4. ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለቱም በኩል ስለት ያለውን መሳሪያ የሰራ የሰው ዘር ማን ይባላላ? ከምን የተሰራና ለምን ይጠቀሙበት ነበር?

## 2.2 የዓለም ህዝብ

**የማምገማ ጥያቄ**

1. ህዝብ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአለም ህዝብ ሥርጭት ምን ይመስላል?
3. በአለም ላይ የህዝብ ቁጥር መጨመር ምን ይመስሰላል?

ህዝብ ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ ሰዎች በብዛት ለረጅም ጊዜ የሚኖሩበት ማለት ነው፡፡ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚገልፁት የህዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ከፍተኛው የህዝብ ቁጥር የታየው ከክርስቶስ ልደት በፊት 10000 ዓመተ ዓለም አከባቢ ነበር፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያትም ከሚያመርታቸው ነገሮች በቂ ምግብ ማግኘት በመቻሉ

ነው፡፡

በአለም ላይ በሁሉም አካባቢዎች የህዝብ ብዛት በተመሳሳይ ሁኔታ ተሰራጭቶ አይገኝም፡፡ በአንዳንድ አከባቢዎች ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ሲሆን፤ በአንዳንድ አከባቢዎች ደግሞ ቀስ በቀስ እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ለአለም ህዝብ ቁጥር መለያየት ምክንያት የሆኑት የአየር ንብረት፣ የምግብ አቅርቦት፣ በሽታ፤ የመሬት አቀማመጥትና ጦርነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በኢኮኖሚ ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች መካከል የህዝብ ቁጥር ዕድገት ብዙ ልዩነቶች አለው፡፡ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በቀላሉ ለመረዳት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተመለከት/ች፡፡

**ሠንጠረዥ 2.2. የአለም ህዝብ ብዛት**

| ተ.ቁ | አህጉር | ህዝብ/በሚሊዮን/ | በመቶ(%) |
|---|---|---|---|
| 1 | ኢሲያ | 4393 | 59.78 |
| 2 | አፍሪካ | 1186 | 16.14 |
| 3 | አውሮፓ | 738 | 10.04 |
| 4 | ሰሜን አሜርካ | 634 | 8.62 |
| 5 | ደቡብ አሜርካ | 358 | 4.87 |
| 6 | አዉስትራሊያ | 39 | 0.53 |
| 7 | ጠቅላላ የአለም ህዝብ | 7348 | 100 |

ምንጭ UN department of economic and social affairs 2015

## 2. 2.1 የህዝብ ቁጥር መጨመር

**የግምገማ ጥያቀዎች**

1. ለህዝብ ቁጥር መቀያየር ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?
2. ስደት በአለም ህዝብ ቁጥር ላይ ለውጥ ልያመጣ ይችላል? ለምን?

የአንድ ሀገር ህዝብ ቁጥር ሁልጊዜም ቋሚ አይደለም፡፡ የህዝብ ብዛት በቦታና በጊዜ ይለያያል፡፡ ለአንድ አገር ህዝብ ቁጥር መቀያየር ምክንያት ከሆኑ ነገሮች ዋናዎቹ፤ ውልደት፣ ሞትና ስደት ናቸው፡፡ ውልደት የህዝብ ቁጥር እንዲጨምር ሲያደርግ ሞት ደግሞ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡

ይሁን እንጂ ስደት የህዝብ ብዛት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡ ስደት የህዝብ ቁጥር ሊቀንስ የሚችለው ሰዎች በቋሚነት ዜግነታቸውን ቀይረው ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ሲሰደዱ ነው፡፡ ስደት በአለም ህዝብ ቁጥር ላይ ለውጥ አያመጣም፡፡

## ውልደት

ውልደት የህዝብ ቁጥር መጨመር ተፈጥሮአዊ ሂደት ነው፡፡ የህዝብ ቁጥር መቀያየር ሂደት ውስጥ ስለ ውልደት ማጥናት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የውልደት መጠን ስሌት

የውልደት መጠንን ለማስላት የሚከተለውን የሒሳብ ቀመርን እንጠቀማለን

ምሳሌ ፤ በ2010 ዓ.ም. ውስጥ በ"ሀ" አገር የተወለዱት ህፃናት 300,000 ናቸው፡፡ የዚያ ሀገር ጠቅላለ የህዝብ ብዛት ደግሞ 15000000 ቢሆን የውልደት መጠን ምን ያህል ይሆናል፡፡

ለዚህ ጥያቄ መልስ ከመስጠትህ/ሽ በፊት የተሰጠውንና የተጠየከውን/ሽውን ጥያቄ መለየት ይኖርብሃል/ሻል፡፡

| የተሰጠ | የሚፈለግ |
|---|---|
| የተወለዱ ህፃናት = 300,000 | የውልደት መጠን? |
| የህዝብ ብዛት =15,000,000 | |
| ስሌት | |

$$\text{የዉልደት መጠን} = \frac{\text{በአንድ አመት ውስጥ በህወት የተወለዱ የህፃናት ብዛት}}{\text{የዘ የን አመት ዓጋማሽ የአገሬተ አ የህዝብ ብዛት}} X1000$$

$$\textbf{የዉልደት መጠን} = \frac{300,000}{15000000} X1000$$

$$\textbf{የዉልደት መጠን} = \frac{300}{15}$$

$$= 20//$$

ይህ ማለት በ1000 ሰዎች ውስጥ 20 ህፃናት በተጠቀሰው ዓመት የተወለዱ ናቸው፡፡

**ሞት**

ሞት የአለም የህዝብ ቁጥር የሚቀንስና በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ኩነት ነው፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በአሁኑ ጊዜ የሞት ቁጥር በአለም ላይ እየቀነሰ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያት የሚሆነው የእርሻና የጤና ተክኖሎጂዎች መሻሻል፣ የአከባቢና የግል ንፅህና አጠበበቅ መሻሻል ቁልፍ ምክንያቶች ናቸው፡፡

**የሞት መጠን ስሌት**

ለምሳሌ፤ በ2013 ዓ.ም ውስጥ በ"M" አገር የሞቱት የሰዎች ቁጥር 20000 ነው፡፡ በዚህ አጋማሽ ዓመት የአገሪቱ የህዝብ ብዛት ደግሞ 5000000 ነው፡፡ የአገሪቱ የሞት መጠን ስንት ነዉ?

| **የሰተጠ** | **ተፈላጊ** |
|---|---|
| የሞቱ ሰዎች ቁጥር 20000 | |
| ጠቅለላ ህዝብ ብዛት 5000000 | የሞት መጠን ? |

**ስሌት**

$$\text{የሞት መጠን} = \frac{\text{በአንድ አመት ውስጥ የሞቱት የሰዎች ብዛት}}{\text{የዚያን አመት ዓጋማሽ የአገሪቷ አ የህዝብ ብዛት}} X1000$$

$$\text{የሞት ማጠን} = \frac{20000}{5000000} x1000$$

= 4//

**ይህ ማለት** በ2013 **ዓ.ም** በ"M" **ሀገር** ከ1000 **ሰዎች ውስጥ** 4 **ሰዎች ሞተዋል ማለት ነው፡፡**

## ስደት

**ስደት ማለት ሰዎች ከሚኖሩበት ቦታ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የሚኖሩበትን ቦታ ሲቀይሩ ነው፡፡**

**የሰደት መጠን ስሌት**

### ሀ. ወደ አገር የሚደረግ የስደት መጠን ስሌት

$$\text{ወደ አገር የስደት መጠን} = \frac{\text{በስደት ወደ አገር የሚገቡ ሰዎች ብዛት}-}{\text{የዚያን አመት ዓጋማሽ የአገሪቷ የህዝብ ብዛት}} X1000$$

ስደት ወደ አገር የሚገቡ የሰዎች ብዛት 300 000፤

የዚያን ዓመት አጋማሽ የአገሪቱ የህዝብ ብዛት 60 000 000

ወደ አገር የስደት መጠን?

$$\text{ወደ አገር የስደት መጠን} = \frac{300\ 000}{60000000} X1000$$

= 5//

**ይህ ማለት ከአገሪቱ** 1000 **ሰዎች ላይ ከውጪ** 5 **ሰዎች ተጨምረውባቸዋል ማለት ነው፡፡**

**ለ. ከአገር ወደ ውጪ የሚደረግ የሰደት መጠን ስሌት**

$$ከአገር ወደ ውጪ የሰደትመጠን = \frac{ከአገር ወደ ውጪ በስደት የሚወጡ ሰዎች ብዛት}{የዚያን አመት ዓጋማሽ የአገሪቷ የህዝብ ብዛት} X1000$$

| የሰተጠ | ተፈላጊ |
|---|---|
| ወደ ውጪ የሚደረግ የስደት ብዛት = 60000 | ወደ ውጪ ስደት መጠን? |
| የዚያን ዓመት አጋማሽ የአገሪቱ የህዝብ ብዛት= 60000000 | |

$$ከአገር ወደ ውጪ የስደት መጠን = \frac{60\ 000}{60000000} X1000$$

$$=\mathbf{1}//$$

ይህ ማለት በአገሪቱ 1000 ሰዎች ላይ 1 ሰው በስደት ተቀንሷል ማለት ነው፡፡

**ሐ. የስደት ልዩነት**

የስደት ልዩነት ማለት ወደ ሀገር የሚገቡና ከአገር የሚወጡ የሰዎች የቁጥር ልዩነት ማለት ነው፡፡ ውጤቱ +Ve፣ −ve ወይም 0 ሊሆን ይችላል፡፡

- ውጤቱ +Ve ከሆነ ወደ ሀገር የሚገቡ የሰዎች ቁጥር ይበልጣል ማለት ነው፡፡
- ዉጠቱ −ve ከሆነ ደግሞ ከሀገር የሚወጡ የሰዎች ቁጥር ይበልጣል ማለት ነው፡፡
- ውጤቱ 0 ከሆነ ደግሞ ከሀገር የሚወጡና ወደ ሀገር የሚገቡ የስደተኞች ቁጥር እኩል መሆኑን ያሳያል፡፡

**ይህ በሒሳብ ስሌት ሲገለፅ**

$$\text{የስደት ልዩነት መጠን} = \frac{\text{ወደ አገር የስደት መጠን} - \text{ወደ ውጪ የስሌት መጠን}}{\text{የአመቱ ዓጋማሽ የአገሪቱ ህዝብ ብዛት}} X1000$$

| **የስተጠ** | **ተፈላጊ** |
|---|---|

ወደ አገር የሚደረግ የሰደት መጠን ስሌት =300000 የስደት መጠን?

ከአገር ወደ ውጪ የሚደረግ የሰደት መጠን ስሌት=60000

$$\text{የስደት ልዩነት} = \frac{300000 - 60\ 000}{60\ 000\ 000} X1000$$

$$\text{የስደት ልዩነት} = \frac{24}{6}$$

= 4//

ይህ ማለት ወደ አገር ያለው የስደት መጠን ወደ ውጪ ካለው የስደት መጠን በ4 ሰዎች ይበልጣል ማለት ነው።

## 2.2.2 የሰዎች ቁጥር መቀያየር ባህሪያት

**የግምገማ ጥያቄ**

1. በማምረት ችሎታ መሰረት ሰዎች በስንት በዕድሜ ክልል ይከፈላሉ?
2. የህዝብ መዋቅር ማለት ምን ማለት ነው?
3. የአምራች ኃይል ዕድሜ ስንት ነዉ?

**የህዝብ ማዋቅር** ማለት የተለያዩ መስፈርቶችን ተጠቅመን ህዝብን በተለያዩ የዕድሜ ክልል መክፈል ማለት ነው። የአንድን አገር ህዝብ በዕድሜ ክልል በመለየት ለትምህርት ቤት የደረሱ ህፃናትን አምራች ኃይልን እንዲሁም

አረጋዊያንን ቁጥር ማወቅ የወደፊቱን የአገሪቷን ዕጣ ፋንታ ለመገመት ያስችላል፡፡

ዕድሜና ሥርዓተ-ፆታ መረጃ የሚገኘው በተለያዩ ጊዜያት በሚደረግ የህዝብ ቆጠራ ነው፡፡ የተገኘውን መረጃ በማምረት ችሎታ ተቀናብሮ መቀመጡ በቀላሉ ስለ ህዝቡ ለመረዳት ያስችላል፡፡

የአንድን አገር ህዝብ በማምረት ችሎታው ላይ በመመርኮዝ በሶስት የዕድሜ ክልል ይከፈላል፡፡ እነሱም የልጆች ዕድሜ እስከ 14 ዓመት ያሉ፤ አምራች ኃይል ከ15 — 64 ዓመትና አረጋዊያን 65 እና ከዚያ በላይ ናቸው፡፡

## የጥገኝነት ሬሾ

የጥገኝነት ሬሾ በአምራችና ሰርተው ራሳቸውን የማይችሉ መካከል ያለው ግንኙነት ማለት ነው፡፡ በማምረት ችሎታ ላይ በመመስረት ህዝቡን በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ እነሱም አምራች ኃይልና ጥገኛ ናቸው፡፡
ጥገኛ የሚባሉት ደግሞ እንደገና በሁለት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም ልጆችና አረጋዊያን ናቸው፡፡
በአምራች ኃይልና ጥገኛ መካከል ያለውን ልዩነት በሒሳብ ህግ ማስላት ይቻላል፡፡

## የጥገኝነት ሬሾ ዓይነቶች

### ሀ. የልጆች ጥገኛነት ሬሾ

የልጆች የጥገኝነት ሬሾ ማለት በአምራቹ ኃይል የሚረዱትን የልጆች ቁጥር ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡

ይህን በሒሳብ ህግ ለማስላት፡

$$\text{ከአገር ወደ ውጪ የስደትመጠን} = \frac{\text{ከአገር ወደ ውጪ በስደት የሚወጡ ሰዎች ብዛት}}{\text{የዚያን አመት ዓጋማሽ የአገሪቷ የህዝብ ብዛት}} X100$$

$$\text{የልጆች የጥገኛነት ሬሾ} = \frac{400}{3}$$

= 133//

**ይህ ማለት 100 አምራች ኃይል 133 የሚሆኑ ልጆችን ይረዳሉ ማለት ነው።**

**ለ. የአረጋዊያን ጥገኘነት ሬሾ**

**አረጋዊያን ጥገኘነት ሬሾ ማለት በአምራች ኃይል የሚረዱ አረጋዊያን ቁጥር ለማወቅ ነው።**

**የአረጋዊያን ጥገኘነት ሬሾን ለማስላት፣**

$$\text{የአረጋዊያን ሬሾ} = \frac{\text{የአረጋዊያን ቁጥር}}{\text{የአምራች ኃይል ቁጥር}} \mathbf{X100}$$

**ለምሳሌ** 2009 **ዓ.ም የ**"G" ***ሀገር*** ህዝብ 30 ሚ ሊዮን **ውስጥ** %50 አምራች ኃይል ሲሆን 30% ደግሞ **ህፃናት** ናቸው ። ከዚህ መ ረጃ **የአረጋዊያን ጥገኛነት ሬሾ** ፈልግ።

**የተሰጠ**

**አምራች ኃይል**= %50 = 15 ሚ ሊዮን

ልጆች = %30 = 9 ሚ ሊዮን

መ ልስ

**አረጋዊያን ጥገኘነት ሬሾ የህዝብ አምራቾች - ልጆች**= 30ሚ ሊ.-15 ሚ ሊ-9 ሚ ሊ.= 6 **ሚሊ**

**ወይንም**

**አረጋዊያን** = 20%= 6ሚ ሊ.ዮን

$$\text{አረጋዊያን ሬሾ} = \frac{600}{15} = 40$$

ይህ ማ ለት 100 አም ራ ች ኃይል 40 **አረጋዊያን** ይረዳሉ ማ ለት ነው ።

**የአጠቃላይ ጥገኝነት ሬሾ**

**የአጠቃላይ ጥገኝነት ሬሾ በአምራች ኃይልና ጥገኛ በሆኑ ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ያሳያል። በሒሳብ ቀመር ሲሰላ፡**

$$\text{አጠ ቃ ላይ ሬሾ}=\frac{\text{የልጆች ቁጥር + የአረጋዊያን ቁጥር}}{\text{አምራች ኃይል ቁጥር}}x100$$

ለም ሳሌ፡ በ 2015 ዓ.ም የ“Z” ህዝብ ብዛት 12,000,000 ሚ ሊዮን ው ስጥ 2,000,000 አረጋዊያን፤7,500,000 ደግሞ አም ራች ኃይል ናቸው ። በዚ ህ መ ረጃ **አጠቃለይ ሬሾ ፈልግ።**

$$\text{አጠ ቃ ላይ ሬሾ}=\frac{\text{የልጆች ቁጥር + የአረጋዊያን ቁጥር}}{\text{አምራች ኃይል ቁጥር}}x100$$

$$=\frac{2,500,000+2,000,000}{7,500,000}x100=\frac{4,500,000}{7,500,000}x100$$

$$=\frac{2,500,000,000}{7,500,000}=\frac{2500}{75}=\underline{\underline{33}}$$


**ይ ህ ማ ለት** 100 **የሚ ሆ ኑ አም ራ ቾ ች** 33 **የሚ ሆ ኑትን ጥ ገኞ ች ን ይረዳሉ ማ ለት ነው።**

**የዕድሜ ኘራሚድ**

**የዕድሜ ፒራሚድ ማለት የአንድን ሀገር ህዝብ ዕድሜና ስርዓተ ፆታን ሥርጭት በግራፍ የማሳየት ዘዴ ነው። የአንድን ሀገር የዕድሜና ስርዓተ ፆታን ኘራሚድ በመመልከት በቀላሉ በየትኛዉ የዕድሜ ክልል ውስጥ ብዙ ሰዎች እንደሚገኙ ማወቅ ይቻላል።**

**ከሥር ሰፋ ብሎ ከላይ በፍጥነት እየጠበበ የሚሄደው ግራፍ በማደግ ላይ የሚገኙ አገሮችን ህዝብ ይወክላል። ሁለተኛው ግራፍ ከሥር ጠበብ ብሎ መሓል የሚሰፋና ከላይ ደግሞ በበተወሰነ መልኩ ጠበብ የሚለው ግራፍ ደግሞ ያደጉ አገሮችን ህዝብ የሚወክል ነው።**

ከሥር ሰፋ ብሎ በፍጥነት ወደ ላይ እየጠበበ የሚሄደው ግራፊ የሚያሳየው የውልደት መጠን ከፍተኛ ሆኖ በሞት ምክንያት የተወለደው በብዛት እየቀነሰ መሄዱን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሁለተኛው ፒራሚድ ብዙ ሰዎች ረጅም ዕድሜ ያሉበት አገርን ያሳያል።




ሥዕል 2.2 የዕድሜ ፒራሚድ

**ስርዓተ-ፆታ ሬሾ**

የስርዓተ ፆታ ሬሾ የወንዶችና የሴቶችን ቁጥር ግንኙነት የሚያሳይ ነው።

የስርዓተ ፆታ ሬሾ በሒሳብ ስሌት የሚገለፀው፤

$$\text{የስርዓተ ፆታ ሬሾ} = \frac{\text{የወንዶች ብዛት} \times 100}{\text{የሴቶች ብዛት}}$$

ምሳሌ 1. የአዳማ ከተማ የህዝብ ብዛት 800000 ከሆን ከዚህ ውስጥ 450000 የሚሆኑት ሴቶች ከሆኑ የከተማው የፆታ ሬሾ ስንት ይሆናል?

| የተሰጠ | የሚፈለግ |
|---|---|
| የአዳማ ከተማ ህዝብ ብዛት =800000 | የፆታ ሬሾ? |

የሰቶች ብዛት = 4500000

**ሒሳባዊ ስሌት**

የፃታ ሬሽ = $\frac{\text{የወንዶች ብዛት} \times 100}{\text{ለሰቶች ብዛት}}$

(የወንዶች ብዛት =የአዳማ ከተማ ህዝብ ብዛት- የሴቶች ብዛት→

800,000-450,000 = 350,000

$\frac{350,000}{450,000} \times 100 = \frac{35,000,000}{450,000} = \frac{3500}{45} = 77.8$

=77.8

ይህ ማለት ሴየቶች ቁጥር100 ሲሆን ወንዶቹ ደግሞ 78 ይሆናሉ፡፡

### 2.2.3. የህዝብ ሥርጭት

**የግምገማ ጥያቄ**

1. የሚትኖሩበት አከባቢ ህዝቦች በምን ሁኔታ ተሰራጭቶው ይገኛሉ? ለምን ይመስለኋል/ሻል?
2. ሰዎች በብዛት ተጠጋግተው የምኖረዉ በከተማ ወይንስ በገጠር ነው? ለምን?
3. የህዝብ ጥግግት ማለት ምን ማለት ነው?

**የህዝብ ጥግግት** ማለት በዓለም ላይ የህዝቦች አሰፋፈር ሁኔታ ማለት ነዉ፡፡ የአለም ለይ ህዝቦች በተመሳሳይ ሁኔታ ተሰራጭተው አይገኙም፡፡ ህዝቦች ከደቡባዊ ንፍቀ ክበብ በበለጠ በሰሜናዊው ንፍቀ ክበብ በብዛት ተሰራጭተው ይገኛሉ፡፡ ምክንያቱም አብዘኛው ደቡባዊው ንፍቀ ክበብ በውሃና በበረዶ የተሸፍነዉ ስለሚገኝ ነው፡፡ የህዝብ ሥርጭን በአህጉራት ደረጃ ስንመለከት በኢሲያ አህጉር 59.78%፣ በአፍርካ አህጉር 16.14%ና በአውሮፓ አህጉር 10.4% በመሆን በተከታታይ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃን ይዘዉ የሚገኙ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## የህዝብ ጥግግት

የህዝብ ጥግግት ማለት በአንድ በተወሰነ አከባቢ ሰፍሮ የሚገኝ የህዝብ ብዛት ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል በመሬት ገፅታ ላይ ሰዎች ምን ያህል ተጠጋግተዉ ወይም ተበታትነው መኖራቸውን የሚገልፅ ነው፡፡ የህዝብን ጥግግት ለማወቅ የህዝብ ብዛትና እነዚህ ህዝቦች ሰፍረው የሚገኙበት ቦታ ሥናነፃር የሚናገኘው ውጤት ነው፡፡

የህዝብ ጥግግት ለማወቅ የሚከተሉትን ፎርሙላ ተጠቀሙ

$$\text{የህዝብ ጥግግት} = \frac{\text{በአንድ አከባቢ ሰፍሬው የምገኝ ህዝብ}}{\text{ለመሬት ስፋት}}$$

ምሳሌ 1. በ40000ኪ.ሜ$^2$ ስፋት ባለው ሀገር ላይ 2000000 ህዝብ ይኖርበታል የሀገርቱ የህዝብ ጥግግት ስንት ይሆናል?

| የተሰጠ | የሚፈለግ |
|---|---|
| ስፋት = 40000 ኪ.ሜ$^2$ | የህዝብ ጥግግት? |
| የህዝብ ብዛት = 2,000,000 | |

$$\text{ሕሳባዊ ስሌት} = \frac{\text{የህዝብ ብዛት}}{\text{የመሬት ስፋት}} = \frac{2000000}{40000\text{ኪ.ሜ}2} = \frac{200}{4\text{ ኪ.ሜ}2} = \frac{50}{\text{ኪ.ሜ}2}$$

ይህ ማለት ከዚህ ሀገር 1 ኪ.ሜ$^2$ ስፋት ባለው መሬት ላይ 50 ሰዎች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ 2. በ2010 ዓ.ም የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት 79000000 ነበር፡፡ ጠቅላላ የመሬቷ ስፋት 1106000 ኪ.ሜ$^2$ ነው፡፡ በዚሁን አመት የኢትዮጵያ ህዝብ ጥግግት ምን ያህል ነው?

| የተሰጠ |
| --- |
| የሚፈለግ |

የመሬት ስፋት = 1,106,000 ኪ.ሜ$^2$ የህዝብ ጥግግት?

የህዝብ ብዛት = 79,000,000

| ሒሳባዊ ስሌት |
| --- |

$$የህዝብ\ ጥግግት = \frac{79000000\ ሰዎች}{1106000\ ኪ.ሜ2} = \frac{79000\ ሰዎች}{1106\ ኪ.ሜ2} = \frac{71.42}{ኪ.ሜ2} = \frac{71}{ኪ.ሜ2}$$

ይህ ማለት በግምት 71 ሰዎች በ1ኪ.ሜ$^2$ ስፋት ባለው መሬት ላይ ሰፍረው ይገኛል ማለት ነው፡፡

**በህዝብ ሥርጭት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች**

በየትኛውም የአለም ክፍል የህዝብ ጥግግትና ስርጭት በተመሳሳይ ሁኔታ ተሰራጭተው አይገኝም፡፡ በሰዎች ስርጭትና አሰፋፈር ለይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ሁለት ትላልቅ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነሱም ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

**ሀ. ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች**

የህዝብ ስርጭትን የሚወስኑ ተፈጥሮአዊ ምክያቶች የሚባሉት አየር ንብረት፣ ለም አፈር፣ ውሃ፣ የመሬት አቀማመጥ የዕፅዋት ሽፋን ናቸው፡፡

- **የአየር ንብረት**፡- ምቹ ያልሆነ የአየር ንብረት(ሙቀት፣ ዝናብ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ እርጥበትና ተስማሚ የሆነ አየር በሌለበት አከባቢ) ባለበት አከባቢ ሰዎች በብዛት አይኖሩም፡፡ ለምሳሌ፡- በበረሃማ አከባቢ ከፍተኛ ቅዝቃዜ ባለበት አከባቢ ሰዎች በብዛት አይኖሩም፡፡ ምክንያቱም በበረሃማ

አከባቢ ሰዎችን ለበሽታ የሚደርጉ ነፍሳቶች ስለሉ ሰዋች በብዛት አይኖሩም፡፡

- **የመሬት አቀማመጥ** ምቹ ያልሆነና ውጣውረዳ የበዛበት አከባቢ ላይ ሰዎች በብዛት ሰፍረው አይገኙም፡፡ ምክንያቱም ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በቀላሉ ስለማያገኙ ለመኖር አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰዎች በብዛት የማይኖሩባቸው አከባቢዎች በተራራማ፣ በገደላማና በረግረጋማ አከባባዎች ናቸው፡፡
- **የውሃ መገኘት፡** ውሃ ለሰው ልጆች በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ በቂና ንፁህ ውሃ ባለበት ቦታ ሰዎች በብዛት ለመኖር ይመርጣሉ፡፡
- **ለም አፈር፡** ለም አፈር ያለበት አከባቢ ለእርሻ ስራ ምቹ ነዉ፡፡ ለም አፈር በሌለበት አከባቢ ደግሞ ሰዎች ለኑሮ በቂ የሆነ ሰብልና ፅዕዋቶች ለማግኘት ስለሚቸገሩ ለመኖር አይመርጡም፡፡

**ለ. ሰው ሰራሽ ምክንያቶች**

ሰው ሰራሽ ሆነው የህዝብ ሥርጭትን ከሚወስኑ ምክንያቶች ውስጥ እርሻ፣ ማዕድን ማዉጣት፣ መጓጓዥና የመሳሰሉት ስሆኑ፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

የፋብሪካዎች መስፋፋት፣ የከተሞችና የቴክኖሎጂ ዕድገትን ይወስናል፡፡ በተጨማሪም አከባቢን መጠበቅ እና አለመጠበቅ ቀጣይነት ያለው የህዝብ አሰፋፈር ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያደርሳል፡፡ እንድሁም ማህበረሰቡ የተሰማራበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ዓይነቶች እንደ እርሻ፣ ከብት ማርባትና ንግድ የመሳሰሉት ተመሳሳይ የሆነ የህዝብ አሰፋፈር የላቸውም፡፡

### 2.2.4. ስደት

**የግምገማ ጥያቄ**

1. ስደት ምንድነው?

ስደት ማለት በቋሚነት ወይም ለግዛዊ ከሚኖሩበት አከባቢ ተነስተው ወደ ሌላ /አድስ/አከባቢ መስፈር ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስደት በፊት ከነበሩት ለቀው ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ለረጅም ጊዜ ወይም ከአንድ ዓመት በላይ ሌላ ቦታ መኖር ማለት ነው፡፡ በአጠቃላይ ህዝቦች ከነበሩበት ተነስተው ሌላ አድስ ቦታ መስፈር ማለት ነው፡፡ ሰዎች ከነበሩበት ቦታ ተነስተው ወደ ሌላ አድስ ቦታ የሚሰፍሩበት ምክንያቶች፡- ለትምህርት፣ ለሥራ፣ ለንግድ ተስማሚ የአየር ንብረት ለማግኘት፣ ምቹ ኑሮን ለመፈለግና በመሳሰሉት ምክንያቶች ልሆን ይችላል፡፡ ስደት በአንድ ሀገር ውስጥ ከገጠር ወደ ከተማ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከሆነ የሀገር ውስጥ ስደት ይባላል፡፡ የአንድን ሀገር ድንበር ተሻግረዉ የሚደረግ የሰዎች እንቅስቃሴ ደግሞ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር የሚደረግ ስደት ይባላል፡፡

### 2.2.5 የህዝብ አሰፋፈር

*የግምገማ ጥያቄ*

1. በአከባቢህ/ሽ ሰዎች እንዴት ሰፍረው ይገኛሉ?
2. የከተማና የገጠር የአሰፋፈር ልዩነት ግለፅ/ጪ?
3. በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝቦች በብዛት ተጠጋግተው የሚኖሩባቸው አከባቢዎች የት የት ናቸው? ሰዎች በጣም ተበታትነው የሚኖሩባቸው ቦታዎችስ? ለክፍል ተማሪዎች አብራራ/ሪ?

የህዝብ አሰፋፈር ማለት ህዝቦች በተወሰነ ቦታ ላይ ሰፍረው የሚኖሩበት ሁኔታ ማለት ነዉ፡፡ የአንድ ሀገር የህዝብ ሥርጭት የምወሰነው በአየር ንብረት በመሬት አቀማመጥና በዕፅዋቶች ሥርጭት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የህዝብ አሰፋፈር የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችና የሰዎችን የአኗኗር ሁኔታ ከማሳየት አልፎ መሠረተ ልማትንና ሥነ ህዝብ ፓሊስን ለማዘጋጀት ቀጥተኛ የሆነ አቅጣጫን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በአንድ አከባቢ የሚኖሩ የሰዎች ብዛትና የሥራ ሁኔታን መሠረት በማድረግ የህዝብ አሰፋፈርን በሁለት ትላልቅ ክፍሎች መክፈል ይቻላል፡፡ እነሱም የከተማና የገጠር አሰፋፈር ናቸው፡፡

**የከተማ ህዝብ፡-** በከተማ ከገጠር በተሻለ ሁኔታ መሠረተ ልማት ተስፋፍተዉ

ይገኛል፡፡ በከተማ በጠባብ መሬት ላይ ብዙ ህዝብ በጋራ ተሰባስበው ይኖሩበታል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ህገ-መንግስት መሠረት ከተማ የሚባለው ቢያንስ ከ2000ና ከዚያ በላይ ህዝብ የያዘ ከሆነ ነው፡፡

**የከተማ አሰፋፈርን የሚወስኑ ሁኔታዎች**

የከተማ አሰፋፈርን የሚወስኑ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡-


- ተፈጥሮአዊ የሰው ቁጥር መጨመር
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ስደት
- የፋብሪካዎች መስፋፋት
- የመሠረተ ልማቶች መስፋፋትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የገጠር ህዝቦች** ፡-የገጠር ህዝቦች ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በእርሻ ላይ የተመሠረተ

በሰፊ መሬት ላይ የሚኖር በቤተሰብ ደረጃ የሚማሩ ሞያ ያላቸው በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች በጣም የሚበዙ ናቸው፡፡

**የኢትዮጵያ ህዝብ**

የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በፍጥነት ከሚጨምሩባቸው የአፍርካ ሀገሮች መካከል ትመደባለች፡፡ ኢትዮጵያ ከአፍርካ ሀገሮች ከናይጄሪያ ቀጥላ በህዝብ ብዛት ሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያም እንደ አለም ሀገሮች ሁሉ የህዝቦች ሥርጭት ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ለምሳሌ በኢትዩጵያ ከፍተኛ ቦታዎች፣ ከደጋና ወይና ደጋ አከባቢ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ ጥግግት የሚገኝ ስሆን በዝቅተኛ ቦታዎች፣ በቆላና በበረሃማ አከባቢዎች ህዝቦች በጣም ተበታትነው ይገኛሉ፡፡




ካርታ. 2.1. የኢትዮጵያ ህዝብ ስርጭት (በሌላ ካርታ የቀየራል)

መልመጃ 2. 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ

1. ለህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. በህዝብ ብዛት ከ1ኛ-3ኛ የያዙ አህጉራት ሥም በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ
3. የህዝብ የዕድሜ ኙራሚድ ምንን ያሳያል? በስራ አሳይ/ዪ።
4. በ2013 ዓ.ም የ"ጠ" ሀገር ህዝብ ብዛት 120 ሚልዮን ነው። በዚህ አመት 20 ሚልዮን ህፃናት የተወለዱ ስሆን 500000 ህዝብ በድርቅ ምክንያት ከሀገር ተሰዷል። 450000 የሚሆኑ ህዝቦች ከተለያዩ ሀገሮች በስደት የገቡ ከሆነ ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች መነሻ በማድረግ ቀጥለው ያለዉ ጥያቀዎች ስራ/ሪ

ሀ. የውልደት መጠን    ሐ. ከሀገር የተሰደዱ

ለ. ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ    መ .የስደት ልዩነትን ሥራ/ሪ

5. የ"መ" ሀገር ህዝብ ብዛት 20 ሚልዮን ነው። ከሀገርቷ ህዝብ ብዛት 45% ወንዶች ከሆነ የፃታ ሬሾ ፈልግ/ጊ
6. 70 ሚልዮን ከሚሆኑት ከ"ረ" ሀገር ህዝብ ውስጥ 20000000 የሚሆኑት ልጆች 10000000 የሚሆኑት ደግሞ አረጋዊያን ከሆኑ የጥገኝነት ሬሾ ስንት ይሆናል?

ሀ. የህፃናት ሬሾ፣

ለ. የአረጋዊያን ሬሾ፣

ሐ. ጠቅላል የሀገሪቱ የጥገኛ ሬሾ ፈልግ።

7. የ"የ" ሀገር መሬት ስፋት 400000 ኪ.ሜ$^2$ ነው። የሀገርቷ ህዝብ ብዛት ደግሞ 80000000 ከሆኑ የሀገርቷ ህዝቦች ጥግግት ስንት ይሆናል?

## 2.3 የመጓጓዣ ዕድገት ፅንሰ ሀሳብ

የግምገማ ጥያቄዎች

1. መጓጓዣ ምንድን ነው?
2. የመጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸዉ?
3. በአከባቢ.ህ/ሺ. የሚኖሩ ህዝቦች ለማጓጓዣ የሚጠቀሙት ምን ምን ናቸዉ?
4. የመጓጓዣ እድገት ማለት ምን ምለት ነዉ?
5. ለመጓጓዣ እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?

መጓጓዣ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እድገትና መሰረተ ልማት መስፋፋት መሰረት ነዉ። መጓጓዣ ለአንድ ሀገር እድገት እንደ የደም ስር ይታያል። መጓጓዣ ሰዎችና የተለያዩ ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለማጓጓዝ ያገለግላል። መጓጓዣ የርቀት ችግሮችን በመፍታት የአለም ህዝብ በቀላሉ እንድገናኙ ያደርጋል ። ይህ ማለት ሰዎችና ዕቃዎችን ከነበሩበት ወደሚፈለግበት ቦታ በቀላሉ ስለሚያጓግ ነዉ። ዘመናዊ መጓጓዣ የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ነው። እድገቱም ከ18ኛው ክፍል ዘመን እንዱስትሪ አብዮት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት አለው። ከእንዱስትሪ አብዮት በኃላ ፈጣን የሆነ ዕድገትና ለውጥ በአለም ላይ አሳይቷል።

ሠንጠረዥ 2.3 የመጓጓዣ

| ተ.ቁ | ክፍለ ዘመን | የመጓጓዝ የዕድገትደረጃ |
|---|---|---|
| 1 | በ18 ክፍለ ዘመን | • የስዊዝ ቦይ መቆፈር |

| | | |
|---|---|---|
| | | • የመኪና መንገድ መሠራት |
| 2 | በ19ኛ ክፍለ ዘመን | • የባቡር ሃዲድ መሠራት<br>• በእንፋሎት የሚሰራ ጀልባ መጀመር |
| 3 | በ20ኛው ክፍለ ዘመን | • የሞተር መጓጓዣ መጀመር<br>• የአየር መጓጓዣ መስፋፋት |

## 2.3.1. መጓጓዣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ያለው ድርሻ

የግምገማ ጥያቄ

1. መጓጓዣ በኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ ያለውን ድርሻ ግለፅ/ጪ?
2. መጓጓዣ በሰዉ ልል ማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለዉ ጠቃሜታ ምንድነዉ?

መጓጓዣ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ አገልግሎት ከሚሰጡ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ከዝህ በላይ እንደተጠቀሰዉ ሰዎችና እቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ለማንቀሳቀስ ትልቅ ድርሻ አለዉ፡፡ ያለመጓጓዣ የሀገር ውስጥና ውጪ ንግድ ለማካሄድ ማሰብ አይቻልም፡፡ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን እንደጤና፣ ትምህርት፣ መንገድ፣ ውሃ፣ ማብራትና የመሳሰሉትን ለማስፋፋት መጓጓዣ ወሳኝ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ መጓጓዣ ከሚሰጣቸዉ ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- ጥሬ ዕቃዎችን ለአምራቾች ያቀርባል፤
- የፋብሪካ ውጤቶችን ከተመረቱበት ቦታ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል፤
- ድንገተኛና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት፤
- የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤
- ሠራተኞችን ከቤት ወደ ስራ ቦታና ከስራ ቦታ ወደ ቤት ለማመላለስ ይረዳል፤

- የሰዎች እርስ በርስ ግንኙነት እንድጠናከር ያደርጋል፡፡

### 2.3.2. የመጓጓዣ ዓይነቶች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. በአከባቢያችሁ አገልግሎት የሚሰጡ የመጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ምን ምን ናቸዉ ? ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች የሚባሉትስ ምን ምን ናቸዉ?

መጓጓዣን በተለያዩ መስፈርቶች መክፈል ይቻላል፡፡ በዘመናዊነታቸው ላይ በመመስራት ባህላዊ መጓጓዣና ዘመናዊ መጓጓዣ በመባል ይከፈላሉ፡፡ በሌላ በኩል በምጓዙበት ወይም በምቀሳቀሱበት መንገድ ላይ በመመስረት በሶስት ይከፈላል፡፡ እነሱም የየብስ፣ የውሀና የአየር መጓጓዣ ናቸው፡፡

**ባህላዊ መጓጓዣ,**

ባህላዊ መጓጓዣ ለዘመናዊ መጓጓዣ መሠረት ነው፡፡ ባህላዊ መጓጓዣ በጥንት ግዜ ጀምረዉ ሰዎች በተለያዩ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶችን ስጠቀሙ ቆይቷል፡፡ እነዝህ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች በሰዉና በተለያዩ እንስሳት ጉልበት የሚከናወን ነዉ፡፡ ባህላዊ መጓጓዣን ለሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ እነሱም የየብስና የውሃ ባህላዊ መጓጓዣዎች ናቸው፡፡ የየብስ ባህላዊ መጓጓዣ በሰው ጉልበትና የተለያዩ እንስሳትን በመጠቀም የሚከናወን ነዉ፡፡ እነዝህም እንስሳት በፈረስ፣ በበቅሎ፣ በግመል፣ በአህያ ዕቃዎችን ከቦታ ቦታ ማጓጓዝ ነው፡፡ ባህላዊ የውሃ ላይ መጓጓዣ ደግሞ በአከባቢው ከሚገኙ ነገሮች/ከእንጨት ተሠርተው አገልግሎት የሚሰጡ ስሆኑ ከእንጨት የተሠሩ ገበቴ መሰል ዕቃዎች፣ ከቄጠማ፣ ከቃጫና ከግንድ የተሠሩ እንድሁም ጀልባ ሌሎች ናቸው፡፡



ሥዕል 2.5 ባህላዊ መጓጓዣ

## ዘመናዊ መጓጓዣ

ዘመናዊ መጓጓዣዎች በሚሰጡት ጥቅም ላይ ተመስርተው በሶስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም የየብስ፣ የውሃና የአየር መጓጓዣዎች ናቸው፡፡




ሥዕል 2.6 ዘመናዊ መጓጓዞዎች

### 1. የየብስ መጓጓዣ

የየብስ መጓጓዣ ማለት መንገደኞችንና ዕቃዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመሬት ገፅታ ላይ ማንቀሳቀስ ማለት ነው፡፡ ይህ እንቅስቃሴ የምደረገውም በመኪና መንገድ ላይ፣ በባቡር ሂድድና በቱቦ አማካይነት ነው፡፡

### 2. የውሃ መጓጓዣ

ይህም ከመጓጓዝ ዓይነት አንዱ ሆኖ በባህሮች፣ በወንዞችና በውቅያኖሶች ላይ ሰዎችንና ዕቃን በመርከብና በጀልባ ማጓጓዝ ማለት ነው፡፡ የውሃ

መጓጓዣ መንገደኞችንና ዕቃዎችን አገር ውስጥና ወደ ውጭ አገር ለመጓጓዝ ይረዳል፡፡ የውሃ መጓጓዣ ብዙ ዕቃዎችን በማጓጓዝ የሚታወቅ የመጓጓዣ አይነት ነው፡፡

### 3. የአየር መጓጓዣ

የአየር መጓጓዣ ካሉት መጓጓዣዎች ውስጥ በጣም ፈጣን የሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም በአስቸጋሪ መልከአ ምድር አንደተራራዎች፣ ሸለቆዎች፣ ኮረብታዎች፣ ውሃማ አካላት እና የመሳሰሉት ላይ ሰዎችንና ዕቃን ለማጓጓዝ ምቹ ነዉ፡፡ እንድሁም ቶሎ የሚበላሹ ዕቃዎችን በፍጥነት ረጅም ርቀት ለማድረስ ተመራጭ ነዉ፡፡

## 2.3.3. የመንገድ ደህንነት፣ የትራፍክ አደጋዎችና በማህበራዊና ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣው ጉዳት

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. የመንገድ ደህንነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የመንገድ ደህንነት ለመጠበቅ ተጠያቅነት ያለው አካል ማን ነው?
3. መንገድን ስታቋርጥ የሚታደርገው ጥንቃቄ ምንድነው?
4. የትራፍክ ህግን ተከትሎ መጓዝ ከምን ዓይነት አደጋዎች ያድናል?

የመንገድ ደህንነት በአሽከርካርዎች፣በመኪ፣ በሰዎች፣ በመሠረተ ልማትና በመሰሰሉት ላይ ከፍተኛ ችግር ያደርሳል፡፡ የመንገድ ደህንነት መጠበቅ በሰዎችና በንብረት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመቀነስ ያስችላል፡፡ ይህን የመንገድ ደህንነት አሽከርካሪዎችና ማንኛውም ግለሰቦች ልተገብሩ የሚገባ ነው፡፡ የመንገድ ደህንነት ከመንገድ አሰራር፣ የመንገድ ሁኔታ፣ የመኪናዎች ብዛትና የሚታገበሩ የትራፊክ ህጐችን ያጠቃልላል፡፡ የመንገድ ደህንነት እንደ የመንገድ መተዳደሪያ ህግና ደንብ፣ የመንገድ ደህንነት ስርአትና ቁጥጥር፣ አሽካርካሪዎችን ማብቃት፣ ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ ማስተማር፣ ለህብረተሰብ በቂ ግንዛቤ መፍጠር ፣ የመንገድ ደህንነት የምገልፁ ምልክቶች በመንገድ ዳር ማቆም፣ የመኪናዎችን ሞተር

ጤንነት በየጊዜው መፈተሽና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ የመንገድ ደህንነትን መጠበቅ ሁለም ካሰበበት ከባድ ሥራ አይደለም፡፡

### የትራፍክ አደጋ


የትራፍክ አደጋ ማለት በመጓጓዣ ምክንያት በመንገድ ላይ የሚደርሱ የተለያዩ አደጋዎች ማለት ነው፡፡ በመኪና መንገድ ላይ አደጋ ልያደርሱ የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውሰጥ ጥቂቶቹ ምቹ የሆኑ ትላልቅ መንገድ አለመኖር፣ ጠጥቶ ማሽከርከር፣ ለረዥም ሰዓት ያለ ዕረፍት ማሽከርከር፣ ስልክ እያናገሩ ማሽከርከር፣ በፍጥነት ማሽከርከር፣ ከተፈቀደለት መንገድ ውጪ ማሽከርከር፣ ወደልተፈቀደ መስመር ለማለፍ መሞከር፣ ፍሬቻ ሳያሳዩ ለማዞር መሞከርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ሥዕል 2.7 የትራፍክ አደጋና የሚደርሰው ጉዳት

### የትራፍክ መብራት

የትራፊክ መብራት በቀይ ብጫና አሬንጓዴ ቀለማት የተዘጋጀ ሆኖ መንገድ ዳር ቆሞ የትራፍክ ፓሊስን በመተካት በኤሌትሪክ የሚሠራ የትፍክ ህግን የሚያስጠብቅ ነው፡፡



- ቀይ መብራት በሚበራበት ሠዓት መኪና በለበት ይቆማል
- ብጫ መብራት በሚበራበት ሰዓት መኪናዎች እንቅስቅሴ ለመጀመር ይዘጋጃሉ
- አሬንጓዴ መብራት በሚበራበት ሰዓት ደግሞ የቆሙ መኪናዎች ይንቀሳቀሳሉ፡፡



ሥዕል 2.8 ሰዎች መንገድን የሚያቋርጡበት ቦታ

ሠንጠረዥ 2.3 የመንገድ የትራፍክ ምልክት

| ተ. ቁ | ምልክቶቹ የሚያስተላልፉት መመሪያ | የምልክቶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሚያስጠነቅቁ |  |  |  |  |  |
| 2 | የሚከለክሉ |  |  |  |  |  |
| 3 | የሚያስገድዱ |  |  |  |  | |
| 4 | ቅድሚያ የሚያሰጡ |  |  |  |  |  |
| 5 | መረጃ የሚሰጡ |  |  |  |  |  |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 6 | አቅጣጫ የሚያሳዩ |  |  |  |

**መንገድን ለማቋረጥ  ልወሰድ የሚገቡ ጥንቃቄዎች**

- መኪና ከሚጓዝበት መንገድ ርቆ መቆም
- ለመኪና በተፈቀደበት ጊዜ ቆሞ ማሳለፍ
- ግራና ቀኝን ማየትና ማዳመጥ
- ለሰዎች በተፈቀደ ቦታ ብቻ ማቋረጥ
- ለሰዎች በተፈቀደ ጊዜ  ቀስ ብሎ ማለፍ

በአጠቃላይ የመጓጓዣ አገልግሎት በአለም ላይ በምጣኔ ሀብት ፣ ፖለቲካና ማህበራዊ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ዛሬ ላይ ያለውን የመጓጓዣ ዕድገት ደረጃ ሰዎች እንደፍላጐታቸው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንቀስቀስ የሚያስችል ሁኔታን ፈጥሮአል፡፡ ስለዚህ ለትራፊክ ደንቦች መገዛት ከሁሉም ዜጋ የሚጠበቅ ነው፡፡

**ትግበራ ጥያቄዎች**

1. እናንተ በሚትኖሩበት አከባቢ የመኪና መንገድ ካለ በመንገድ ዳር የቆሙና መረጃ የሚሰጡ የትራፊክ ምልቶችን በቡድን ሆናችሁ 5 ምልክቶችን ሥዕል እንሱ፤ ለምን አገልግሎት እንደምውሉ ጻፍ? በመቀጠልም  ስለ ምልክቶቹ የሚያወቁ ሰዎች ወይም የትራፊክ ፓሊስ ጋር በመሄድ ምልክቶቹ ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ጠይቁ፡፡ ያገኛችሁትን መልስ ደግሞ ለክፍል ተማሪዎች አብራራ/ሪ?
2. በሠንጠረዥ 2.4. ለይ የተቀመጡት ምልክቶች እያንዳንዳቸው ምን አይነት መረጃ እንደምያስተላልፉ መብራራያ ስጥ/ጪ?

## መልመጃ2.3

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. መጓጓዣ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ዘመናዊ መጓጓዣዎች ስንት ናቸው? ስማቸውን ፃፍ/ፊ?
3. የትራፊክ ህግን ጠብቆ መጓዝ ከምን አይነት አደጋዎች ያድናል?
4. ስድስቱን የትራፊክ ምልክቶች ምንድናቸው ?ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጥ/ጪ?

መንገድ ለማቋረጥ የሚንተገብራቸውን ጥንያቄዎች ዘርዝር/ሪ።

### የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የሰው ልጅ አመጣጥ ላይ ሁለት መላ ምቶች አሉ። እነሱም ሳይንሳዊና ሃይማኖታዊ መላምት ናቸው።
- ኢትዮጵያና ሌሎች የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ አላቸው።
- አርክኦሎጅ ሳይንስ ሆኖ ስለ ጥንታዊ የሰው ልጅ አመጣጥ ከቅሪታ አካል የሚያጠና ነው።
- አውስትራሎኘትከስ በረዥም ጊዜ ዝግመታዊ ለውጥ ከጅናስ ዘር ወደ ሆሞ ሀብልስ፣ ሆሞ እሬክተስና ሆሞ ሳፒያንስ እያደገ የመጣ ነው።
- በአለም ላይ የሰው ልጅ ሥርጭት ወይም አሰፋፈር አይመሳሳልም። የመለያየቱ ምክንያት የአየር ንብረት፣ የምግብ አቅርቦት፣ በሽታና ጦርነት በዋናነት ይጠቀሳሉ።
- የህዝብ ቁጥርን የሚቀይሩ ሁኔታዎች ውልደት፣ ሞትና ስደት ናቸው።
- የአንድ ሀገር ህዝብ በምጣኔ ሀብትና በማህበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ልጆች፣ ጉልማሶችና አረጋዊያን ተብለው በሶስት ይከፈላሉ።

- የህዝብ ጥግግት ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚኖር የህዝብ ብዛት ማለት ነው፡፡
- መጓጓዣ ማለት ሰዎች ወይም ዕቃዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መጓጓዝ ማለት ነው፡፡ የመጓጓዣ አይነቶች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ባህላዊና ዘመናዊ የመጓጓዣ አይነቶች ናቸው፡፡
- የትራፊክ ደህንነት ማለት ማንኛውም ግለሰብ በመንገድ ስገለገል ልከተለዉ የሚገባ የትራፊክ ህግ ነው፡፡
- የትራፍክ አደጋ ማለት በሰዎችና በንብረት ላይ በማጓጓዣ ምክንያት የሚደርስ አደጋ ማለት ነው፡፡
- የትራፊክ ህጐች ማለት ግለሰቦችና አሽከርካሪዎች መንገድ ስጠቀሙ ልተገብሩ የሚገባቸው የትራፊክ ደንቦች ናቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

**ክፍል I. የሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክል የሆነዉ እዉነት ትክክል ያልሆነዉን ሐሰት በማለት ፃፍ/ፊ**

1. ሁሉም ሀይማኖቶች ሰዉን የፈጠረው እግዚአብሔር ወይም ፈጣሪ ነው ብለዉ ያምናሉ፡፡
2. የሰው ልጅ አመጣጥ በዝግመታዊ ለውጥ ከሆሞወደ አውስትራሎፕትከስ እየተቀየረ የመጣ ነው፡፡
3. ስደት የአለምን ህዝብ ቁጥር ይቀይራል፡፡
4. ባህላዊ መጓጓዣ የየብስ እንጅ የውሃና የአየር መጓጓዣዎች የለዉም፡፡
5. የትራፍክ ደህንነትን ማስጠበቅ የትራፍክ ፓሊስ ድርሻ ብቻ ነው

**ክፍል II. በ ለ ሥር የተዘረዘሩት በ ሀ ሥር ካሉት ጋር አዛምድ/ጂ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 6. ባህላዊ መጓጓዣ | ሀ. በህይወትና በንብረት ላይ |

ጉዳት ያደርሳል

7. ዘመናዊ መጓጓዣ ለ. በመንገድ ዳር የሚቆም

8. የትራፍክ ህግ ሐ. አውሮፕላን

9. የትራፍክ ምልክቶች መ. በቅሎ

10. የመኪና አደጋ ሠ. ግራና ቀኙን አይቶ መንገድ ማቋረጥ

**ክፍል III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ በመምረጥ ጻፍ/ፊ**

11. የሰዉ ልጅ መገኛ ነዉ ተብሎ ይገመታል

ሀ. የአፍርካ ቀንድ ሐ. አሜሪካ

ለ. አዉሮፓ መ. አውስትራሊያ

12. በመጀመሪያ ጊዜ በሁለት እግሩ ቆሞ መሄድ የጀመረው የሰው ዘር የቱ ነው?

ሀ. ሆሞ ሀብሊስ ሐ. ሆሞ ሳፒያንስ

ለ. ሆሞ ኤሬክተስ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

13. ከሚከተሉት ውስጥ የህዝብ ቁጥር የሚቀንስ ተፈጥሮአዊ ክስተት የቱ ነው?

ሀ. ውልደት ሐ. የሰዎች ዝውውር

ለ. ስደት መ. ሞት

14. ከሚከተሉት ውስጥ የትራፍክ አደጋ ምክንያት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ምቹ ያልሆነ የመኪና መንገድ መኖር

ለ. የትራፍክ ህግን የሚያሳዩ የትራፍክ ምልክቶችን ማቆም

ሐ. ከፍጥነት በላይ ማሽከርከር

መ. የማብራት ምልክት ሳያሳይ መኪናን ማዞር።

15. ከሚከተሉት የትራፍክ ምልቶች ተሽከሪካሪዎች ለማቆም የሚያገለግል የቱ ነው?

ሀ.  ለ.  ሐ.  መ.  ሠ.  ረ. 

ክፍል IV ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዶ ቦታዉን በመሙላት መልስ/ሽ

16. ለመጀመሪያ ጊዜ በእጅ መስራት የጀመራው ጥንታዊ የሰው ዘር-- ይባላል፡፡

17. ሰዎችንና ዕቃን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ማንቀሳቀስ ------------ ይባላል

ክፍል 5 ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ

18. የትራፍክ አደጋን ልያስከትሉ ከሚችሉት ምክንያቶች ውስጥ ሶስት ፃፍ/ፊ

19. መንገድን ስናቋርጥ ልናደርጋቸው የሚገቡ ጥንቃቀዎችን ዘርዝር/ሪ

ክፍል VI የሚከተሉትን ጥያቄዎች በስራ አሳይ/ዩ

20. የጃፓን ሀገር ህዝብ ብዛት 50 ሚሊዮን ብሆንና ከእነዚህ ውስጥ 65 % ጉልማሶችና 5% አረጋዊያን ናቸው፡፡ ጠቅላላ የሀገርቷ የቆዳ ስፋት ደግሞ 10 ሚሊዮን ኪ.ሜ$^2$ ነው፡፡ እነዚህን መረጃዎች መሠረት በማድረግ

ሀ. የሀገርቱ የአምራች ኃይል ስንት ይሆናል?

ለ. የሀገሪቱ የጥገኝነት ሬሾ ስንት ይሆናል

ሐ. የሀገሪቱ የህዝብ ጥግግት ስንት ነው?

# ምዕራፍ 3

# ሰውና የተፈጥሮ ሀብት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡

- በሰውና በተፈጥሮ ሃብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ትገልፃለህ/ሽ
- ተፈጥሮ ሃብቶችን በመገኛቸው መጠንና በጠቀሜታቸው መክፈል ትችላለህ/ሽ
- በተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱትን ነገሮች ትዘረዝራለህ/ሽ
- በሰውና በተፈጥሮ ሃብቶች መካከል ያለውን ግንኙነት፤ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች ህዝብ ምን እንደ ሆኑ ትገልፃለህ/ሽ

### መግቢያ

ባለፉት ምዕራፎች ውስጥ ስለ ሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ፣ የህዝብ ቁጥር መቀየር፤ የህዝብ አሰፋፈር፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ስርጭትን መማራችሁ ይታወቃል፡፡

በዚህ ምፅራፍ ውስጥ ደግሞ ስለ ሰው ልጅና አከባቢያዊ ግንኙነት፣ ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና አነስተኛ የሆነ የህዝብ አሰፋፈር የሚሉ ፅንሰ ሃሳቦች ይቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ

በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አማካይነት የሚመጡ ተፅዕኖዎች እንደ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ የከተሞች መስፋፋትና የህዝብ አሰፋፈርን ትማራላችሁ፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ልደርሱበት የሚገቡ የመማር ብቃቶች**

- በተፈጥሮ ሀብትና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችና የሚሰጡትን ጠቀሜታ ትለያለህ/ሽ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት ልያደርሱ የሚችሉ ነገሮችን ትዘረዝራለህ/ሽ፡፡
- በተፈጥሮ ሀብትና ሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት /ከአቅም በላይ የሆነ የህዝብ አሰፋፊር ተመጣጣኝ የህዝብ አሰፋፈርና አነስተኛ የህዝብ አሰፋፈር/ ምን እንደሆኑ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የሚታደሱና የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለውን ልዩነት ትገልፃለህ/ሽ፡፡

## 3.1 በሰዉና ተፈጥሮ አከባቢ መካከል ያለው ግንኙነት

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. በሰው ልጅና በአከባቢያቸው ያለውን ልዩነት ግለፅ/ጪ
2. በሰዎችና አከባቢ ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
3. የሰው ልጅ በተፈጥሮ የተገኘ ነገሮችን ሁሉንም ይጠቀምበታል? የማይጠቀምበት ከሆነ እንቅፋት የሆነበት ምንድነው?
4. ከአቅም በላይና ከአቅም በታች ህዝብ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

የሰው ልጅና አከባቢ የማያቋርጥ ግንኙነት አላቸው፡፡ ይኸውም የሰው ልጅ ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ሁሉ የሚያገኘው ከአከባቢ ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ አከባቢው ውጭ መኖር አይችልም፡፡ ይሁን

እንጂ በተፈጥሮ የተገኙትን ነገሮች ሁሉ እየተጠቀመቀ አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያት የሚሆኑት የሳይንስና ቴቅኖሎጅ፣ የዕውቀት እና የገንዘብ እጥረት ናቸው፡፡ በተፈጥሮ ከተገኙት እስካሁን ሰዎች ያልደረሱበት የተፈጥሮ ሀብቶች ብዙ አሉ፡፡ ይህ ማለት ሳይንስና ቴክኖሎጂ እያደገ ሲሄድ እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶችን ጥቅም ላይ ያውላል ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ በበረሃማ አከባቢ የሚገኘውን አፈር እስከ አሁን በውሃ እጥረት ምክንያት ለእርሻ ሥራ ያልዋለውን ከጊዜ በኃላ በዘመናዊ መስኖ በመጠቀም ተፈጥሮን ወደ ጥቅም እየቀየረ ነው፡፡

በተገቢው ሁኔታ ያለመጠቀም የተፈጥሮ ሃብቶችን ለብክነት ይዳርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ አፍሪካ ውስጥ ከሰሐራ በታች ያሉ አገሮች ላይ ይታያል፡፡ በመሆኑም የተፈጥሮ ሃብቶችን በተገቢ ሁኔታ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም በተመለከተ በሰውና ተፈጥሮ ሃብቶች መካከል ያለው ግንኙነት፤ ከአቅም በላይ፤ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች አሰፋፈር በማለት መግለፅ ይቻላል፡፡

**ከአቅም በላይ የሆነ የህዝብ አሰፋፈር**

ከአቅም በላይ የሆነ የህዝብ አሰፋፈር ማለት የአንድ ሀገር የህዝብ ብዛት ከሀገሪቷ የተፈጥሮ ሀብት መጠን በላይ ሲሆን ማለት ነው፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ህዝብ ያላቸው ሀገሮች የተፈጥሮ ሀብቱ ከሰው ቁጥር በታች ስለሆነ መጠኑ ቀስ በቀስ እየተመናመነ ይሄዳል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ህዝብ ያላቸው ሀገሮች ለብዙ አይነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ናቸው፡፡ ከነዚህም ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ከፍተኛ የሆነ ድህነት ፣ሥራ አጥነት፣ የመሠረተ ልማት ችግርና የፖለቲካ አለመረጋጋት ናቸው፡፡

**የተመጣጠነ የህዝብ ቁጥር**

የተመጣጠነ የህዝብ ቁጥር ማለት የአንድ ሀገር የህዝብ ብዛትና በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኘው የተፈጥሮ ሀብት መጠን ተመጣጣኝ ሲሆኑ ነው፡፡ እነዝህ ሀገሮች ውስጥ ሰዎች የተሸለ ህይወት ይኖራሉ፡፡ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊኖር ይችላል፡፡ መሰረተ ልማትም ሊስፋፉ ይችላል፡፡

**ከአቅም በታች የሆነ የህዝብ ቁጥር**

ከአቅም በታች የሆነ የህዝብ ቁጥር ማለት ሀገሯ ያላት የህዝብ ቁጥር ከተፈጥሮ ሀብት መጠን በታች ሆነዉ ሲገኝ ነው፡፡ በተወሰኑ የአለም ሀገሮች ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት መጠን ከህዝብ በላይ በልጠው ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ሀገሮች ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ ጥቅም ላይ አይውልም፡፡

## 3.2 የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች

### የተግበር ጥያቄ

1. ራሳቸዉን የሚያድሱና ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉ ልዩነት ምንድን ነዉ?
2. ራሳቸዉን የሚያድሱና ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶችን ዘርዝር/ሪ?

የተፈጥሮ ሀብት ማለት በተፈጥሮ ያሉና ለሰው ልጅ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡ እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ራሳቸውን የሚያድሱና ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡

### 3 . 2 .1 ራሳቸውን የሚያድሱ የተፈጥሮ ሀብቶች

ራሳቸውን የሚያድሱ የተፈጥሮ ሀብቶች በተፈጥሮ ራሳቸው መተካት የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ውሃ የፀሐይ ብርሃን፣ ደን፣ አየር፣ አፈርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ፍላጐቱን ለሟሟላት የተለያዩ የተፈጥሮ

ሀብቶችን ይጠቀማል፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ካልተጠቀሙበት ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል፡፡

### 3. 2 . 2 ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብቶች

ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብት ማለት አንድ ጊዜ ተጠቅመን ካለቁ በኃላ መልሰን ልናገኛቸው የማንችል የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ ብረት ማዕድን፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ነዳጅ ዘይትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3.3 ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች

#### የግምገማ ጥያቄዎች

1. በተፈጥሮ ሀብት ላይ ተፅዕኖዎችን የሚደርሱ የተፈጥሮ ክስተቶች ምንድናቸው?
2. በሰው ሰራሽ ምክንያት በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎች ምንድናቸው?

በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተፅዕኖ በሁለት መንገድ ሊደርስ ይችላል፡፡ እነሱም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንቶች ናቸው፡፡ በተፈጥሮ የሚመጡ ተፅዕኖዎች የእሳተ-ገሞራ ፍንዳታ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና ሰደድ እሳት ናቸው፡፡

በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊደርስ የሚችለው በሰዎች ተፅዕኖ አማካይነት ነው፡፡ ከእነዚህም የተወሰኑት፤

#### የህዝብ ብዛት መጨመር

የሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሄድ ለተፈጥሮ ሀብቶች ብክነት ከፍተኛ ምክንያት ነው፡፡ በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የህዝብ ቁጥር አሳሳቢ ሁኔታ እየጨመረ ከመሆኑ የተነሳ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት እየደረሰ ነው፡፡

### የእርሻ መሬት ማስፋፋት

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣው የህዝብ ቁጥር በግጦሽ መሬት፣ በደኖችና በፓርኮች የተሸፈኑ ቦታዎችን በመመንጠር ወደ እርሻ መሬት እየተቀየረ ነው። ይህ ድርጊት በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ከፍተኛ ጉዳት በተፈጥሮ ሀብት ላይ ያደርሳል።

### የከተሞች መስፋፋት

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተሞች በጣም እየተስፋፉ መሆናቸው ይታወቃል። በዚህ የተነሳ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት እየጨመረ በመምጣቱ በህገ-ወጥ መንገድ የከተሞች መስፋፋት ይከሰታል።

**መልመጃዎች**

1. ራሳቸውን የሚያድሱና ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብት በመለየት ዘርዝር/ሪ።
2. አለግባብ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የሚኖር ከሆነ በሰው ለጅና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ያለው ግንኙነት ተቃራኒ ይሆናል። ይህ ሀሳብ ምንን ለመግለፅ ታስቦ ነው?
3. በሰውና በተፈጥሮ ሀብቶች መካከል ያለው ግንኙነትን በተመለከተ፤ ከአቅም በላይ፣ ተመጣጣኝና ከአቅም በታች የሚሉትን ነጥቦች ግለፅ/ጪ
4. በአገራችን ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ነገሮች ምንድናቸው? ዘርዝር/ሪ።

**የተማሪው/ዋ ተግባር**

1. በትምህርት ቤትህ/ሽን አካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን ከጎበኘህ/ሽ በኋላ ራሳቸውን የሚያድሱና ራሳቸውን የማያድሱ የተፈጥሮ ሀብት ለይተህ/ሽ ዘርዝር/ሪ።
2. የትምህርት ቤትህ/ሽን አካባቢን ቀላል ካርታ በማዘጋጀት በተፈጥሮ ሀብት ዓይነትን አመቺ በሆኑ ምልክቶች አሳይ/ዪ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የሰዉ ልጅና የተፈጥሮ ሀብት የማይለያይ ግንኙነት አላቸዉ:: ስለዚህ የተፈጥሮ ሀብት እንዳይባክን በጥንቃቄ መጠቀም አስፈላግ ነዉ::
- የተፈጥሮ ሀብትን በጥንቃቄ የማንጠቀምበት ከሆነ ከፍተኛ ብክነት ይደርስበታል::
- ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመሬ ያለዉ የህዝብ ቁጥር መሰረታዊ ፍላጎቶቹም እየጨመረ ይሄዳል:: በጥንቃቄ ጉድለት የሰዉ ልጅ የራሱን ፍላጎት ለማሟት በተፈጥሮ ሀብት የሚጠቀም ከሆነ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል:: ለምሳሌ፣ የእረሻ መሬትን ለመስፋፋት ሲባል ደኖችና ፓርኮች ይመነጥራሉ:: ይህ በመሆኑ በተፈጥሮ ሀብትና በሰዎች መካከል ያለዉ ግንኙነት ማመጣጠን ያስፈልጋል::

### የምዕራፉ ማጠቃለያ መልመጃ

**ክፍል Ị. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ::**

1. ከሚከተሉት የተፈጥሮ ሀብቶች ዉስጥ ራሳቸውን የሚያድሰው የትኛው ነው?

   ሀ/ ዉሃ ለ/ የተፈጥሮ ጋዝ ሐ/ እንቁ መ/ ነሐስ

2. ከሚከተሉት ዉስጥ የተፈጥሮ ሀብት ያልሆነዉ የቱ ነዉ?

   ሀ/ አፈር ለ/ ደን ሐ/ ማዕድን መ/ መልስ የለም::

3. ከሚከተሉት ዉስጥ በሰዎችና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ባለዉ ግንኙነት አማካይነት ችግር የማይኖረው በየቱ ነዉ?

ሀ/ አነስተኛ የሆነ የህዝብ ብዛት
ለ/ ከተፈጥሮ ሀብት በላይ የሆነ የህዝብ ብዛት
ሐ/ የህዝብና የተፈጥሮ ሀብት መመጣጠን
መ/ መልስ የለም

## ክፍል 2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ፡፡

1. የተፈጥሮ ሀብት ዓይነቶች ምን ምን ናቸዉ?
2. በሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያለዉን ግንኙነት ግለፅ/ጪ፡፡
3. በተፈጥሮ አጠቃቀም ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉት ነገሮች ዘርዝር/ሪ?
4. ከአቅም በላይ የህዝብ ብዛት ማለት ምን ማለት ነዉ?

## ክፍል 3. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎችን ሙላ/ይ

1. በኢትዮጵያ ዉስጥ በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደረሱ ነገሮች___________, _______________ እና _______________ናቸዉ፡፡
2. ተጠቅመንበቸው ከለቁ በኋላ ተመልሰዉ የማናገኛቸዉ የተፈጥሮ ሀብቶች__________ይባላሉ፡፡

# ምዕራፍ 4

## ቀደምት የአለም ስልጣኔ ከጥንት እስከ መካከለኛው ክፍለ ዘመን

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች፡**

- በካርታ ላይ በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ስልጣኔዎች ታሳያለህ/ሽ
- ቀደምት የአለም ስልጣኔንና የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ስልጣኔን ታመዛዝናለህ/ሽ
- የቀደምት አለም ስልጣኔ ውጤቶችን ታብራራለህ/ሽ
- የክርስትና ሀይማኖት አመጣጥና መስፋፋትን ትገመግማለህ/ሽ
- የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋፋትን ትገመግማለህ/ሽ
- የባዛንታየን ኢምፓየር ባህሪያትን ትገልፃለህ/ሽ፡፡

## መግቢያ

በአከባቢ ሳይንስ ትምህርት ውስጥ ስለ ማህበራዊ ኑሮ፣የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ ግብርና እና ንግድ በክልል እና በኢትዮጵያ ያለበትን ደረጃ ተምረሀል/ሻል፡፡በተጨማሪም በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ታሪካዊ የቅርሶች ማዕከላትን ለይተሀል/ሻል፡፡በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ቀደምት የአለም ወንዞች ዳርቻ ስልጣኔዎች እንዴት እንደ ተጀመሩ ትማራለህ/ሽ፡፡ለምሳሌ የጥንት ሜሶፖታሚያ፣ የህንድ ስልጣኔ፣ የቻይና እና የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔዎችን በስፋት ትማራለህ/ሽ፡፡እንዲሁም ስለ

ክርስትናና እስልምና ሀይማኖቶች አመጣጥ እና መስፋትን ትማራለህ/ሽ፡፡ በመጨረሻም ስለ ባዛንታየን ኢምፓየር ባህሪያትን ትማራለህ/ሽ፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- በወንዞች ዳርቻ የተመሰረቱትን ስልጣኔዎች ትዘረዝራለህ/ሽ
- ቀደምት የአለም ልጣኔዎች እና የመካከለኛውን ክፍለ ዘመን የአለም ስልጣኔዎችን ታመዛዝናለህ/ሽ
- ቀደምት የአለም ስልጣኔና የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ስልጣኔ ውጤቶችን ታብራራለህ/ሽ
- የክርስትናና የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እና መስፋትን ታብራራለህ/ሽ
- የባዛንታየን ኢምፓየር ታሪክ እና ባህሪያትን ታብራራለህ/ሽ፡፡

## 4.1.ጥንታዊ የአለም ስልጣኔ

### 4.1.1.የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የወንዞች ዳርቻዎች ለቀደምት የአለም ስልጣኔዎች ምቹ ያደረጋቸው ምንድነው?
2. የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ የተጀመረበትን አህጉር ታውቃለህ/ሽ?
3. ስለ ሀሞራቢ ህጎች የምታውቀውን/ውን ለክፍል ጓደኞችህ አብራራ/ሪ

የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ ከአለም ስልጣኔዎች ሁሉ ቀደምት ነው፡፡ በግሪክ ቋንቋ ሜሶፖታሚያ ማለት "በሁለት ወንዞች መካከል የሚገኝ መሬት" ማለት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ የተጀመረው በቲግሪስ እና ኢፍራጤስ ወንዞች መካከል በ3500 ዓ.ዓ አከባቢ ነው፡፡




ካርታ.4.1.1.የጥንት ሜሶፖታሚያ መገኛ


በቲግሪስና ኢፍራጤስ ወንዞች ዳርቻ አከባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰፈሩና የሜሶፖታሚያን ስልጣኔም የመሰረቱት ህዝቦች ሱሜሪያኖች ይባላሉ፡፡በቀደምት ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ ሱሜሪያኖች ጠንካራ ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ አደረጃጀት ነበራቸው፡፡ እንዲሁም ነገስታቶቻቸው ፍጹማዊ ስልጣንን በመጠቀም ሜሶፖታሚያን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡ ከሜሶፖታሚያ ነገስታት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ህግ በማውጣትና ህብረተሰቡ እንዲገለገሉበት ያደረገው ሀሙራቢ (1792-1750 ዓ.ዓ) ይባላል፡፡ የሀሙራቢ ህጎች ጭካኔ የተሞላባቸውና ከባድ ህጎች ከመሆናቸው የተነሳ በተፈፀመ ወንጀል ልክ ተመሳሳይ ቅጣቶች የሚሰጡ ህጎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌም “ዓይን ያጠፋ ሰው ዓይኑ በመጥፋት ይቀጣ” የሚል ነበረዉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሀሙራቢ ህጎች ህብረተሰቡ ተከባብሮ እንዲኖሩና ወንጃል እንዳይሰፋፋ እነዲሁም ሰላምና መረጋጋት በህዝቦች መካከል እንዲረጋገጥ ትልቅ አስተወጽኦ አድርጎ ነበር፡፡

በቲግሪስ እና ኢፍራጤስ ወንዞች አከባቢ ያሉት ውሃ እና ለም አፈር ለግብርና ምቹ በመሆናቸው ለሜሶፖታሚያ ስልጣኔ መመስረት ምክንያት ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ሱሜሪያኖች ወንዞችን በመገደብ እና በመስኖ እርሻ ስራ ይታወቁ ነበር፡፡ ቀደምት ሜሶፖታሚያኖች በየብስና በውሃ ላይ ከተለያዩ አከባቢ ህዝቦች ጋር ንግድ በማካሄድም ይታወቃሉ፡፡ እንዲሁም በንፋስ ሀይል የሚሰራ ጀልባዎችንና በሰውና በእንስሳት ጉልበት የሚሰሩ ሰረገላዎችን በመስራት ለመጓጓዣነት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ የተለያዩ ብረታ ብረቶችን በመጠቀም የተለያዩ መሣሪያዎችን በመስራት ለአለም አበርክቷል፡፡

ግብርና ለሁሉም ስልጣኔዎች መሰረት ነው፡፡ እንዲሁም ህዝቦች በቋሚነት በአንድ አከባቢ ሰፍረው እንዲኖሩና ከተሞች እንዲስፋፉ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ የናይሎቲክ አብዮት በሰው ልጅ የአኗኗር ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ አስመዝግቧል፡፡ የዚህ ሁሉ ለውጥ መሰረት የግብርና ስራ ነው፡፡ በአጠቃላይ ግብርና ለሁሉም ዘመናዊ ስልጣኔዎች መሰረት ሆኗል፡፡

ቀደምት ሜሶፖታሚያዎች የቀን አቆጣጠር (ካላንደር) እንዲሁም የሂሰብ ስሌቶችን በመጠቀም የክብ ቅርጽ $360^0$ (ዲግሪ) እንዳለው እና አንድን ቀንን በ24 ሰዓት በመክፈል አንድ ሰዓት 60’ (ደቂቃ) እንዳለው ማግኘት ችለዋል፡፡ ይህ ግኝት ደግሞ ለዘመናዊ ሰዓት አቆጣጠር መሰረት ሆኗል፡፡ በተጨማሪም በውሃ የሚስራ ሰዓት ማግኘት ችለዋል፡፡

ቀደምት ሜሶፖታሚያኖች የሸክላ አፈርን በመጠቀም የተለያዩ ህንጻዎችን በመገንባትም ይታወቃሉ፡፡ በተጨማሪም የሸክላ አፈርን በመጠቀም የራሳቸውን ስነ ፅሁፎች መፍጠር ችለዋል፡፡ የሜሶፖታሚያን ስነ ፅሁፍ **ኩኒፎርም** ይባላል፡፡



ሥዕል 4.1.1 የሜሶፖታሚያን ስነ ፅሁፍ ኩኒፎርም

ከጊዜ በኋላ አካዲያኖች፣ ባቢሎኒያኖች ፣ አሲሪያኖች እና ፐርሽያኖች ሜሶፖታሚያኖችን በመወረር በቅደም ተከተላቸው ገዝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ወራሪዎች ለሜሶፖታሚያ ስልጣኔ ከፍተኛ አሰተዋፅኦ አበርክዋል፡፡

በአጠቃላይ የሜሶፖታሚያ ጠንካራ ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አደረጃጀት በውሰጣዊ ችግርና በውጫዊ ችግር ምክንያቶች ሊወድቅ ችሏል፡፡ የውስጣዊ ችግር የእርስ በእርስ ጦርነት ሲሆን የውጫዊው ችግር ምክንያት ደግሞ በ6ኛ ዓ.ዓ ፐርሺያኖች ያደረጉባቸው ተደጋጋሚ ወረራ ነው፡፡

## 4.1.2. ቀደምት የህንድና ቻይና ስልጣኔዎች

### ሀ. ቀደምት የህንድ ስልጣኔ

### የሙከራ ጥያቄዎች


1. የቀደምት ሜሶፖታሚያ እና ህንድ ስልጣኔዎችን የሚያመሳስላቸው ነገሮች ምንድናቸው?

2. የቀደምት ህንድ ስልጣኔ ላይ በመወያየት አብራሩ
3. የቀደምት ህንድ ስልጣኔ በየትኛው የወንዞች ዳርቻ ተመሰረተ?

ቀደምት የህንድ ስልጣኔ የተጀመረው በኤሺያ አህጉር በኢንዱስና ጋንጀስ የወንዞች ሸለቆዎች አከባቢ ነው፡፡ ይህም ስልጣኔ ከ2,500 እስከ 1,500 ዓ.ዓ ድረሰ ሊቆይ ችሏል፡፡ የህንድ ስልጣኔ መስራች ህዝቦች ድራቪዲያኖች በመባል ይታወቃሉ፡፡ እንደ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ በኢንዱስና በጋንጀስ ወንዞች ዳርቻ አከባቢ ያሉት ውሃ እና ለም አፈር ለግብርና ምቹ በመሆናቸው ለህንዶች ስልጣኔ መመስረት ምክንያት ሆነዋል፡፡ በተለይ ጥጥ በማምረት የሸማ ልብሶችን ሰርተው ለአለም ህዝቦች አስተዋውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደምት ህንዶች ወንዞችን በመጥለፍ የመስኖ እርሻ ስራ እንዲሰፋፉ ትልቅ አስተወጽኦ አበርክተዋል፡፡ እንዲሁም የሸከላ አፈርን በመጠቀም የተለያዩ ግንባታዎች፣ እደ-ጥበቦች እና የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን በመስራት ሲጠቀሙበት ቆይዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀደምት ህንዶች የተለያዩ ጌጣጌቶችን በማምረት ከተለያዩ የአለም ህዝቦች ጋር በመነገድ በአለም ላይ ይታወቁ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ከፐርሺያ፣ ሱሜሪያ፣ ቻይና፣ አክሱም፣ ግብፅ እና ከአውሮፓ ሀገር ነጋዴዎች ጋር ሲለዋወጡ ቆይቷል፡፡ ቀደምት የህንድ ነጋዴዎች የራሳቸው ማህተምና የምርት ዝርዝር (trade manual) በማዘጋጀት ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡

በቀደምት የህንድ ስልጣኔ የሸክላ አፈርን በመጠቀም የተገነቡት ከተማዎች ሀራፓና ሞሂንጆዳሮ ይባላሉ፡፡ በአርኪዮሎጂ ጥናት መሰረት ሁለቱ ከተሞች በዘመናዊ አሰራር መልክ የተገነቡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ሁለቱ ከተሞች ፍሳሽና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ እና የሕዝብ መታጠቢያ ገንዳዎች አሏቸው፡፡



ሥዕል. 4.1.2 (ሀ) ቀደምት የሞሂንጃ ዳሮና ሐራፓ ከተሞች ቅሪት

በቀደምት የህንድ ስልጣኔ ህዝቦች የተለያየ የስራ ክፍፍል ነበራቸው፡፡ በዚህ ስራ ክፍፍል መሰረት ህዝቦች የየራሳቸው የስራ ድርሻ ኣላቸው፡፡ በዚህ መስረት የአከባቢ አለቆች የአከባቢውን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት ነበራቸው፡፡ የሀይማኖት አባቶች ደግሞ ህብረተስቡ የሀይማቱን ህግና ደንብ እንዲያከብሩና አብሮነትን እንዲያጎለብቱ ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ቆይቷል፡፡ ቀደምት የህንድ ታዋቂ ሀይማኖቶች ሂንዱይዝምና ቡዲዝም በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሁለቱም ሀይማኖቶች ህብረተሰቡ የአብሮነትን እሴት እንዲጎለብቱ ሲያስተምሩ ቆይቷል፡፡

በጠቃላይ ቀደምት የህንድ ስልጣኔ የተለያዩ እውቀቶችንና ሙያዎችን ለዓለም ህዝብ አበርክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ቀደምት የህንድ ስልጣኔ በውስጣዊና ውጫዊ ችግር ምክንያቶች ሊወድቅ ችሏል፡፡ የውስጣዊው ችግር የተላላፊ በሽታዎች መስፋፋትና ድርቅ ሲሆኑ የውጫዊ ችግር

ምክንያት ደግሞ በ1500 ዓ.ዓ አርያኖች የደረጉት ተደጋጋሚ ወረራ ነበር፡፡

## ለ.ጥንታዊ የቻይና ስልጣኔ

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. ቀደምት የቻይና ስልጣኔ ከሌሎች አከባቢ ስልጣኔዎች በምን ይለያል?
2. በቀደምት የቻይና ስልጣኔ ውስጥ የተስፋፉ ግኝቶች ምንድናቸው? በቡድን ተወያዩበት
3. የኮንፊሺያኒዝም ፍልስፍና ምንን ያካትታል?

ቀደምት የቻይና ስልጣኔ የተመሰረተው በኤሺያ አህጉር በሚገኙ በያንግቲዝና ህዋንግሆ የወንዞች ሸለቆዎች ውስጥ ነው፡፡ ከ1700 ዓ.ዓ ጀምሮ በእነዚህ የወንዞች ዳርቻ አካባቢ የተለያዩ ስልጣኔዎች ተስፋፍተዋል፡፡ ጥንታዊ የቻይና ስልጣኔ የሚታወቀው በሀር ልብስ ምርት፣ በከሰል ድንጋይ፣ በሴራሚክስ ስራ፣ በጦር መሳሪያ (በባሩድ) ምርት እና በእንጨትና የቆዳ ስራ ምርቶች ናቸው፡፡ በ150 ዓ.ዓ አከባቢ የማባዣ ማሽንና በሰውና በእንስሳት ጉልበት የሚንቀሳቀሱ ሰረገላዎችን ሰርተዋል፡፡

ቀደምት ቻይናውያን ቀርከሀን በመጠቀም የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን ሰርተው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ እንዲሁም ቀርከሀን በመጠቀም የራሳቸውን ስነ ፅሁፍ መፍጠር ችለዋል፡፡ የቀደምት ቻይና ስነ-ፅሁፍ ሎጎገራፊክሰ ይባላል፡፡ የጥንታዊ ቻይያና ስነ-ፅሁፍ የሚገለፀው በስዕላዊ መልክ ነው፡፡ በሎጎገራፊክሰ ስነ ፅሑፍ አንድ ምልክት አንድ ሀሳብን ይገልጻል፡፡

የቀደምት ቻይና ነገስታት አህዳዊ መንግስትን በመመስረት ይታወቃሉ፡፡ ከቻይና ስርወ መንግስታት ውስጥ ታዋቂዎቹ ሻንግ (1700-1122 ዓ.ዓ) እና ቾን(1122-256 ዓ.ዓ )ናቸው፡፡ እነዚህ ነገስታት በቅደም ተከተል ቻይናን ገዝተዋል፡፡ በሁለቱም ስርወ መንግስት አገዛዝ ቻይናን ከውጫዊ ጠላት ለመከላከል በድንበራቸው ላይ 7400 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው የግምብ አጥር አሰርተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የታጠረው ግብ የተጠበቀውን ያህል ቻይናን ከውጪ ኃይል ወራሪ ሊከላከል አልቻልም፡፡ ምክንያቱም ወደ ጎን ያለው ርዝመት በጣም ረጅም ሰለሆነ አሰተማመኝ የሆነ ጥበቃ ሊደረግለት አልቻለም፡፡




ሥዕል.4.1.2 (ለ) ትልቁ የቻይና የግንብ አጥር

ቀደምት ቻይናዊያን በስነ-ፅሁፍና በኮንፊሻኒዝም ፍልስፍናም ይታወቃሉ፡፡ የኮንፊሻኒዝም ፍልስፍናን የመሰረተው ሰዉ ኮንፊሽስ (551-479 ዓ.ዓ) ይባላል፡፡ የኮንፊሻኒዝም ፍልስፍና በህበረተሰቡ ውስጥ መልካም ስነ ምግባር እንዲስፋፋ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኮንፊሻኒዝም ፍልስፍና መሰረት አንድ የቤተሰብ አባል በእድሜውና በያታው መከባበር እንዳለበት፣ ባህሉንና ቱፊቱን መጠበቅ እንዳለበት ያስተምራል፡፡ ህብረተሰቡም ለመንግስት የሚፈልገውን ትብብር መፈጸም እንዳለባቸውና መንግስትም የህዝቡን ባህልና ወግ የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለበት ያስተምራል፡፡ በድምሩ የኮንፊሻኒዝም ፍልስፍና መከባበርና መረዳዳት ላይ ያተኮረ ነው፡፡

በአጠቃላይ ቀደምት የቻይና ስልጣኔ እራሱን ችሎ የተመሰረተ ስልጣኔ ነው፡፡ ምክንያቱም የቀደምት ቻይና ስልጣኔ ከውጭ ኃይሎች ጫና ነፃ ሆኖ የተመሰረተ ሰለሆነ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ቀደምት የቻይና ስልጣኔ ከሌሎች የአለም ስልጣኔ የተለየ ነበር፡፡

### 4.1.3.ጥንታዊ የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔዎች

#### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የጥንታዊ የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ የት ተጀመሩ?
2. ከጥንታዊ የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔዎች ውስጥ በዘመናዊው አለም የሚተገበሩትን በመለየት ተወያዩበት፡፡ የሁለቱንም ስልጣኔ ውጤቶችን ዘርዝር/ሪ
3. በጥንታዊ የግሪክ ዴሞክራሲና ዘመናው ዴሞክራሲ ላይ ክርክር አድርለጉ

የጥንታዊ ግሪክና የሮማ ህዝቦች በጥንታዊ የአለም ስልጣኔ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ በመድረስ ለአለም ህዝቦች ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ጥንታዊ የግሪክና ሮማን ህዝቦች ብዙ ስልጣኔዎች በጋራ ስለነበራቸው ስልጣኔያቸው ባብዛኛው የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ በመባል ይታወቃል፡፡

### ሀ)ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ

ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ በ3000 ዓ.ዓ አከባቢ በኤጂያን ባህር አከባቢ የተመሰረተ ነው፡፡ ግሪኮች መሬታቸዉን ሄላስ ሲሉ ህዝቦቿን ደግሞ ሄለንስ (ሄለኖች) በማለት ይጠራሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ የሄለንስ ስልጣኔ በመባል ይታወቃል፡፡ ለግሪክ ስልጣኔ መሰረት የሆነው ጥንታዊ የክሬት ስልጣኔ ነው፡፡ የክሬት ከተማ በሜዲቴራኒያን ባህር መካከል የምትገኝ ደሴት ነበረች፡፡ ይሁን እንጂ የክሬት ከተማ ባልታወቀ ምክንያት ሙሉ በሙሉ ከአለም ላይ ጠፋፍታለች፡፡ የክሬት ስልጣኔ የሚኖንያን ስልጣኔ በመባልም ይታወቃል፡፡

የጥንታዊ ግሪክ ስልጣኔ ለተለያዩ የአለም ስልጣኔዎች መስረት ነው፡፡ ቀደምት ግሪኮች የሚታዉቁት በዴሞክራሲ ስርዓት፣ ማራቶን፣ ፍልስፍና፣ ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ህክምና እና በታሪክ ጥናቶች ነው፡፡ በተጨማሪም ቀለማትን በመቀባት ጥበብ፣ የተለያዩ ቅርፃ ቅርጸችን በመስራት፣ በስነ-ህንፃ፣ ስዕል በመሳል እና በተለያዩ ስነፅሑፎች በመግጠም ይታወቁ ነበር፡፡

እንድሁም ጥንታዊ የግሪክ ህዝቦች በተለያዩ ግንባታዎችና በሀይማኖት በአለም ለይ ይታወቁ ነበር፡፡ በተለይ ሀይማኖታቸውን የሚገልፁ የተለያዩ ቅረፃ ቅርፆችን በመስራት የበዓል ቀን አምልኮ ስርአት ያካሂዱበት ነበር፡፡

**የፕሮጅክት ስራ**

**የሚከተለውን ጥያቄ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ**

- **አራት አራት ሆናችሁ በመደራጀት በጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ ሲገለገሉበት የነበሩትን የቤት ዕቃዎች ለምሳሌም በሰዕል 4.1.3 ላይ ያለውን በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሳ ቁሶች በመጠቀም ሰርታችሁ አቅረቡ፡፡**





ሰዕል 4፡1.3 የጥንታዊ ግሪክ ህንፃና ቅረፃ ቅርፆች

**ቀደምት ግሪክ ከምትታወቅበት ውስጥ ዋነኛው የዴሞክራሲ ስርዓት ፅንሰ-ሀሳብን በማመንጨት ነው፡፡ ዴሞክራሲ የሚለው ቃል ከዴሞና ክራቶስ ከሚባሉት ሁለት ቃላቶች የተመሰረተ ሲሆን ትርጉሙም የህዝብ አስተዳደር ማለት ነው፡፡**

**ጥንታዊ የግሪክ ዴሞክራሲና ዘመናዊዉ የምዕራባዊያን ዴሞክራሲ ተመሳሳይነትና ልዩነት አላቸው፡፡ ተመሳሳይነታቸው፤ሁለቱም አሳታፊ መሆናቸው፣ ለአብላጫ ድምፅ መገዛት እና የስልጣን ገደብ መኖር ሲሆን ልዩነታቸው ደግሞ ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ተዘርዝረዋል፡፡**

| ጥንታዊ የግሪክ ዴሞክራሲ | ዘመናው ዴሞክራሲ |
|---|---|
| ህዝቦች በቀጥታ ይሳተፋሉ | ህዝቦች በተወካዮቻቸው በኩል ይሳተፋሉ |
| እድሚያቸው የመምረጥ እና ለመመረጥ ለደረሱ ወንድ ዜጎች ብቻ መብት ይሰጣል | ለዜጎች እኩል የመሳተፍ መብት ይሰጣል |
| ሁሉንም ዜጎች እኩል አያሳትፍም ለምሳሌ፣ ባሮችና ሴቶችን አጣሳትፍም | እዲሚያቸው የመምረጥ እና ለመመረጥ የደረሱ(ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ)ዜጎችን ሁሉ ያሳትፋል |

በጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ ዘመን ለዚህ ስልጣኔ መሰረት የሆኑ ታላላቅ ምሁራን ነበሩ፡፡ እነሱም ሄሮዶተስ (484-425 ዓ.ዓ)፣ ሂፖክራተስ (460-357 ዓ.ዓ)፣ ሆሜር (750-700 ዓ.ዓ)፣ ሶቅራተስ (470-399 ዓ.ዓ)፣ ፕላቶ (427-347 ዓ.ዓ) እና አርስቶትል (384-322 ዓ.ዓ) ናቸው፡፡ ሄሮዶተስ የታሪክ ፀሀፊ ስለነበረ የታሪክ አባት ተብሎ ይታወቃል፡፡ እንዲሁም ሆሜር ኢሊያድና(Iliad) ኦዲሴይ(Odyssey) የሚባሉ ታዋቂ ግጥሞችን በመግጠም ይታወቃል፡፡ በጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ እነዚህ የግሪክ ተመራማሪዎች ለአለም ህዝብ ከፍተኛ አሰተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ የከተማዎች ስልጣኔ በመባልተ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም ከተሞች የራሳቸውን የአስተዳደር ድንበር ስለ ነበራቸው ነው፡፡ የጥንታዊ ግሪክ ከተሞች በዲምሩ ፖሊስ ተብለዉ ይጠራሉ፡፡ ጥንታዊ የግሪክ ከተሞች አስተዳደር የገጠር ቀበሌዎችንም ያጠቃልላል፡፡ የገጠር ቀበሌዎች በግብርና ስራ ይተዳደሩ ነበር፡፡ እነዚህ

የገጠር ቀበሌ ነዋሪዎች ለከተማ አሰተዳደሩ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡ በተጨማሪም ጥንታዊ የግሪክ ከተሞች በንግድ ስራ ዘርፍም ሲተዳደሩ ነበር፡፡ በወቅቱ ከነበሩት ታዋቂ የጥንት ግሪክ ከተሞች አቴንስና እስፓርታ ይባላሉ ፡፡ አቴንስ የጥንት ግሪክ ከተማ ስለ ነበረች እንደ የአስተዳደር ማዕከል ትታይ ነበረች፡፡

የጥንት ግሪክ ከተሞች በእርስ በእርስ ጦርነትም ይታወቁ ነበር፡፡ ለምሳሌ አቴንስና እስፓርታ በተለያዩ ጊዜያት እርስ በእርሳቸው ሲዋጉ ነበር፡፡ ሁለቱ ከተሞች ከእርስ በርስ ጦርነት እራሳቸውን ለመከላከል ሲባል በመካከላቸው የአጥር ግንብ ገንብተው ነበር፡፡ በጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ ዘመን የእስፓርታ መንግስት ሴቶችን ለውትድርና ሲያሰለጥናቸው ነበር፡፡ በዚህ መሰረት ሴቶች በተለያዩ ጦርነቶች ላይ ሲሳተፉ ቆይተዋል፡፡

በመጨረሻም ጥንታዊ የግሪክ ስልጣኔ በውሰጣዊ ችግርና በውጫዊ ችግር ምክንያቶች ተደክሟል፡፡ የውስጣዊው ችግር ምክንያት የእርስ በርስ ጦርነት ሲሆን የውጫዊው ችግር ምክንያት ደግሞ በ6ኛ ዓ.ዓ በፐርሺያኖች የደረሰባት ወረራ ነው፡፡

### ለ.ጥንታዊ የሮማ ስልጣኔ

ጥንታዊ የሮማ ስልጣኔ በ753 ዓ.ዓ በአሁኑ መካከለኛ ጣሊያን ላቲን ተብለው በሚጠሩ ህዝቦች ተመስርቶ የተስፋፋ ነው፡፡ ጥንታዊ ሮማውያን የግሪክ ስልጣኔን ሲጠቀሙ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የራሳቸውን ስልጣኔ በመጨመር ለአለም ህዝቦች ከፍተኛ አሰተዋጾኦ አበርክተዋል፡፡ ጥንታዊ የሮማን ስልጣኔ የሚታወቀው በሪፐብሊክ አስተዳደር ስርአት፣ የተለያዩ ህጎችን በማውጣት፣ በድራማ፣ በቲያትር

እና ትምህርትን በማስፋፋት ነው፡፡ የጥንታዊ የሮማ ትምህርት በይበልጥ ያተኮረው ማንበብና መጻፍ ላይ ነበር፡፡ የሚጽፉበት ፊደል ላቲን ሲሆን በአሁኑ ጊዜ አፋን ኦሮሞን ጨምሮ ብዙ የአለም ቋንቋዎች የላቲን ፊደላትን ይጠቀማሉ፡፡ በተጨማሪም ጥንታዊ የሮማ ስልጣኔ በውሃ ቧንቧዎች ዝርጋታ፣ የከተማ ፍሳሽ ማስወገጃ ቦይዎችና ድልድዮችን በመሰራት እንዲሁም የከተሞቻቸውን ንጽህና በመጠበቅ ይታወቃሉ፡፡

ጥንታዊ የሮማን ሪብሊክ በ509 ዓ.ዓ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህ የሪብሊክ አስተዳደር በሁለት መዋቅር የሚመራ ሆኖ ጠንካራ ህጎች አለው፡፡ እነዚህ የአስተዳደር መዋቅር ሴኔት (Senate)ና ኮንሱል (Consul) በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሴኔት አባል ሆነው መመረጥ የሚችሉ ፓትሪሺያኖች ብቻ ናቸው፡፡ ፓትሪሺያኖችና ፒሊቢያኖች ታዋቂ የሮማን ህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፡፡ በጥንታዊ የሮማ ሪፐብሊክ ውስጥ ፓትሪሺያኖች ሀብታሞችና የገዢ መደብ አባላት ናቸው፡፡ የሴኔት አባል ሆነው የሚመረጡ ዕድሜ ልክ የሚያስተዳድሩ ሲሆኑ የኮንሱል አባሎች ደግሞ ለአንደ አመት ብቻ ያገለግላሉ፡፡ ፒሊቢያኖች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ጭቁን ህዝቦች ሲሆኑ መንግስት የሚፈልገውን ግብር በአስገዳጅነት የሚከፍሉ የህብረተሰብ ክፍል ናቸው፡፡

ጥንታዊ የሮማ መንግስታት በሜድትራኒያን ባህር አከባቢ ጠንካራ የጦር ኃይልና የንግድ መሰመሮችን ተቆጣጥረው ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ከ216-146 ዓ.ዓ በሰሜን አፍሪካ አከባቢ የሚገኙ ጥንታዊ ካርቴጅና ግብፅን በኃይል ተቆጣጥረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥንታዊው የሮማ ስልጣኔ በእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ኃይሉ እስከ መጨረሻ ዘልቆ ሊቆይ አልቻለም፡፡

በዚህ መሰረት ጥንታዊ የሮማን ሪፐብሊክ መንግስት በ27 ዓ.ዓ የኢምፓየር ስርዓት ስር ወደቋል፡፡ ይሁን እንጂ ለ200 አመታት ያህል ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ሊደርስ ችላኋል፡፡ ይህ ጊዜ ፓክስ ሮማና (pax Romana) ወይም ታላቋ ሮም በመባል ይታወቃል፡፡ ቢሆንም በ4ኛው ዓ.ዓ ጥንታዊ ሮማ ለሁለት በመከፈል ምዕራባዊና ምስራቃዊ ሮማ ተመሰረቱ፡፡ በመጨረሻም ምዕራባዊ ሮማ በ476 ዓ.ም በጀርመን ጎሳዎች የወደመች ሲሆን ምስራቃዊ ሮማ (ባይዛንታይን) ደግሞ በ1453 በቱረኮች ወረራ ልትወረር ችላለች፡፡

## 4.1.4 የክርስትና ሀይማኖት አመጣጥና መስፋፋት

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ምን ይባላሉ?
2. ጥንታዊ የሮማን መንግስታት የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮችን ምን አይነት መብት ከለከሏቸው?
3. የክርስትና ሀይማኖት የትና እንዴት እንደ ተስፋፋ ተወያዩበት፡፡

የክርስትና ሀይማኖት የተጀመረው በ1ኛው ዓ.ም በመካከለኛው ምስራቅ ኤሺያ በአሁኑ ፊሊስጤምና እስራኤል በሚባሉት አገሮች ውስጥ በኢየሱስ ክርሰቶስ ተከታዮች አማካኝነት ነው፡፡ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ክርስትያኖች ይባላሉ፡፡ ይህ ስም የተወሰደው ከግሪክ ቃል ነው፡፡ ክርሰቶስ የሚለው ቃል መሲህ የሚል ሲሆን ትርጉሙም ማዳን ማለት ነው፡፡ የክርስትና ሀይማኖት መተዳደሪያ መፅሐፍ ቅዱሰ ይባላል፡፡ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች በመፅሐፍ ቅዱሰ ህግጋት ይተዳደራሉ፡፡

የክርስትና ሀይማኖት ከ1ኛው እስከ 4ኛው ዓ.ም የተለያዩ ችግሮችን አሳልፏል፡፡ ምክንያቱም ጥንታዊ የሮማ ኢምፓየር መንግስታት የክርስትና ሀይማኖት ትምህርትና ተከታዮችን አምርረው ይጠሉ ስለነበር ነው፡፡ በተለይ ከክርስትና ሀይማኖት ትምህርት ውስጥ "የሰው ልጅ እኩልነትን ማስተማሩ" በጥንታዊ ሮማ ኢምፓየር መንግስት ፊት ተቀባይነትን እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡

በጥንታዊ ሮማ መንግታት ዘመን ከ1ኛው እስከ 4ኛ ዓ.ም መካከል አብዛኞቹ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ድሃ የሮማ ህዝቦች ነበሩ፡፡ በዚህ ምክንያት ጥንታዊ የሮማ መንግስት የሮማ ክርስቲያኖችን ለኛ ከመታዘዝ ለኢየሱስ መታዘዝን ይመርጣሉ በማለት የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ላይ ተጽዕኖ አድርሰዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሮማ መንግስታት ብዙ ክርስቲያኖች ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ጭፍጨፋ ሲያካሄዱ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ብዙ ክርስቲያኖች ሞተዋል እንዲሁም ከሀገር ተሰደዋል፡፡

ነገር ግን የሮማ መንግስታት የክርስትና ሀይማኖትን ለማጥፋት ሲያደርጉ የነበረው ተጽዕኖ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡ እንዲሁም የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች እየተጠናከሩና ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱ የሮማ መንግስት ተስፋ እንዲቆርጥ አድርጎታል፡፡ በዚህ ምክንያት በ312 ዓ.ም ታዋቂው የሮማ ንጉስ ቆንስጣንጣይን የክርስትናን ሀይማኖት ተቀብሎ ለክርስቲያኖችን ሙሉ መብት ሰቷል፡፡ የክርስትና ሀይማኖት የሮማ መንግስት ሀይማኖት በመሆን መስፋፋት ችሏል፡፡ በ6ኛው እና 7ኛው ዓ.ም ጥንታዊ የግብፅ ህዝቦችና ኑቢያኖችም የክርስትና ሀይማኖት በሰሜንና ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ እንዲስፋፋ የራሳቸውን አስተዋፅዖ አበርክተዋል፡፡ እንዲሁም ከ500 እስከ 1000 ዓ.ም የሮማ ቤተክርስቲያን መንግስትን በመተካት የሮማንን ኢምፓየር

ማስተዳደር ችሏል፡፡

በመካከለኛው ዘመን (500 እስከ 1500 ዓ.ም) የክርስትና ሀይማኖት በአውሮፓ ትልቅ የበላይነትንና ተቀባይነትን አገኝቷል፡፡ እንዲሁም በአፍሪካ፣ በኤሺያ እና በሰሜንና ደቡብ አሜሪካ መስፋፋት ችሏል፡፡ በተለይ በ332 ዓ.ም በአፍሪካ ቀንድ የአክሱም መንግስት በቅድሚያ የክርስትና ሀይማኖትን በመቀበል ሂማኖቱን እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ግን የክርስትና ሀይማኖት በአፍሪካ አህጉር በስፋት የተሰፋፋው ከአውሮፓ ሚሽነሮች/ሚሲዮኖች ወደ አፍሪካ አህጉር ከመጡ በኋላ (ከ16ኛ እስከ 18ኛ ዓ.ም) ነው፡፡

**መልመጃ 4.1**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ፡፡

1. ጥንታዊ የሜሶፖታሚያን ስነ ፅሁፍ ምን በመባል ይታወቃል?
2. የሀሞሪቢ ጠንካራ ህግ ማውጣት አላማው ምን ይመስላችኋል?
3. ጥንታዊ የሜሶፖታሚያ፣ ህንድ እና ቻይና ስልጣኔዎች በምን ይመሳሰላሉ? ልዩነታቸውስ ምንድነው?
4. የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ ውጤቶች ዘርዝር/ሪ
5. የወንዞች ዳርቻ ለምን ለጥንታዊ ስልጣኔዎች ምቹ ሆኑ?

## 4.2. የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የአለም ታሪክ

### 4.2.1 የባይዛንታየን ኢምፓየር

**የሙከራ ጥያቄዎች**


1. ኢምፓየር ማለት ምን ማለት ነው?
2. የባይዛንታየን ኢምፓየር የት አከባቢ ተመሰረተ?

ኢምፓየር ማለት ሰፊ አከባቢ ሆኖ በንጉስ ወይም በንግስት የሚመራ ግዛት ማለት ነው፡፡ የባይዛንታይን ኢምፓየር ከ5ኛው እስከ 15ኛ ዓ.ም ከምስራቅ አውሮፓ እስከ መካከለኛው ምስራቅ አውሮፓ ያሉትን አካባቢ ሲያስተዳድር ነበር፡፡ የባይዛንታይን ኢምፓየርን የመሰረተው ታላቁ ቆንስጣንጣይን ይባላል፡፡ በ324 ዓ.ም የምዕራብ ሮማን በመልቀቅ የባይዛንቲም ከተማን የአስተዳደሩ ማዕከል አድርጓታል፡፡ በ330 ዓ.ም የባይዛንታየን ኢምፓየር ስም ወደ ንጉሱ ስም፣ **ኮነስታንቲኖፐል** ተቀይሮ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የባይዛንታየን ከተማ የምስራቅ አውሮፓ የአስተዳደር ማዕከል ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል፡፡

የኮንሰታንቲኖፕል ከተማ በአውሮፓና በኤሺያ የንግድ መስመር ላይ በመመስረቷ ምጣኔ ሀብቷን ማሳድግ ችላለች፡፡ በተጨማሪም የሜደቴራኒያንና የጥቁር ባህር አካባቢ የንግድ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር የባይዛንታየን ከተማ ምጣኔ ሀብት እንዲበለፅግ አድርገዋል፡፡ ከዚህ በሚገኘው ገቢ ትልቅ እግረኛና የባህር ጦር ኃይል ገንብቷል፡፡ የባይዛንታይን ኢምፓየር ከምዕራብ ሮማ ውድቀት በኋላ የአውሮፓውያን የስልጣኔ ማዕከል በመሆን የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

የባይዛንታይን ኢምፓየርን ሲያስተዳድሩ ከነበሩት ነገስታት ውስጥ ጁስቲኒያ (527-565 ዓ.ም) ታዋቂ ንጉስ ነበር፡፡ የባይዛንታየን ኢምፓየር ትልቅ ደረጃ የደረሰውና ግዛቱ የተስፋፋው በጁስቲኒያ አስተዳደር ዘመን ነበር፡፡ የባይዛንታየን ኢምፓየር ግዛት ከደቡብ ምስራቅ አውሮፓ እስከ ሶሪያና ሊባኖስ ይደርስ ነበር፡፡ እንዲሁም የሰሜን አፍሪካ አካባቢንና ግብፅን መቆጣጠር ችለው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የሜድትራኒያን አከባቢ ፖሊቲካና ምጣኔ ሀብትን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር አስገብተው ነበር፡፡ የባይዛንታየን ኢምፓየር ከኮንሰታንቲኖፕል ከተማ

በተለያዩ አቅጣጫ በመስፋፋት ትልቅ ኢምፓየር መሆን ችሏል፡፡




ካርታ. 4.2 (ሀ) የባይዛንታየን ኢምፓየር

ንጉስ ጁስቲኒያ በግሪክና በሮማ ስልጣኔ ዘመን የወጡትን ህጎች በመጨመር አዲስ ህግ አርቅቋል፡፡ ይህንንም ህግ የጁስቲኒያ ህግ በማለት ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ንጉስ ጁስቲኒያ፤ አንድ አምላክ፣ አንድ ኢምፓየር እና አንድ ሀይማኖት የሚል ሃሳብን በባይዛንታየን ኢምፓየር ውስጥ እንዲሰፋፋ አድርጓል፡፡

ይህ ንጉስ የመንግስት አስተዳደርንና የሀይማኖት አስተዳደርን በማስተሳሰር ኮንስታንቲኖፕል የአስተዳደርና የክርስትና ሀይማኖት ትምህርት ማዕከል እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ውብ የሆኑ ቤተመንግስት፣ ቤተ መፅሃፍ እና ቤተክርስቲያናትን በኮንስታንቲኖፕል ከተማ ውስጥ ተገንብተዋል፡፡ ሮማኖች የኪነ ጥበብ እና የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም

ውብ እና ማራኪ የሆኑ ስዕሎችን በመሳል ይታወቁ ነበር፡፡ የግሪኮ-ሮማ፣ ፐርሽያኖች እና የአረቦችን ስነ ህንፃ ጥበብበ በማሻሻል ይጠቀሙበት ነበር፡፡ በተለይ ውብ የሆኑ ቤተክርስቲያኖችን በማሰገንባት ይታወቁ ነበር፡፡ ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የሀጊያ ሶፊያ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ በአጠቃላይ የባይዛንታየን ኢምፓየር መንግስታት በህዝብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ነበራቸው ፡፡



**ሥዕል፡4.2 (ለ) የሀጊያ ሶፊያ ቤተክርስቲያን**

የባይዛንታየን ኢምፓየር ምጣኔ ሀብት(ኢኮኖሚ) የተመሠረተው በግብርና፣ ንግድ እና የተለያዩ እደጥበብ ስራ ላይ ከሚገኝ ገቢ ሲሆን የምጣኔ ሀብት ስርዓታቸው የፊውዳሊዝም ስርአት ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ መሬት የባለባቶች ሲሆን ሰፊው ህዝብ ደግሞ ጪሰኛ ነበር፡፡ አርሶ አደሮች የባለባቶችን መሬት የሚያርሱ ሲሆን ከሚያገኙት ምርት ይበልጡን ምርት ለባለባቶች ለመስጠት ይገደዱ ነበር፡፡ በተለያዩ የእደ ጥበብ ስራ ላይ የተሰማሩትም ከሚየገኙት ገቢ ለባለባቶች ይገብሩ ነበር፡፡በተጨማሪም የሜድትራኒያን

የንግድ መስመርን በመቆጣጠር ትልቅ ገቢ ሲያገኙ ነበር፡፡ የንግድ ስርዓትን ለማዘመን ከወርቅ የተሰሩ ሳንቲሞችን በመስራት ይጠቀሙበት ነበር፡፡ በአጠቃላይ ከተለያዩ አቅጣጫ በሚያገኙት ገቢ የባይዛንታየን ኢምፓየር ፖሊቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ አደረጃጀቱን አጠናከሯል፡፡

በውጫዊና በውስጣዊ ችግር ምክንያቶች የባይዛንታየን ኢምፓየር በ7ኛው ዓ.ም መዳከም ጀመረ፡፡ በተለይ የሜድትራኒያንና የቀይ ባህር አከባቢ የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር ፍላጎት ከነበራቸው ሀገሮች እንደ ስላቮች ፣ ሱልጂክ ቱርክ እና ኦቶማን ቱረክ ጋር በቅደም ተከተል ለዘመናት ሲዋጉ ቆይተዋል፡፡ በመጨረሻም ከኦቶማን ቱርክ ጋር በ1453 ዓ.ም ባደረጉት ጦርነት ኦቶማን ቱረኮች የኮንሰታንቲኖፐል ከተማን በመቆጣጠር ኮንስታንቲኖፐል የሚለውን ስምም ወደ ኢስታንቡል ቀይሯል፡፡

በአጠቃላይ የባይዛንታይን ኢምፓየር የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ እንዲቀጥል በማድረግ፣ የፊውዳል ስርዓት እነዲስፋፋ በማድረግ፣ የመንግስትና የሀይማኖት አስተዳደርን በማስተሳሰር ትልቅ ሀብት ማፍረት እና የጥንት ዘመን ስልጣኔ ከመካከለኛው ዘመን ስልጣኔ ጋር እንዲተሳሰር ከፍተኛ አሰተወፅዖ አበርክቷል፡፡

## 4.2. 2. የእስልምና ሀይማኖት አመጣጥና መስፋፋት

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. እስላም ማለት ምን ማለት ነው?
2. የእስልምና ሀይማኖት ትምህርት የት ተጀመረ?
3. የእስልምና ሀይማኖት በምን አይነት አካሄድ በኢትዮጵያ ተስፋፋ?

በሳውዲ አረቢያ አከባቢ ሲኖሩ የነበሩ ህዝቦች አርብቶ አደር ነበሩ፡፡እንዲሁም የሳውዲ አረቢያ አከባቢው ቆላማ ስለሆነ ለሰው ልጅ ኑሮ እምብዛም ምቹ አልነበረም በዚህ ምክንያት ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ነበሩ ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በንግድ ስራ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ሲሳተፉ ቆይተዋል፡፡ ከጊዜ በኃላ የእስልምና ሀይማኖት በሳውዲ አረቢያ መስፋፋት ጀመረ ፡፡

የእስልምና ሀይማኖት ከሳውዲ አረቢያ አከባቢ በ612 ዓ.ም ወደ ተለያዩ አከባቢዎች መስፋፋት ጀመረ፡፡ የእስልምና ሀይማኖት በማስተማር እንዲስፋፋ ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው ነቢዩ መሀመድ ነበር፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ትምህርት መሰረት ያደረገው ለፈጣሪ የበላይነት መገዛት የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡ እንዲሁም የስው ልጅ ከመጥፎ ስራና ከክፉ ድርጊት መቆጠብ አለበት የሚለዉ አስተምሮት ነዉ፡፡

የእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት በጀመረበት ወቅት ትልቅ ተቃውሞ ከቁረሽ ጎሳዎች አጋጥሞታል፡፡ ይህ የቁረሾች ተቃውሞ በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረስ የሀይማኖቱ ተከታዮች በ622 ዓ.ም ከመካ ወደ መዲና እንዲሰደዱ አድርጓል፡፡ ይህ የስደት ጊዜ በታሪክ ሂጂራ በመባል ይታወቃል፡፡ ሂጂራ በአሁን ወቅት የእስልምና ሀይማኖት የቀን አቆጣጠር (ካላንደር) በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

በ624 ዓ.ም የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች በመዲና ከተማ ኃይላቸውን በማጠናከር ባድር በሚባል ጦር ሜዳ ቁረሾችን ማሸነፍ ችለዋል፡፡ ቀጥሎም በ630 ዓ.ም መካን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር

ለመጀመሪያ ጊዜ መካን በአስተዳደራቸው ስር አስገብተዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ባቋቋሙት አሰተዳደር ነብዩ መሀመድ የእስልምና ሀይማኖትና የፖሊቲካ መሪ መሆን ችሏል፡፡

ከነብዩ መሀመድ አስተዳደር ዘመን ጀምር የእስልምና ሀይማኖት ትምህት በቁራን ይመራል፡፡ በ632 ዓ.ም ነብዩ መሀመድ ከሞተ በኋላ የተለያዩ የሙስሊም ካሊፌቶች አስተዳደሩን ተክቶ የእስልምና ሀይማኖትን አስፋፍተዋል፡፡ ካሊፍ ማለት ተወካይ ማለት ሲሆን የእስልምና ሀይማኖትና ፖሊቲካን የሚመሩ መሪዎች ነበሩ፡፡ አራቱ የመጀመሪያ የሙስሊም ካሊፌቶች አቡበከር (632-634ዓ.ም)፣ ኡመር (634-644 ዓ.ም)፣ ኦስማን (644-656ዓ.ም) እና አሊ (656-661 ዓ.ም) ናቸው፡፡ እነዚህ ካሊፌቶች የእስልምና ሀይማኖት በተለያዩ አከባቢዎች እንዲስፋፋና የሙስሊም ኢምፓየሮች እንዲመሰረቱ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

በቁራን ትምህት ላይ በመመስረት አራቱ የመጀመሪያ ካሊፌቶች የእስልምና ሀይማኖት በተለያዩ የአለም ሀገሮች እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ የእስልምና ሀይማኖት ሊስፋፋ የቻለው በሁለት መንገድ ነው፡፡ እሱም በሰላማዊ መንገድና በጦርነት ነው፡፡ በአፍሪካ ቀንድ አከባቢዎች በሰላማዊ መንገድ የተስፋፋ ሲሆን በሰሜን አፍሪካ ፣ ምስራቅ አውሮፓ፣ የመካከለኛ ምሰራቅ እና ሰሜን ምስራቅ ኤሺያ ሀገሮች ደግሞ በጦርነት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከእስልምና ሀይማኖት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ብዙ ስልጣኔዎች ማደግ ችለዋል፡፡ የፐርሺያና የግሪኮ-ሮማ ህንፃ ግንባታ ስልጣኔን በማሻሻል በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲሰፋፋ ከፍተኛ ሚና

ተጫውቷል፡፡ እንሁም የአረብኛ ቋንቋም የአለም ማህበረስብ የመግባቢያ ቋንቋ እንዲሆን አድረጓል፡፡

**መልመጃ 4. 2**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. ጁስቲኒያ የሚባል የባይዛንታይን ንጉስ በምን ስራ ይታወቃል?
2. የባይዛንታይን ስልጣኔ ውጤቶችን ዘርዝር/ሪ
3. የባይዛንታይን ኢምፓየር ባህሪያትን አብራራ/ሪ
4. የእስልምና ሀይማኖት ወደ ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ እንዲስፋፋ ያደረጉት ምክንያቶችን ዘርዝር/ሪ

**ማጠቃለያ**

አብዛኞቹ ጥንታዊ የአለም ስልጣኔዎች የወንዞችን ዳርቻ መሰረት በማድረግ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ለግብርና ስራ ምቹ የሆነ ለም አፈርና በቂ ውሃ ስለ ነበራቸው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የወንዞች ዳርቻ ለተለያዩ የአለም ስልጣኔዎች ምቹ ሊሆኑ ችለዋል፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ብዙ የወንዞች ዳርቻዎች ለብዙ የአለም ስልጣኔዎች መሰረት መሆናቸዉ ተረጋግጠዋል፡፡

ከጥንት የኤሽያ እና የአውሮፓ ስልጠኔዎች ታዋቂዎቹ ሜሶፖታሚያ፣ ህንድ፣ ቻይና፣ ሮማ እና ግሪክ ናቸው፡፡ በእነዚህ የጥንት ዘመን ስልጠኔዎች የተገኙ እድገቶች ውስጥ የዴሞክራሲ ፅነሰ-ሀሳብ፣ የሪፐብሊክ ስርዓት፣ የተለያዩ ህጎች፣ ፍልስፍናዎች፣ የህክምና ጥናቶች እና የተለያዩ የቅርፃ ቅርጾች ስራዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ለዘመናዊው ትምህርት መሰረት የሆኑ እንደ ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ህክምና እና የታሪክ ጥናቶች ተካሄደዋል፡፡ በተጨማሪም ቀለማትን የመቀባት ጥበብ፣ ስነ-ህንፃ፣ ስነ-ሥዕል መሳል እና የተለያዩ ስነ-ጽሑፎችን ግጥሞችን በመግጠም ለአለም ህዝብ አበርክተዋል፡፡

የክርስትና ሀይማኖት የተጀመረው በ1ኛው ዓ.ም በመካከለኛው ምስራቅ በአሁኑ ወቅት ፊሊስጤምና እስራኤል በሚባሉ ሀገራት አከባቢ

በክርሰቶስ ተከታዮች አማካኝነት ነው፡፡ የክርስትና ሀይማኖት ከ1ኛ እስከ 4ኛ ዓ.ም የተለያዩ ችግሮችን ቢያሳልፍም ከ4ኛዉ ዓ.ም በኃላ በተለያዩ የአለም ሀገራት መስፋፋት ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የእስልምና ሀይማኖት በሳውዲ አረቢያ አከባቢ በነቢዩ መሀመድ ትምህርት አማካኝነት በ612 ዓ.ም ተጀመረ፡፡ ከነብዩ መሀመድ ሞት በኋላ (632 ዓ.ም) የተለያዩ የሙስሊም ካሊፌቶች የእስልምና ሀይማኖት በተለያዩ አከባቢዎች እንዲስፋና የሙስሊም ኢምፓየሮች እንዲመሰረቱ አድርገዋል፡፡

## የምዕራፍ 4 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ክፍል I. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች “እውነት” ወይም “ሐሰት” በማለት መልስ/ሽ

1. ግብርና የሁሉም ስልጣኔዎች መሰረት ነው፡፡
2. የሜሶፖታሚያን ስነ-ፅሁፍ ሃይሮግሎፊክስ ይባላል፡፡
3. የእስልምና ሀይማኖት በአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የተሰፋፋው በሰላማዊ መንገድ ነው፡፡
4. የባዛንታይን ኢምፓየር ነገስታት ለክርስትና ሀይማኖት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡
5. የባዛንታይን ኢምፓየር ነገስታት ለክርስትና ሀይማኖት መስፋፋት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

**ክፍል. II. በ "ለ" ስር ያለውን ምርጫ ከ "ሀ" ስር ካሉት ጥያቀየቄዎች ጋር አዛምድ/ጂ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጥንታዊ ሜሶፖታሚያ | ሀ. ኮንሰታንቲኖፐል |
| 2. ጥንታዊ ህንድ | ለ. ሪፐብሊክ |
| 3. ጥንታዊ ቻይና | ሐ. ዴሞክራሲ |
| 4. ባይዛንታይን | መ. ሎጎግራፊክስ |
| 5. ጥንታዊ ሮማ | ሠ. ኩኒፎርም |
| 6. ጥንታዊ ግሪክ | ረ. ሀራፓ |

**ክፍል III.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥት ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ መልስ/ሽ**

1. የጥንታዊ ሜሶፖታሚያ ስልጣኔ በየትኛው ወንዝ ዳርቻ ተመሰረተ?
   - ሀ. ጋንጀስ እና ኢንዱስ
   - ለ. ትግሪስ እና ኢፍራጤስ
   - ሐ. ያንግቲዝ እና ህዋንግሆ
   - መ. ናይል እና ቲግሪስ
2. ከሜሶፖታሚያ ነገስታት ህጎችን በማርቀቅ የሚታወቀው ንጉስ ማን ይባላል ?
   - ሀ. ጁስቲኒያ
   - ለ.ሔሮዶተስ
   - ሐ. ሀሞራቢ
   - መ.ቆንስጣንጣይን
3. ከጥንታዊ ስልጣኔ ዉስጥ በውሃ የሚስራ ሰዓት በመስራት የሚታወቀዉ የትኛው ነው?
   - ሀ. ጥንታዊ ግሪክ
   - ለ.ጥንታዊ ህንድ
   - ሐ. ጥንታዊ ቻይና
   - መ.ጥንታዊ ሜሶፖታሚያ
4. ከ5ኛው እስከ 15ኛዉ ዓ.ም የሜድትራኒያንን አከባቢ ተቆጣጥሮ ሲያስተዳድር የነበረው ኢምፓየር የትኛው ነው?
   - ሀ. ባይዛንታይን
   - ለ.ጥንታዊ ሮማ
   - ሐ.ግሪኮ-ሮማ
   - መ.ሞንጎሊያ

5. ከጥንታዊ ግሪክ ምሁራን ውስጥ "የታሪክ አባት" በመባል የሚታወቀው ማነው?

ሀ.ፕላቶ ሐ. ሔሮዶተስ

ለ.ሂፖክራተስ መ.ሶቅራጠስ

6. ከሚከተሉት ጥንታዊ ስልጣኔዎች ውስጥ ከውጭ ጫና ነፃ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.የጥንታዊ ቻይና ሐ.የጥንታዊ ግሪክ

ለ.የጥንታዊ ህንድ መ.የጥንታዊ ሮማ

# ምዕራፍ 5

# ጥንታዊ የአፍሪካ ታሪክ

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች፤**

- ጥንታዊ የአፍሪካ ስልጣኔዎችን ትዘረዝራለህ/ሽ
- የጥንት ኑቢያ ስልጣኔን ከሌሎች ስልጣኔዎች የሚለየውን ትገነዘባለህ/ሽ
- ጥንታዊ የአለም ስልጣኔ አመስራረትን ታመዛዝናለህ/ሽ
- የጥንት ኑቢያ ስልጣኔ ልዩ የሚያደርገውን በመገንዘብ ታደንቃለ/ሽ
- የጥንት ኑቢያና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ባህርያት ትገነዘባለህ/ሽ
- የአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ግዛት በፊትና በኋላ ያሉትን ሁኔታዎችን በማስተያየት ትገመግማለህ/ሽ::

## መግቢያ

በምዕራፍ አራት ውስጥ ስለ ቀደምት የአለም ስልጣኔዎች አጀማመርና አስተዋፅኦዋቸው ተረድተሀል/ሻል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግም ከጥንታዊ የአፍሪካ ስልጣኔዎች ውስጥ ስለ ጥንታዊ ግብፅ፣ ኑቢያ እና ሜሮኤ ትማራለህ/ሽ፡፡ ጥንታዊ ግብፅ፣ ኑቢያ እና ሜሮኤ ታዋቂና የመጀመሪያ የሰለጠኑ ጥንታዊ የአፍሪካ ሀገር ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ የተመሰረተው በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ሲሆን ኑቢያ እና ሜሮኤ ደግሞ በአሁኑ ሱዳን ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ ነው፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- ጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ ለአለም ስልጣኔ ያበረከተውን ትዘረዝረለህ/ሽ
- የጥንት ኑቢያና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ባህርያት ትገናዝባለህ/ሽ
- በአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ግዛት በፊት የነበሩትን ሁኔታዎችን ትገልፃለህ/ሽ
- ብረትን የማቅለጥ ስልጣኔና ጥቅሙን ታብራራለህ/ሽ

## 5.1 ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የጥንታዊ ግብፅ መንግት በየተትኛው የአፍሪካ ክፍል ይገኝ ነበር?
2. ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ በምን ይገለፃል?

ጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ የተመሠረተዉ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ በናይል ወንዝ ስምጥ ሸለቆ አከባቢ ነው፡፡ ጥንታዊ የግብፅ ህዝቦች የናይል ወንዝ ዉኃን በመጠቀም እንደ ተልባ፣ ገብስ፣ ዘንጋዳ እና ስንዴ ያሉ ሰብሎችን በማምረት ይታወቁ ነበር፡፡ በተጨማሪም በግብርናና በግንባታ ሥራዎች በአለም ላይ ይታወቁ ነበር፡፡ ነገር ግን አብዛኛው ጥንታዊ የግብፅ ህዝቦች ድሀ ነበሩ፡፡ ከዚህም የተነሳ ዝቅተኛ የሆነ ኑር ይኖሩ ነበር፡፡

ናይል የሚለው ቃል የመጣው ከግሪክ ቃል ሲሆን ትረጉሙም ሸለቆ ማለት ነው፡፡ እንደ ግሪክ ታሪክ ፀሀፊ ሂርደተስ አገላለፅ ግብፅ(Egypt) ማለት የናይል ስጦታ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ለጥንታዊ ግብፅ መንግስት መመስረት ትልቁ ምክንያት የናይል ወንዝ መሆኑን

ገልጿል፡፡ በአጠቃላይ ጥንታዊ የግብፅ ህዝቦች ስልጣኔ የናይል ወንዝ ላይ የተመሰረተ ስልጣኔ ነበር፡፡




ካርታ 5.1 (ሀ) የናይል ወንዝ ሸለቆ አከባቢ ስልጣኔዎች

ጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ በአፍሪካ የመጀመሪያና ቀደምት የሆነ ስልጣኔ ነዉ፡፡ ይህ ስልጣኔ ከ3000 ዓ.ዓ አከባቢ ጀምሮ የተስፋፋ ነበር፡፡ የጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ የተለያዩ ጥበብና እውቀቶችን በማጎልበት ለአለም ትልቅ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ ከነሱም ውስጥ የሀይማኖትን ፅንሰ-ሀሳብ፣ የፒራሚድ ግንባታ፣ ስነ-ፅሁፍ፣ የስነ ክዋክብት እና የህክምና ጥናቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ የሚታወቀው የሞተ ሰውን ሬሳ ለረጅም ጊዜ አቆይቶ በማስቀመጥና ከነቤት ዕቃው አብሮ መቅበር ነው፡፡ ይህም ዘዴ "ሙሚፊኬሽን" በመባል ይታወቃል፡፡ ይህንን ስርዓት የሚያካሂዱበት ምክንያት የሞተው ሰው ተመልሶ ይነሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

የጥንታዊ ግብፆች ጽሑፍ ረዥም እድሜ ካላቸዉ የዓለም ጽሑፎች

ውስጥ አንዱ ነበር፡፡ ይህ ጽሑፍ ሃይሮግሎፊክስ በመባል ይታወቃል፡፡ ሃይሮግሎፊክስ ምልክቶች ወይም ሥዕልን በመጠቀም አንድን ሃሳብ ወይም ድምፅ የሚገለፅበት ሂደት ነዉ፡፡ ሃይሮግሎፊክስ የሚጻፍበት ወረቀት መሳይ መሣሪያ ፓፒሬስ ይባላል፡፡ ጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ በተለያዩ ስነ ጽሑፎች ይታወቃል፡፡ ከነሱም ውስጥ ዘ ቡክ ኦፍ ዘ ዴድ (the book of the dead) የሚባለው በጣም ታዋቂ ነው፡፡የዚህ መጽሐፍ ዋና ይዜት ትንሳኤ መኖሩን ለመግለጽ ነው፡፡



ሥዕል.5.1. (ሀ) የሃይሮግሎፊክስ ፅሑፍ በፓፒረሰ ላይ

ጥንታዊ የግብፅ ሥልጣኔ ጠንካራ አስተዳደራዊ መዋቅሮች በማደራጀት ይታወቃል፡፡ ጥንታዊ ግብፅ በአንደ መንግሥት ከመተዳደራቸው በፊት በሁለት መንግስታት ተከፍለው ይኖሩ ነበር፡፡ እነሱም፤

1ኛው የላይኛው ናይል ጥንታዊ የግብፅ መንግስት፡፡ የላይኛው ናይል ጥንታዊ የግብፅ መንግስት መቀመጫው **ቴቢስ** ሲሆን የራሱ የሆነ ነጭ አርማ ነበረው፡፡

2ኛው የታችኛው ናይል ጥንታዊ የግብፅ መንግስት፡፡ የታችኛው ናይል ጥንታዊ የግብፅ መንግስት ማዕከል **ሜምፊስ** በምትባል ዋና ከተማ የነበረ ሆኖ ከላይኛው ግብፅ የሚለይ ቀይ አርማ ነበረው፡፡



በ3100 ዓ.ዓ አከባቢ ሜነስ የተባለዉ የታችኛው የግብፅ ንጉሥ የላይኛውን ጥንታዊ የግብፅ መንግስት በመውረር የላይኛውና የታችኛው ጥንታዊ የግብፅ መንግስታት በማዋሀድ ጠንካራ መንግስት መሰርቷል፡፡ የጥንታዊው ግብፅ መንግስታት አገዛዝ ጊዜያት በሦስት ደረጃ ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፤

- አሮጌዉ ጥንታዊ የግብፅ መንግሥታት ዘመን (2686-2181ዓ.ዓ)
- መካከለኛው ጥንታዊ የግብፅ መንግሥታት ዘመንና (2049-1730ዓ.ዓ)
- አዲሱ የጥንታዊ ግብፅ መንግሥታት ዘመን (1150-1080ዓ.ዓ) ነበሩ፡፡

የጥንት ግብፆች ፈረኦን በሚባሉ መሪዎች ይመሩ ነበር፡፡ በጥንታዊ የግብፅ ቋንቋ ፈረኦን ማለት ከድንጋይ የተሰራ ቤት ማለት ነው፡፡የጥንታዊ ግብፅ ፈረኦኖች ግዙፍ ፒራሚዶችን በመስራት፣ በግብርናና(በመስኖ እርሻ ስራ) ንግድ ስራ ይታቀወቁ ነበር፡፡ በ1500 አመታት ውስጥ 70 ፒራሚዶችን አሰርተዋል፡፡

አብዛኞቹ የተሰሩት በአሮጌዉ የግብፅ መንግስት ዘመን ነው፡፡ ከነዚህ ፒራሚዶችን መካከል ግዙፉ ፒራሚድ የተገነባው በንጉስ **ኩፉ** (2575-2465ዓ.ዓ) ዘመን የተሰራ ነው፡፡ ይህ ፒራሚድ በአሁኑ ወቅት **ጊዛ** በሚባልበት ቦታ ይገኛል፡፡

የጥንታዊ ግብፅ ፒራሚዶችን በብዛት ግብፆች ሊሰሩ የቻሉበት ምክንያት ተጨባጭ መረጃ አልተገኘም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ጥንታዊ ግብፆች ፒራሚዶችን የሰሩት ለተለያየ የሀይማኖት አምልኮዎችና ለነገስታት መቃብርነት አገልግሎት እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በአጠቃላይ የጥንታዊ ግብፅ ነገስታት ስልጣኔ ሕብረተሰቡን በተለያዩ ስራዎች ላይ ያሳተፉ ነበር፡፡

ሥዕል 5.1 (ለ) ከጥንታዊ የግብፅ ፒራሚዶች ውስጥ በከፊል

**የፕሮጅክት ስራ**

የሚከተለውን ጥያቄ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ

- ስድስት ስድስት ሆናችሁ በመደራጀት ሥዕል 5.1(ለ) ያለውን የግብፅ ፒራሚድ እንደ ምሳሌ በመጠቀም በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሶች በመጠቀም ሰርታችሁ አቅርቡ፡፡

ጥንታዊ የግብፅ መንግሥታት የውጭ ኃይል ወራሪ ሲከላከሉ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን የውጭ ኃይል ወረራዎችን ለረጅም ጊዜ ግብፅ ላይ በከፈቱት ጦርነት ምክንያት የግብፅ ሥልጣኔ እየተዳከመ መምጣት ጀመረ፡፡

እነዚህ ወረራዎችም አሞራይትስ(1800 ዓ.ዓ)፣ ሂቲተስ(1289-31ዓ.ዓ)፣ አሲሪያኖች(670-664ዓ.ዓ)እና ፔርሺያኖች (525-332 ዓ.ዓ) ናቸው፡፡በመጨረሻም ግርኮች (332 ዓ.ዓ)እና ሮማዊያን (30-644 ዓ.ም) ባተካሄዱት ወረራ ምክንያት የግብፅ ሥልጣኔ ሊወድቅ ችሏል፡፡

**መልመጃ 5.1**

**ክፍል I፡ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ**

1. ሙሚፊኬሽን የጥንታዊ ግብፅ ፒራሚድ አሰራር ዘዴ መስሪያ ነው፡፡
2. የግብፅ ህዝቦች ከጥንት ዘመን ጀምሮ የናይል ወንዝን ለእነሱ ብቻ እንደተሰጣቸው ልዩ ስጦታ ይቆጥራሉ፡፡
3. የላይኛው ናይል ጥንታዊ የግብፅ መንግስት የራሱ የሆነ ነጭ አርማ ሲጠቀም ቆይቷል፡፡
4. ከጥንታዊ የግብፅ ታረካዊ ቅርሶች ውስጥ ፒራሚዶች ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡

**ክፍል II፡ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ**

5. የጥንታዊ ግብፅ ስነ-ጽሑፍ ምን በመባል ይታወቃል?
6. የጥንታዊ ግብፅ ስነ-ጽሑፍ______________በሚባል የፅሁፍ መሳሪያ ላይ ይፃፋል፡፡
7. የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ለምን በናይል ሸለቆ አከባቢ ተመስረተ?
8. የላይኛውና የታችኛው ጥንታዊ የግብፅ መንግስታት መቼ ተዋሀዱ?
9. ከቀደምት የግብፅ ስልጣኔ ውጤቶች ውስጥ አምስቱን ዘርዝር/ሪ

## 5.2 ጥንታዊ የኑቢያ ስልጣኔ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ጥንታዊ የኑቢያ ስልጣኔ የት እንደ ተመስረተ ካርታ በመስራት አሳይ/ዪ
2. የኑቢያ ስልጣኔ ውጤቶችን ዘርዝር/ሪ


ጥንታዊ የኑቢያ ስልጣኔ የተመሠረተዉ በአሁኑ ሰሜን ምስራቅ የሱዳን ሪፑብልክ ዉስጥ ነው፡፡ የኑቢያ ስልጣኔ የኩሽ ስልጣኔ በመባል ይታወቃል፡፡ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚገልጹት እነዚህ ህዝቦች በኑቢያ

በቆላማ ኑቢያ አካባቢዎች ሲኖሩ የቆዩ መሆኑን ያመለክታል፡፡ኑቢያኖች ኩሽ በሚል ስምም ይታወቃሉ፡፡ ኩሽ የሚለው ስም በጥንታዊት ግብፆች የተሰየመ ሲሆን ከጥንታዊ ግብፅ በስተ ደቡብ ለሚገኙ ህዝቦችን በሙሉ የተሰጠ ስም ነው፡፡ በ2000 ዓ.ዓ አካባቢ ጥንታዊት ኑቢያኖች **ከርማ** በምትባለው ቦታ ጠንካራ መንግስት መስርተው ነበር፡፡

ጥንታዊት ኑቢያ መልካ ምድር አቀማመጥ የተለያየ አየር ንብረት ነበረው፡፡ ምስራቃዊ ቆላማውን ክፍል አረብቶ አደሮች ሲኖሩበት የነበረ ሲሆን ደጋማ ክፍሉ ደግሞ በቂ ዝናብ ያለውና ለግብርና ምቹ የሆነ አከባቢ ነበር፡፡ በተጨማሪም ደጋማው ክፍል በተለያዩ ማዕድናት ለምሳሌ ወርቅና በሌሎች ማዕድናት የበለፀገ ስፍራ ነበር፡፡ በሌላ በኩል የናይል ተፋሰስ አከባቢ የሚገኘው ደግሞ ለም አፈርና በቂ ውሃ ያለው ሲሆን ለግብርና ስራ ምቹ የሆነ ቦታ ነው፡፡

ጥንታዊ ኑቢያዊያን በግብርና ስራ ብቻ ሳይሆን በንግድ ስራም ይታወቃሉ፡፡ ከጥንታዊ ግብፅና ቀይ ባህር አከባቢ የንግድ መስመሮች ጋር የዝሆን ጥርስ፣ ወርቅ እና የሰጎን ላባ ይነግዱ ነበር፡፡ በተለይ ከአርጌው ጥንታዊ የግብፅ መንግስት ጋር በምጣኔ ሀብትና በፖሊቲካው ዘርፍ ጠንካራ ትስስር ፈጥሯል፡፡ ከጥንታዊ የግብፅ መንግስት ጋር በነበራቸው ጠንካራ ግንኙነቶች የተነሳ የግብፆችን ስልጣኔ ከራሳቸው ስልጣኔ ጋር በማዋሃድ ሲገለገሉ ቆይቷል፡፡ ለምሳሌ ሀይማኖት፣ የአስተዳደር ስርዓት፣ እደ ጥበብ፣ የቅርፃቅርፆች ስራ እና የፒራሚዶች ግንባታ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡





ሥዕል 5፡2(ሀ) ጥንታዊ የኑቢያ ህንፃዎች እና ቅርፃ ቅርፆች በከፊል

ጥንታዊ የግብፅ መንግስት በ1500 ዓ.ዓ ኑቢያን በመውረር ለ400 አመታት አከባቢ ሲያስተዳደሩ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጥንታዊ የግብፅ መንግስታት ቀስ በቀስ እየተዳከሙ በመሄዳቸዉ ኑቢያኖች በ1100 ዓ.ዓ ከጥንታዊ የግብፅ መንግስት እራሳቸውን መልሰው ነፃ አውጥተዋል፡፡ በመቀጠልም በ750 ዓ.ዓ ጥንታዊ የኑቢያ መግስት በተራው የግብፅ መንግስትን በመውረር በራሱ አስተዳደር ስር ሊያስገባ ችሏል፡፡ በጥንታዊ ግብፅ በጥንታዊት ታዋቂዉ የኑቢያ መንግስት አስተዳደር ስር ያስገባው **25ኛ ስርወ መንግስት** ተብሎ ይጠራል፡፡ በመጨረሻም አሲሪያኖች ግብፅን በወረሩበት ጊዜ ጥንታዊት ኑቢያኖችም ግብፅን ለቀው በመውጣት ወደ ደቡብ ተመልሰዋል፡፡

በመቀጠልም የኑቢያ መንግስት እሰከ **አትባራ** ወንዝ ተፋሰስ ግዛቱን አስፋፍቷል፡፡ ነገር ግን የክርስትናና እስልምና ሀይማኖት በአካባቢው መስፋፋት ለኑቢያ መንግስት መዳከመና መውደቅ ምክንያት ሆኗል፡፡

**መልመጃ 5፡2**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. ለኑቢያ መንግስት መውደቅ ምክንያት የሆነው በመለየት ግለጽ?
2. የጥንታዊ ኑቢያ መንግስት ምጣኔ ሀብት መሰረት ምን ነበር?
3. 25ኛዉ የኑቢያ ስርወ መንግስታት ጥንታዊ ግብፅን በሚያስተዳደርበት ዘመን ለምን ኩሻዊ አስተዳደር ተብሎ ሊጠራ ቻለ?
4. የጥንታዊ ኑቢያና የግብፅ ስልጣኔዎች ያላቸውን ትስስር ግለጽ/ጪ?

## 5.3 ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የጥንታዊት ሜሮኤ ስልጣኔ መመስረት ልዩ የሚያደረገው ምንድነው?
2. ጥንታዊት ሜሮኤ የምትታወቅበትን ስልጣኔዎች አብራራ/ሪ፡፡

የጥንታዊት ሜሮኤ ህዝቦች ከ1000-730 ዓ.ዓ በጥንታዊ ኑቢያ ውስጥ ይኖሩ ነበር፡፡ ጥንታዊ የሜሮኤ ነገስታት የኩሽ መንግስት በመባልም እንደሚታወቁ የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ በጥንታዊ ግብፅ መስፋፋት ምክንያት ሜሮኤዎች እንደ ኑቢያኖች ለዘመናት በግብፆች አስተዳደር ስር ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን ከኑቢያኖች ጋር በመሆን ከ730 ዓ.ዓ ጀምሮ ሜሮኤዎች የፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብት የበላይነትን በመቆጣጠር ለ60 አመታት ጥንታዊ ግብፆችን አስተዳድረዋል፡፡


የጥንታዊት ኑቢያና ሜሮኤ ህዝቦች አንድ መሆናቸውን የሚገልፅ መረጃ ባይኖርም ሁለቱ ህዝቦች በአሲርያኖች ወረራ ምክንያት ወደ ደቡብ (የአሁኑ ሱዳን ሪፐብሊክ) አብረው እንደተመለሱ ይገልፃሉ፡፡ በ593 ዓ.ዓ ከነበሩበት ርቀው በመሄድ መዲናቸውን ወደ ሜሮኤ ቀይረዋል፡፡

**ጥንታዊ ሜሮኤ ከጥንታዊ ግብፆች በስተ ደቡብ በጣም ርቀው አዲስ ማዕከል ያቋቋሙበት ምክንያቶች እንደሚከተለው ተገልጿል፡**

- **ከጥንታዊት ግብፆች ጫና ለመሸሽና**
- **ለሰው ልጅ ኑሮ ምቹ የሆነ የአየር ንብረት ፍለጋ ነዉ፡፡ ከቆላማው ሰሜን አካባቢ ክፍል ወደ ሳቫና ደን ያለበት ደቡብባዊው ክፍል መስደድ የምጣኔ ሀብት ጠቀሜታውን ስለ ተረዱ ነበር፡፡**

**የጥንታዊት ሜሮኤ ህዝቦች በብረታ ብረት ስራ፣ በሸክላ ስራ ፣ በእንጨት ስራ እና የተለያዩ ቅርጻ ቅርጾችን በመሰራት ይታወቃሉ፡፡ በተለይም ብረታ ብረቶችን በማቅለጥ ቢላዋ፣ ጦር እና የተለያዩ ስለታማ መሳሪያዎችን ሰርተው ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡ ብረታ ብረትን በማቅለጥ ስራ ታዋቂ ስለሆኑ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የብረት ኢንዱስትሪ ማዕከል ተብለዉ ይጠሩ ነበር፡፡ የተለያዩ የታሪክ ቅርሶችም ይሄንኑ ያረጋግጣሉ፡፡**

**በተጨማሪም ጥንታዊ የሜሮኤ ህዝቦች በከብቶች እርባታና በንግድ ስራ ከጥንታዊት ግብፅና ኑቢያ ጋር ግንኙነት ነበራቸው፡፡ እንዲሁም ከአክሱምና ከቀይ ባህረ አከባቢ ካሉት ህዝቦች ጋር ንግድ ሲያካሄዱ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ ንግድ ስራም ከፍተኛ ገቢ አግኝቷል፡፡**





ሥዕል 5፡3(ሀ)ከጥንታዊ የሜሮኤ ፒራሚዶችና  በከፊል

ጥንታዊ ሜሮኤዎች ፒራሚዶችን በመስራት፣ የተለያዩ ቅረፃ ቀርጾችን በመስራት፣ ቀለማትን በመቀባት ይታወቁ ነበር፡፡ ከጥንታዊ የግብፅ መንግስታት ጋር ካላቸው ጠንካራ ግንኙነት የተነሳም የግብፆችን ስልጣኔ ከራሳቸው ስልጣኔ ጋር በማዋሃድ ሲገለገሉበት ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ ሀይማኖትዊ አመለካከቶችን ፣ የአስተዳደር ስርዓት፣ የእደጥበብ ስራ፣ የቅርፃቅርፆች ስራ እና የፒራሚዶች ግንባታ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የንግድ መስመርን ለመቆጣጠር ሲል የአክሱም መንገግስት ንጉስ ኢዛና እና ጥንታዊ ሜሮኤ ትልቅ ፉክክር ዉስጥ ገብተዉ ነበር፡፡ በመጨረሻም በአክሱም መንገግስት ወራራ ምክንያት በ350 ዓ.ም ሜርኤ ልትጠፋ ችላለች፡፡

**መልመጃ 5 3**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. የጥንታዊ ሜሮኤና ኑቢያ ስልጣኔዎች ግንኙነት አብራራ/ሪ፡፡
2. ጥንታዊ ሜሮኤ የምትታወቅበት ስልጣኔ ምን ተብሎ ይጠራ ነበር?
3. ጥንታዊ የሜሮኤና ኑቢያ ስልጣኔዎች የምጣኔ ሀብት መሰረት የሆነውን ግለፅ/ጪ
4. ጥንታዊ የሜሮኤና ግብፅ ስልጣኔዎች ግንኙነት ዘርዝር/ሪ፡፡

## ማጠቃለያ

በሰሜንና ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ታዋቂ ከሆኑት የጥንት ስልጣኔዎች መካከል የግብፅ፣ ኑቢያ እና ሜሮኤ ዋናዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ቀዳሚ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ከ7ኛው ዓ.ዓ ጀምሮ በአሲሪያኖች፣ ፔርሺያኖች፣ ግርኮች እና ሮማዊያኖች ወረራ ምክንያት ሊውደቅ ችሏል፡፡

የጥንታዊት ኑቢያ ስልጣኔ የተመሠረተዉ በአሁኑ ሰሜን ምስራቅ የሱዳን ሪፑብልክ አከባቢ ነው፡፡ ጥንታዊ የግብፅ መንግስት በ1500 ዓ.ዓ ኑቢያኖችን በኃይል ወሯል፡፡ በዚህ ምክንያት የኑቢያ መንግስት በጥንታዊ ግብፅ ስር ለመተዳደር ተገዷል፡፡ ይሁን እንጂ ጥንታዊ የግብፅ መንግስት ቀስ በቀስ እየተዳከም በመሄድ ኑቢያኖች በ1100 ዓ.ዓ ከጥንታዊ የግብፅ መንግስት እራሳቸውን መልሰው ነፃ በማወጣት በተራቸው ግብጾችን ማስተዳደር ችለዋል፡፡ ነገር ግን አሲሪያኖች ግብፅን በወረሩበት ጊዜ ኑቢያኖች ግብፅን ለቀው በመውጣት ወደ ደቡብ በመመለስ አዲስ መንግስት አዋቅረዋል፡፡

ጥንታዊ ሜሮኤ ከጥንታዊ የግብፅ መንግስት ጋር ካላቸው ጠንካራ ግንኙነት የግብፆችን ስልጣኔ ከራሳቸው ስልጣኔ ጋር በማዋሃድ ሲገለገሉበት ቆይዋል፡፡ በ350 ዓ.ም ግን በአክሱም መንገግስት ንጉስ ኢዛና ወራራ አማካኝነት ጥንታዊ ሜሮኤ ልትጠፋ ችላለች፡፡

## የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ክፍል.I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥት ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ መልስ/ሽ

1. በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ማዕከል በመባል የምትታወቀው የቷ ናት?

   ሀ.ግብፅ ለ. አክሱም ሐ. ሜሮኤ መ.ኑቢያ

2. ለጥንት ግብፃውያን መንግስት ውድቀት ምክንያት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የአሲርያኖች ወረራ ለ.የግሪኮች ወረራ

   ሐ. የሮማኖች ወረራ መ.ሁሉም መልስ ነው

3. ጥንታዊ የግብፅ መንግስትና ኑቢያ ያላቸው ግንኙነት በይበልጥ ምን ላይ ያተኮረ ነበር ?

   ሀ. ንግድ ለ. ባህል ሐ. ፖለቲካ መ. ሁሉም መልስ ነው

4. በ350 የሜሮኤን ስልጣኔ በመውረር ያስወደቀው የቱ ነው?

   ሀ.ኑቢያ ለ. አክሱም ሐ.ግብፅ መ. ኩሽ

5. የጥንታዊ ግብፅ ስልጣኔ ውጤት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ሂሮግሎፊክስ ለ.ፒራሚዶች

   ሐ.የሙሚፊኬሽን ስራ መ.ሁሉም መልስ ነው

**ክፍል II ፡በ "ለ" ስር ያለውን ምርጫ ከ "ሀ" ስር ካሉት ጥያቀየቄዎች ጋር አዛምድ/ጅ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጥንታዊ የኑቢያ ስልጣኔ | ሀ. በአክሱም መንግስት ወደመ |
| 2. ጥንታዊ የግብፅ ስልጣኔ | ለ. በአሲሪያኖች ቁጥጥር ስር ዋለ |
| 3. ጥንታዊ የሜሮኤ ስልጣኔ | ሐ. የኩሽ ስልጣኔ |
| 4. የግብርና ዘርፍ | መ. ግዢ እና ሽያጭ |
| 5. የንግድ ዘርፍ | ሠ. የእንስሳት እርባታ |
| | ረ. አዱሊስ |

**ክፍል III ፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ፡:**

1. የጥንታዊ ግብፅና ሜሮኤ ስልጣኔዎች ውጤቶችን በማነጻፀር ተንትን/ኚ
2. የጥንታዊ ግብፅ መንግስት አገዛዝ ዘመን ክፍፍሎችን ፃፍ/ፊ፡፡

# ምዕራፍ 6

# ጥንታዊና የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና ህዝቦች ታሪክ

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች፤**

- የኢትዮጵያን ጥንታዊ የሥልጣኔ መገለጫዎችን ትዘረዝራለህ/ለሽ
- የአክሱምና ዛጉዌ የጥንት ሥልጣኔ ታሪክ በመገንዘብ ታደንቃለህ/ሽ
- የኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች አነሳስና መስፋፋትን ታብራራለህ/ሽ
- የጐንደር ታሪካዊ ሁኔታዎችን በመገንዘብ ታደንቃለህ/ሽ
- የኢትዮጵያ የጥንትና መካከለኛው ዘመን ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ በመገንዘብ ተሳትፎህን/ሽን ታዳብራለህ/ሽ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ታሪክ ከተከናወነበት ጊዜ አንፃር ሲታይ በሶስት ደረጃ ይከፈላል፡፡ እነዚህም ጥንታዊ፣ መካከለኛ እና ዘመናዊ ታሪክ በመባል ይታወቃሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የጥንታዊና መካከለኛ ዘመን ታሪክ በአጭሩ ትማራለህ/ሽ፡፡ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚባለው መንግሥት ከተመሠረተበት እስከ 1270 ዓ.ም ያለው ጊዜ ማለት ነው፡፡ የአክሱምና የዛጉዌ መንግሥታት አመሠራረት በዚሁ በጥንታዊ ታሪክ

ዘመን ውስጥ ይካትታል፡፡ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ ደግሞ ከ1270 ዓ.ም እስከ 1855 ዓ.ም ድረስ ያለውን ያካተተ ነው፡፡ በዚህ መካከለኛ ዘመን ታሪክ ደግሞ የተለያዩ የኢትዮጵያ ህዝቦች የበላይነትን ለመያዝ ሲፎካከሩ የነበሩበትን ክፍለ ዘመን ታሪክ የያዘ ነው፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባ የትምህርት ብቃት፤**

- ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ታሪክ ትገልፃለህ/ሽ፣
- የኢትዮጵያን ጥንታዊና መካከለኛ የማህበራዊ፣ ፓለቲካዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎችን ታብራራለህ/ለሽ
- የኢትዮጵያ ህዝቦች ግንኙነትና ትስስር ሁኔታዎችን ትተነትናለህ/ሽ
- ግብርና፣ ንግድ እና የተለያዩ ገቢዎች በአገሪቷ ምጣኔ ሀብት ውስጥ ያላቸውን አስተዋፅኦ ትገልፃለህ/ሽ


## 6.1. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥት

### 6.1.1. የአክሱም መንግሥት

ጥንታዊ የአክሱም ሥልጣኔ የተመሰረተው በሰሜን ኢትዮጵያ በ100 ዓ.ዓ አከባቢ ነው፡፡ የአክሱም መንግሥት አስተዳደር ድንበር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመስፋፋት የአክሱም መንግሥት ግዛቱን አጠናክሯል፡፡ ከ4ኛ እስከ 7ኛ ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግስት ድንበሩን ወደ ተለያየ አቅጣጫ አስፋፍቶ ነበር፡፡ በዚሁ መሠረት በስሜን አቅጣጫ እስከ ኤርትራ፣ በደቡብ አቅጣጫ እስከ ሰሜን ሸዋ፣ በስተምዕራብ አቅጣጫ እስከ አባይ ሸለቆ፣ በስተምስራቅ በኩል ደግሞ እስከ ቀይባህር ይደርስ ነበር፡፡

በንጉሥ ኢዛና ዘመን መንግሥት የአክሱም መንግሥት አስተዳደር በስተ ምዕራብ አቅጣጫ እስከ ሜሮኤ መንግሥት ደርሶ ነበር፡፡ እንዲሁም በተለይ በንጉሥ ካሌብ ዘመነ መንግሥት የአክሱም

መንግሥት ድንበር ሰፍቶ ቀይ ባህርን ተሻግሮ እስከ ደቡብ ምሥራቅ አረቢያ ድረስ እንደተስፋፋ ይታወቃ፡፡




ካርታ. 6 :1. የጥንታዊ አክሱም መገኛና የንግድ መስመሮች

የአክሱም መንግሥት ምጣኔ ሀብት የተመሰረተው በግብርናና በንግድ ሥራ ላይ ነበር፡፡ ከ4ኛው እስከ 7ኛው ዓ.ም ክፍለ ዘመን የአክሱም መንግሥት በሃይማኖት፣ በትምህርት እና በንግድ ስራ ይታወቅ ነበር፡፡ በቀይ ባህር አካባቢ የሚገኝ የአክሱም ወደብ **አዱሊስ** ይባላል፡፡ አክሱም ወደ ቀይ ባህር ቀረብ ብላ ከመገኘቷ የተነሳ ከህንድና ከሜዲትራኒያ አገሮች እንደ ሶሪያ፣ ግብፅ ሮም እና ባይዛንታየን ጋር ሰፊ የንግድና የፖሊተካ ግንኙነት ነበራት፡፡ ወደ ውጭ ሲላኩ ከነበሩት የንግድ የሸቀጥ አይነቶች ወርቅ፣ የዝሆን ጥርስ፣ እጣን፣ የግብርና ውጤቶች ቅመማቅመም እና የተለያዩ እንስሳቶች ዋናዋናዎቹ ሲሆኑ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ የነበሩት ደግሞ አልባሳት፣ የጦር መሳሪያዎች፣ የተለያዩ

የአልኮል መጠጦች፤ሽቶዎች እና የተለያዩ የቤት ዕቃዎች ናቸው፡፡

የጥንታዊ አክሱም ህብረተሰብ በተለያዩ የአስተዳደር መዋቅሮች የተከፈሉ ነበሩ፡፡ እነዚህ የአስተዳደር መዋቅሮች የላይኛው መደብ፣ መካከለኛው መደብ እና የታችኛው መደብ በመባል ይታወቃሉ፡፡ የላይኛው መደብ አባላት፤ የመንግስት ባለስልጣንና የሃይማኖት አባቶች ሲሆኑ የመካከለኛ መደብ ደግሞ አርሶ አደሮች፣ የተለያዩ የዕድ ጥበብ ሰራተኞች እና ነጋዴዎች ናቸው፡፡ የታችኛው መደብ ባሮች ተብለው የሚጠሩ ወይም መብትና ነጻነት የተነፈጉ የህብረተሰብ ክፍሎች ነበሩ፡፡

ከአክሱም ሥልጣኔ መገለጫዎች ታዋቂዎቹ የቅርፃ ቅርፆች ስራ፣ ስነ ህንፃ፣ ስነ ፅሑፍ፣ ሃይማኖት እና ንግድ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሥልጣኔዎች ውስጥ ታዋቂዉ አንዱ የአክሱም ሀውልት ነው፡፡ ከዚህም ሌላ የተለያዩ ትላልቅ የአምልኮ ቤቶች እና የቤተመንግስት ሕንፃዎች ተገንብተዋል ፡፡



*ሥዕል 6.1(ሀ) ጥንታዊ የአክሱም ሀውልት*

**የፕሮጅክት ስራ**

የሚከተለውን ጥያቄ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ

- በቡድን በመደራጀት በሥዕል 6.1(ሀ) ላይ የሚታየዉን ጥንታዊ የአክሱም ሀውልትን በአከባቢያችሁ የሚገኙትን ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሰርታችሁ አቅረቡ፡፡

ጥንታዊ የአክሱም መንግስት የራሱ የሆነ ስነ-ጽሑፍ ነበረው፡፡ ለረዥም ጊዜ የአክሱም መንግስት የሳባን ፊደል በመጠቀም **በግዕዝ** ቋንቋ በመፃፍ የስራ ቋንቋ አድረጎ ሲጠቀምበት ቆይቷል፡፡ የአክሱም መንግስት የራሱ

የሆነ ሳንቲም ከወርቅ፣ ከብር እና ከነሀስ በመቅረጽ የንግድ እንቅስቃሴን በማካሄድ ይታወቃል፡፡



ሥዕል 6.1(ለ) ጥንታዊ የአክሱም መንግሥት ሳንቲሞች

ከ8ኛው እስከ 12ኛው ክፍለ ዘመን በአክሱም መንግሥት ታሪክ ውስጥ የጨለማ ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ሊባል የቻለበት ዋናው ምክንያት በዚያን ዘመን ስለ አክሱም መንግሥታት ምንም የሚታወቅ ተጨባጭ መረጃ ባለማኖሩ ነው፡፡ በተጨማሪም የአክሱም የፖለቲካና ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ መውደቅ እንዲሁም የውጭ ሀገር ግንኙነት መላላት ናቸው፡፡

የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች እነደሚገልጹት የአክሱም መንግሥት ሊወድቅ የቻለበት ምክንያት የአገር የውስጥ ችግር እና የውጭ ተፅዕኖ ነበር፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤

- የአገር ውስጥ ችግር የምንለው የአየር ፀባይ መለወጥ፣ የቤጃ ህዝብ አመፅ እና ነገስታት ስልጣን ለመያዝ እርስ በእርስ ያደረጉት ፉክክሮች ሲሆኑ
- የውጭ ተፅዕኖ የሚባለው ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት በአረቢያ ውስጥ በመስፋፋትተቱ ምክንያት የቀይ ባህር አካባቢ የንግድ መስመር በአረቦች ቁጥጥር ስር መውደቁና የአክሱም መንግሥት የውጭ ግንኙነት መቋረጥ ነው፡፡ የአክሱም መንግሥት የንግድ ወደብ አዱሊስ በአረቦች በመውደሙ የአክሱም መንግሥት እንዲወድቅ አድርጎታል፡፡ በአጠቃላይ የአክሱም መንግሥት በአገር ውስጥ ችግር እና በውጭ ተፅዕኖ በ1150 ወድቋል፡፡

## 6.1.2. የዛጉዌ "ዘአገው" መንግሥት(1150- 1270 ዓ.ም)


### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የዛጉዌን መንግስትና የላሊበላን ከተማ ግንኙነት ግለጥ/ጭ
2. የዛጉዌን ግዛት ከጥንታዊ የአክሱም ከተማ በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?
3. የዛጉዌ መንግስት አመሰራረት ሂደት በቡን በመሆን ተወያዩበት

የዛጉዌ መንግሥት የተመሠረተው ከአክሱም በስተሰሜን በ1150 ዓ.ም ነው፡፡ የዛጉዌ ሥረወ መንግሥትን ያቋቋመው **መራ ተክለሃይማኖት** ይባላል፡፡ መራ ተክለሃይማኖት በአክሱም አስተዳደር ውስጥ በከፍተኛ ቦታ ተሹሞ ሲያገለግል ነበር፡፡ ነገር ግን የአክሱም የመጨረሻ ንጉስ የነበረውን ድልናዖድ በማሸነፍ የዛጉዌ ሥረወ መንግሥትን መሰረተ፡፡ የዛጉዌ ዋና ከተማ **ሮሃ ወይም አዳፋ** ይባላል፡፡ እሱም በሰሜን ወሎ

በላስታ አውራጃ ቡግና በመባል በሚታወቀው ቦታ ነው፡፡ የዛጉዌ ሥረወ መንግሥት ግዛት በስተሰሜን የቀድሞ አክሱም መንግሥት ግዛት፣ አብዛኛውን ክፍል ያካተተ ነው፡፡ በስተ ደቡብ ሰሜን ሸዋ፣ ወሎ (ሐይቅ አካባቢ) እና ሰሜን ምዕራብ ጎጃም ነበሩ፡፡ የዛጉዌ ነገስታት መንግስት የአክሱም መንግስት ስልጣኔ እና ሀይማኖትን አስቀጥለዋል፡፡

የዛጉዌ መንግስት ምጣኔ ሀብት እንደ አክሱም መንግስታት በግብርናና ንግድ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ የዛጉዌ ነገሥታት ከምሥራቅ ሜዲቴራንያን አካባቢ አገሮች ጋር የንግድና የባህል ትስስርም ነበራቸው፡፡ የዛጉዌ ነገሥታት እንደነ ገብረመስቀል፣ ይማነክርስቶስ፣ ሐርቤ፣ ላሊበላ እና ይተባረክ ተዋቂዎቹ ነበሩ፡፡ እነዚህ ነገሥታት አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ይታወቃሉ፡፡ በተለይ ንጉሥ ላሊበላ (1181- 1221 ዓ.ም) አስራ አንድ ውቅር አብያተ ክርስቲያን ወጥ ከሆነ ድንጋይ አሰርቷል፡ ይህም አስራ አንድ የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት በ1978 በአለም የቅርስ መዝገብ (UNESCO) ላይ ተመዝግቧል፡፡ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የቱሪዝም ማዕከል በመሆን እያገለገለ ነው፡፡



ሥዕል. 6.1.2.(ሀ) የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያ ዉስጥ አንዱ

ይሁን እንጂ በዛጉዌ የገዢ ቤተሰብ አባላት መካከል የነበረው የእርስበርስ ሽኩቻ ለዛጉዌ መንግሥት መውደቅ ዋነኛው ምክንያት ሆኗል ፡፡ በዛጉዌ ነገሥታት መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ነበር፡፡ በ1270 ዓ.ም **ተሰፋ ኢየሱስ** የሚባል ሰው ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የመጨረሻውን የዛጉዌ ንጉስ **ይትባረክን** ድል አድርጎ ሥልጣኑን ተቆጣጠረ፡፡ **ተሰፋ ኢየሱስ** በሰሜን ሸዋ እና በአማራ ድጋፍ የዛግወዌን መንግስትን በመጣል ሥልጣን ሊይዝ ችሏል፡፡ ከዚህ በኋላ እራሱን **ይኩኖአምላክ** በሚል የንግስና ስም ንጉሥ በመሆን የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥትን መልሶ አቋቁሟል፡፡

## 6.1.3. የጎንደር ከተማ

ጎንደር የተመሰረተችው በ1636 በንጉስ ፋሲሊደስ ነው፡፡ ለረጅም ጊዜ ጎንደር ከተማ የአስተዳደር ማዕከል በመሆን እስከ 1850 ስታገለግል ቆይታለች፡፡ የጎንደር ነገስታት ጎንደርን የአስተዳደር ማዕከል በማድረግ ቤተመንግስት፣ ቤተክርስቲያኖችን እና የሹማምንቶችን ቤቶች ገንብተው ነበር፡፡ የጎንደር ስነ-ህንጻ ግንባታ ከአክሱምና ከላሊበላ ጋር ተመሳሳይነት ነበረው፡፡



6.1.3.(ሀ) የንጉስ ፋሲለደስ ቤት መንግስት

የጎንደር ስልጣኔ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰው በንጉስ ፋሲሊደስ (1632-1667)፣ ዮሐንስ(1632-1667) እና ቀዳማዊ ኢያሱ (1632-1667) ዘመነ መንግስት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ጎንደር በሀይማኖት ትምህርት ማዕከልነትና ቤተክርሰቲያኖችን በማነጽ ትታወቅ ነበር፡፡ ጎንደር በስነ-

ህንጻ ግንባታ ጥበብ ከምትታወቅበት ስልጣኔዎች ውስጥ አንዱ የፋሲሊደስ ቤት መንግስት አንዱ ነው፡፡ ይህ የፋሲለደስ ቤተመንግስት በ1979 ዓ.ም በአለም የቅርስ መዝገብ (UNESCO)ላይ ተመዝገቧል፡፡ እንዲሁም በአሁኑ ወቅት የቱሪዝም ማዕከል በመሆን እያገለገለ ነው፡፡

የጎንደር ከተማ የተመሰረተችው ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በሚወስደው የንግድ መስመር ላይ ነው፡፡ ከደቡብ ኢትዮጵያ ወደ መተማ፣ አድዋ እና ምፅዋ የሚወስዱት የንግድ መስመሮች ጎንደርን አቋርጠው ያልፋሉ፡፡ ጎንደር በዚህ የንግድ መስመር ላይ መመስረቷ የንግድ ማዕከል እንድትሆን አድርጧል፡፡

የጎንደር ከተማ የተለያዩ ሀገር ዜጎች፣ የሀይማኖት ተከታዮች እና የተለያየ ማንነት ያላቸው ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ ነበረች፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ **የሙስሊም** ማህበረሰብ ሲሆኑ እነሱም በንግድ ስራ ላይ በመሰማራት ይታወቃሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ **ፈላሻዎች** ሲሆኑ በሸክላ ስራ፣ በእንጨት ስራ እና በብረታ ብረት ስራ ይታወቃሉ፡፡

ይሁን እንጂ ከጊዜ በኃላ ጎንደር የማህበራዊ፣ፖሊቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ማዕከል ሆና ልትቀጥል አልቻለችም፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያት የሆነው በጎንደር ነገስታት መካከል የተካሄደው የእርስበርስ የሥልጣን ሽኩቻና የጦር አበጋዞች እየጠነከሩ መምጣታቸው ነው፡፡ ይህ የሥልጣን ሽኩቻ በጎንደር ከተማ ሰላምና መረጋት እንደይኖር በማድረጉ በ1850 ዎቹ የጎንደር መንግስት ሊንኮታኮት ችሏል፡፡

**መልመጃ 6፡1**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. ከአክሱም ሥልጣኔ ውጤቶች ውስጥ ሶስቱን ግለጽ/ጪ
2. የአክሱም፣ የዛግዌ እና የጎንደር ምጣኔ ሀብት መሰረት ምንድነው?
3. የአክሱምና የዛግዌ መንግስት የንግድ ወደብ የሆኑትን በማነፃፀር ግለጽ/ጪ?
4. የአክሱም፣ የዛግዌ እና የጎንደር ማህበራዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነት ግለጽ/ጪ?
5. ስለ ጎንደር ስልጣኔ አጀማመርና አወዳደቅ አብራራ/ሪ

## 6.2 የኢትዮጵያ ሙሰሊም ሱልጣኔቶች

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. ሱልጣኔት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በኢትዮጵያ የሙሰሊም ሱልጣኔቶች እንዴት እንደ ተመረቱ ግለጽ/ጪ?

ሱልጣኔት ማለት የአንድ አከባቢ የአስተዳደር ድንበር ሆኖ በሱልጣኖች የሚመራ ማለት ነው፡፡ የተለያዩ የታሪክ መረጃዎች እንደሚገልፁት ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሙስሊም ሱልጣኔቶች በምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ ተመስርተዋል፡፡ እነሱም ሸዋ፣ ኢፋት፣ ፈጣጋር፣ ዳዋሮ፣ ባሊ፣ የአዳል እና የመሳሰሉት የሙስሊም ሱልጣኔቶች ናቸው፡፡

**የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔ፤** የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔት ከኢትዮጵያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች ውስጥ ቀዳሚው ነው፡፡ የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔትን ማክዙማይት በመባልም ይታወቃል፡፡ ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ማክዙሚ የሚባል ቤተሰብ ከአረቢያ አካባቢ በመፍለስ ወደ ሸዋ መጥተው የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔትን መስርተዋል፡፡ የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔት በአከባቢው ካሉት ሙስሊም ሱልጣኔቶች ጋር የተለያዩ ጦርነቶችን አካሂደ‹ል፡፡ ካደረጉት ጦርነት ውስጥ አንዱ ከኢፋት ጋር ለረጅም ጊዜ ያካሄዱ ጦርነት ዋነኛው ነው፡፡ በመሆኑም በ13ኛው ክፍለ ዘመን የሸዋ ሙስሊም ሱልጣኔት በኢፋት በመሸነፉ የኢፋት አስዳደር ስር ወድቋል፡፡


**የኢፋትና አዳል ሙስሊም ሱልጣኔቶች፤** የኢፋትና የአዳል ሙስሊም ሱልጣኔቶች ታሪካዊ ትስስር ነበራቸው፡፡ የኢፋት ሱልጣኔት በ1285 ዓ.ም **ኡመር ወላስማ** በሚባለው ሱልጣን በምስራቅ ሸዋ ተመሰረተ፡፡ የዚህ ሱለጣኔት ስም **ወላስማ** በመባልም ይታወቅ ነበር፡፡ የኢፋት ሱልጣኔት በ13ኛውና በ14ኛው ክፍለ ዘመን በምስራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሱልጣኔቶች ሁሉ ጠንካራ ነበር፡፡

የኢፋት ሱልጣኔት ምጣኔ ሀብት ከዘይላ የንግድ መስመር አከባቢው ከሚገኙ ህዝቦች የሚሰበሰብ ቀረጥና ግብር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ግዛትን የማስፋፋትና የንግድ መሥመሮችን ዘይላን ጨምሮ የመቆጣጠር ፍላጎት በክርስትያን ነገሥታትና በኢፋት መካከል ጦርነት እንዲፈጥር አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት ኢፋት የአስተዳደር ማዕከሉን ዳካር ወደ ተባለው የምስራቅ ኢትዮጵያ አከባቢ ካዛወረ በኋላ በ15ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከበቢ አዳል የሚባል የሙስሊም ሱልጣኔት መስርቷል፡፡

**የአዳል ሱልጣኔት፤** በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግስትና የሙስሊም ሱለጣኔቶች መካከል የነበረዉ ግጭት እየተካረረ በመምጣቱ ፖርቹጋልና ኦቶማን ቱርኮች በቀጥታ በጦርነቱ ተሳትፈዋል፡፡ የእነዚህ የውጭ አገራት ጣልቃ ገብነትና ድብቅ ፍላጎትም የቀይ ባህር አከባቢ ያለዉን የንግድ መስመር መቆጣጠር ነበር፡፡

በ1529 በኢትዮጵያ የክርስቲያን መንግስትና በአዳል መካከል በተደረገው ጦርነት በአህመድ ኢብን ኢብረሂም አሊ.ጋዚ (አህመድ ግራኝ) የሚመራ ጦር በኦቶማኖች ድጋፍ ሽምብራ ኩሬ ጦርሜዳ ላይ የክርስቲያን መንግስት ጦር አሸንፏል፡፡

በዚህ መሰረት ከ1529 እስከ 1543 የክርስቲያን መንግስትን አስተዳደር በመቆጣጠር የሙስሊም አስተዳደር የፖለቲካ የበላየነቱን ተረከቦ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የክርስቲያን መንግስት በንጉስ ገላውዲዎስ መሪነትና በፖርቹጋል እገዛ ሀይሉን በማጠናከር በ1543 በወይናደጋ ጦርሜዳ በማሸነፉ ስልጣኑን መልሶ ሊቆጣጠር ችሏል፡፡




ካርታ 6.2 የኢትዮጵያ ሙሰሊም ሱልጣኔቶች መስፋፋት

## 6.3 የህዝቦች ግንኙነት፣ትስስር እና እንቅስቃሴ

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የህዝቦች እንቅስቃሴና መሰፋፋት ማለት ምን ማለት ነው? በቡድን ተወያዩበት፡፡
2. የህዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያቶች ምንድናቸው?
3. የህዝቦች እንቅስቃሴ ጥቅምና ጉዳቶች ምንድ ናቸው?

የኢትዮጵያ ብሄር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ በተለያዩ ምክንያቶች እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በኢትዮጵያ ከተደረጉት የህዝብ እንቅስቃሴዎች ዋና ዋናዎቹ የአፋር፣ የሀረሪ፣ አርጎባ፣ ሶማሌ እና የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡ ለህዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያት የሆኑት ማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና የተፈጥሮ ችግሮች ናቸው፡፡ ህዝቦች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያደረጉት እንቅስቃሴ የባህል፣ የሀይማኖት፣ የማህበራዊ ህይወትና የተለያዩ እሴቶች ትስስር እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

### 6.3.1. የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ

የኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴ በአጭር ጊዜ ውስጥ የተካሄደ አልነበረም፡፡ በ1522 ሁለቱ የኦሮሞ ፊደሬሽኖች፤ ቦረናና ባሬንቱ በሁለት አቅታጫ በመንቀሳቀስ በአሁኑ ጊዜ ወደ አሉበት አካባቢ መንቀሳቀስ ችለዋል፡፡ የቦረና ፊደሬሽን ወደ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ አቅጣጫ በመንቀሳቀስ የአሁኑን ኦሮሚያ ዞኖች እንደ ቦረና፣ ጉጂ፣ ወለጋ፣ ኢሉአባቦር፣ ጂማ እና ሸዋ ሰፍረዋል፡፡ የባሬንቱ ፊደሬሽን ደግሞ ወደ ደቡብ ምስራቅና ምስራቅ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡በዚህ ሁኔታ የባሬንቱ ፊደሬሽን እንደ አርሲ፣ ሀረርጌ፣ ወሎ እና ባሌ አካባቢ ሰፈሩ፡፡

በአጠቃላይ ሁለቱም ፌደሬሽኖች የሁለቱ ማዕከል (ጨፌ) ከሆነው **መደ ወላቡ** በቅርበትና ርቀው በመሄድ አዳዲስ ማዕከላትን መስርተዋል፡፡እነሱም ኦዳ ነቤ፣ ኦዳ ቢሲል፣ ኦዳ ቡሉቅ እና ኦዳ ገራዶ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ማዕከላት የኦሮሞ ሕዝብ ባለበት አካባቢው የገዳ ስርዓትን እንዲያካሄዱ ትልቅ አሰተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ ይሁን እነጂ በየስምንት አመቱ ከተለያዩ ማዕከላት አባላት **መደ ወላቡ** ላይ በመሰብሰብ የተለያዩ ህግና ደንቦችን በማውጣትና በማሻሻል ለዘመናት ወጥ በሆነ የገዳ ህግ ስተዳደሩ ቆይተዋል ፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴ ሲጀምር የኦሮሞ ሕዝብ በገዳ ስርዓት በመደራጅታቸው ስኬታማ እንቅስቃሴ አድርገው ነበር፡፡ የገዳ ስርዓት አደረጃጀት ፖሊቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ወታደራዊ፣ ሀይማኖታዊና ማህበራዊ አደረጃጀትን ያካትታል፡፡ ይህ አደረጃጀት የኦሮሞ ሕዝብ እንቅስቃሴ ባደረገበት ወቅት መልካም ስነ ምግባር እንዲሁም መልካም ስብእና እንዲኖረው አደርጎታል፡፡ ለምሳሌ በጦርነት ወቅት ሞጋሳንና ጉዲፈቻን በመጠቀም የሴቶችንና የህጻናትን ሰብአዊ መብት እንዲሁም ኦሮሞ ያልሆኑ ዜጎችን መብት ማክበር ናቸው፡፡

## የኦሮሞ ገዳ ስርዓት

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የገዳ ስርዓት ለኦሮሞ ሕዝብ ምንድነው?
2. የገዳ ስርዓት አደረጃጀት ምን ምንን ያካትታል?
3. የገዳ ስርዓት አደረጃጀት እና አወቃቀር ላይ አጭር ውይይት አድርጉ፡፡

የኦሮሞ ገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው፡፡እንዲሁም የተለያዩ አደረጃጀትና አወቃቀር ያቀፈ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የገዳ ስርዓት አደረጃጀት ፖሊቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ወታደራዊ ፣ ሀይማኖታዊ እና ማህበራዊ አደረጃጀትን ያካትታል፡፡ በገዳ ስርዓት ውስጥ ሁሉም ክንውኖች የኦሮሞን ህዝብ ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ቱፊት ጠብቆ ይከናወናሉ፡፡



6.3 ሥዕል (ሀ) ከገዳ ስርዓት ዉስጥ የምክክር ስርዓት

በተጨማሪም በገዳ ስርዓት ውስጥ በዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መልኩ የስልጣን ሽግግር ይካሄዳል፡፡ በተጨማሪም በገዳ ስርዓት ውስጥ በእድሜ ታላቅነትና ታናሽነት የሚከበርበት እና የሚደጋገፍበት ሲሆን ሽማገሌዎች እና ምሁራን ደግሞ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ የገዳ ስርዓት በ2016 ዓ.ም በአለም የቅርስ መዝገብ (UNESCO) ላይ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ የገዳ ስርዓት የሰው ልጅ ለኑሮው የሚያሰፈልጉትን ነገሮች በውስጡ ያካተተ ነው፡፡

### የገዳ ስርዓት አደረጃጀትና መዋቅር

በገዳ ስርዓት ውስጥ የኦሮሞ ህዝብ በተለያዩ የገዳ አደረጃጀት ክፍሎች ውስጥ ያልፋሉ፡፡ እነሱም ደበሌ/ኢቲመኮ (0-8) ፣ ትንሹ ጋሜ (8-16) ፣ ትልቁ ጋሜ (17-24) ፣ ፎሌ/ኩሳ (25-32) ፣ ቆንዳላ/ራባ (32-40)፣ ገዳ/ሉባ(41-48)፣ 1ኛ ዩባ(49-56)፣ 2ኛ ዩባ(57-64)፣ 3ኛ ዩባ (65-72) እና 4ኛዩባ(73-80) ሲሆኑ እድሜያቸው ከ80 በላይ የሆኑት ደግሞ ጃርሳ ወይም ሽማግሌ ይባላሉ፡፡

## የገዳ ስርዓት አደረጃጀትና የስራ ድረሻ

| ተ.ቁ | መጠሪያ ስም | የስራ ድረሻ |
|---|---|---|
| 1 | ደበሌ/ሱሉዳ/ኢ.ቲመኮ | • በመኖሪያ ቤት አካበቢ አነስተኛ ስራዎችን ይሰራሉ |
| 2 | ትንሹ.ጋሜ/ሩቦ/ቀሬዱባ | • ከቤተሰብ ጋር በመሆን የተለያዩ ትምህርቶችን ይማራሉ ለምሳሌ እንደ ተረት ፣ ቀልዶች እና አባባሎች፡፡ |
| 3 | ትልቁ.ጋሜ/ፎሌ/ጀማሪ ቀሬ/ ጎበመ… | • የተለያዩ ስልጠና በመውሰድ በህብረተሰቡ ውስጥ የስራ ድርሻ ወስዶ ይሰራሉ፡፡ |
| 4 | ኩሳ/ ቆንዳላ እና ራባ | • የገዳ መተዳደሪያ ህግና ደንብን በመማር በህብረተሰቡ ውስጥ ከፍተኛውን የስራ ድርሻ በመውስድ ይሰራሉ፡፡ |
| 5 | ራባ-ዶሪ/ ሉባ… | • የተለያዩ ሀላፊነት ላይ ይሰማራሉ ለምሳሌ ህግ ማጥናት:: በተጨማሪም የትዳር ጓደኛ ማጨት ወይም ማግባት ይችላሉ |
| 6 | ገዳ/ገዶመ | • የኦሮሞን ህዝብ የማስተዳደር ሀላፊነት ይወስዳሉ፡፡ |
| 7-10 | ዩበ/ገደሞጂ … | • እንደ ምክር ምርቃት እና ልምድ ይሰጣሉ፡፡ |

### የገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ስልጣን ሽግግር

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የገዳ አስተዳደር ክፍሎች የስራ ድርሻ ልዩነትና ተመሳሳይነት ላይ ተወያዩ
2. በአከባቢያችሁ የሚገኘው የገዳ አስተዳደር(ፓርቲ) ክፍሎችን ቤተሰቦቻችሁን እና ሽማግሌዎችን በመጠየቅ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

የገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ ስልጣን ሽግግር ከዘመን ቆጠራ ጋር ይያያዛል፡፡ እነሱም ቀን፣ ወር እና አመት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡በገዳ ስርዓት ህግ የተለያዩ ፓርቲዎች ወደ ስላጣን ከመጡ በኃላ ለስምንት አመታት ብቻ ያስተዳድራሉ፡፡ከተለያዩ ፓርቲዎች ውስጥ ታዋቂ የሆኑ ሜልባ፣ ሙደና፣ ኪሎሌ፣ ቢፎሌ እና ሚቺሌ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የገዳ ዴሞክራሲያዊ ስልጣን ሽግግር በየስምንት ስምንት አመታት ቆይታ ይከናወናል፡፡ በዚህም ጊዜ በገዳ ስርዓትና ደንብ መሰረት የሚሰናዱ ዝግጅቶችና በዓላትም አሉ፡፡ እነዚህ የገዳ ፓርቲዎች ከቦታ ቦታ የተለያየ ስም አላቸው፡፡ በ6ኛ እና 7ኛ ክፍል ገዳ ትምህርት ውስጥ በስፋት ስለተገለጸ ዝርዝሩን ከመጻፉ ላይ አንብቡት፡፡

## 6.3.2 የገዳ ስርዓት አደረጃጀቶች (ተቋማት)

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. ሰለ ሲንቄ ምንነት እና ጥቅሙ ላይ በሰፋት ተወያዩበት
2. የሞጋሳ እና ጉዲፋቻ ጥቅም ላይ በዝርዝር ተወያዩበት

ከገዳ ስርዓት አደረጃጀቶች ውስጥ ታዋቂዎቹ የሲንቄ ስርዓት፣ የኢሬቻ ስርአት፣ የሙዳ ስርአት፣ ዋቄፈና፣ ጉዲፋቻ እና ሞጋሳ ስርቶች ናቸው፡፡ የሲንቄ ስርዓት የኦሮሞ ሴቶችን መብት የሚያስከብር ተቋም ነው፡፡



ሥዕል 6.3 (ለ) የሲንቄ ስርዓት

ኢሬቻ የምስጋናና ሃይማኖታዊ በዓል ሲሆን በአመት ሁለቴ ይካሄዳል፡፡ የመጀመሪያው የክረምቱ ወራት እንዳለፉ በመስከረም ወር የሚከበር ሲሆን ቀጥለው የሚከበረው ደግሞ የበጋዎቹ ወራት እንደተጠናቀቁ በበልግ ወራት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡

የዋቄፈና ሀይማኖት ትምህርት ደግሞ መሰረት የሚያደርገው በአንድ ፈጣሪ ማመን የሚል እምነት ነው፡፡ የጉዲፋቻና ሞጋሳ ስርዓቶች ኦሮሞ እና ኦሮሞ ያልሆኑ ሰዎች ከኦሮሞ ጋር የሚዛመዱበት ስርዓቶች ናቸው፡፡ የገዳ አስተዳደር የሚመራው በጨፌ አባላት ነው፡፡



ሥዕል 6፡3 (ሐ) የኢሬቻ በዓል አከባበር

## መልመጃ 6፡3

### ክፍል ١፡ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች “እውነት”ወይም “ሐሰት” በማለት መልስ/ሽ

1.የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለያዩ መንገዶች ግንኙነት አላቸው፡፡

2. ለህዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያት ከሆኑት አንዱ የምጣኔ ሀብት ጫና ነው፡፡

3.በመካከለኛው ዘመን ከተካሄዱት የህዝቦች እንቅስቃሴዎች ውስጥ በስፋት የተካሄደው የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ነው፡፡

4.የኦሮሞ ገዳ ስርዓት የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቶችን የሚያስከብር ነው፡፡

5.በኦሮሞ ገዳ ስርዓት ፖሊቲካዊ ፣ ምጣኔ ሃብታዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች የራሳቸው የሆነ ህግጋት አላቸው፡፡

**ክፍል II ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ መልስ/ሽ**

1. በኦሮሞ ገዳ ስርዓት የሴቶችን መብት በማስከበር የሚታወቀው የቱ ነው?

   ሀ. ሙዳ   ለ. ቃሉ   ሐ. ሲንቄ   መ. ኢሬቻ

2. በኦሮሞ ገዳ ስርዓት ውስጥ የማስተዳደር ኃላፊነት የሚሰጠው በየትኛው የገዳ ክፍል ነው?

   ሀ. ኩሳ   ለ.ቆንዳላ   ሐ. ዩባ   መ. ገዳ

3. ከሚከተሉት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው

   ሀ. ሀርሙፋ   ለ. ሮበሌ   ሐ. ሉባ   መ. ሆረታ

4. በኦሮሞ ገዳ ስርዓት ውስጥ ህጋዊ ዝምድናን የሚሰጥ የቱ ነው?

   ሀ. ዋቄፈና   ለ. ስልጣን ማስተላለፍ   ሐ ሞጋሳ   መ. ጂለ

## 6.4. የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች

## (ግብርና፣ ንግድ እና ግብር)

### ሀ. ግብርና

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የግብርና ስራ ምንን ያካትታል?
2. የግብርና ስራ ጥቅሞች ምንድናቸው?
3. የግብርና ስራ እንዴት እንደሚከናወን በቡድን ተወያዩበት?

ግብርና የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት መስረት ነው ፡፡ ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያ መንግስታት ከግብርና በሚያገኙት ገቢ ምጣኔ ሀብታቸውን ሲያጠናክሩ ቆይተዋል፡፡ ግብርና የእንስሳት እርባታና ሰብል ማምረትን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ መሰረት የጥንታዊ አክሱምና ዛገዌ ነገሰታት ከግብርና በሚያገኙት ገቢ ምጣኔ ሀብታቸውን ሲያጠናክሩ ቆይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ የሚታወቁ የሰብል አይነቶች

ገብስ፣ ዳጉሳ እና የቅባት እህሎች ናቸው፡፡ እነዚህ የግብርና ምርቶች ከምጣኔ ሐብት ውጭ ለጦር ኃይሎችና ለሕብረተሰቡ የምግብ ፍጆታ ይውላሉ፡፡

### ለ. ንግድ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የንግድ ስራ እንዴት ይካሄደል?
2. የንግድ ስራ ለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት የሚያስገኘውን ጥቅም በመግለጽ ተወያዩበት፡፡
3. የሀገር ውስጥ ንግድናና ከሀገር ውጪ የሚደረጉ ንግድ አንድነት እና ልዩነታቸው ላይ በስፋት ተወያዩ?

እንደ ግብርና ስራ ዘርፍ የንግድ ስራም ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ ለኢትዮጵያ መንግስታት የምጣኔ ሀብት መሰረት ሆኖ ቆይቷል፡፡ የተለያዩ መረጃዎች እደሚያመለክቱት የንግድ ስራ የገቢ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ለከተሞች መቆርቆርና ለመንግስታት መቋቋም ትልቅ አሰተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በዚህ መሰረት እንደ ኮሎኤ፣ መጠራ፣ የሃ፣ ሮሃ፣ አክሱምና ጎንደር ከተሞች መንግስታት ተቋቁመዋል፡፡

ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ ጥሬ ዕቃዎች እንደ የዝሆን ጥርስ፣ የግብርና ምርቶች ውጤት፣ ወርቅ፣ የጉማሬ ቆዳ እና የሰጎን ላባ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ የጦር መሳሪያዎች ፣ የአልኮል መጠጦች እና የተለያዩ ጌጣ ጌጦች ከውጭ ሀገር የሚገቡ ነበሩ፡፡

### ሐ.ግብር

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ግብር ማለት ምን ማለት ነው?

2. ለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት ግብር የሚያስገኘው ጥቅም ምንድነው?

ከጥንት ዘመን ጀምሮ እስከአሁን ድረስ የኢትዮጵያ መንግስታት ከግብር በሚያገኙት ገቢ ምጣኔ ሀብታቸውን ሲያጠናክሩ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ከህብረተሰቡ በተለያዩ መንገዶች ግብር ሲሰበሰብ ቆይተዋል፡፡ ከአርሶ አደሮች ላይ ግብር የሚሰበሰበው በምርት አይነት እና በገንዘብ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከነጋዴዎች የሚሰበሰብ በግብርና በቀረጥ መልክ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የግብር አሰባሰብ ስርዓት እንደ ዘመናዊው የግብር አሰባባሰብ የተቀናጀ አልነበረም፡፡ ስለዚህም መንግስታት የሚፈለገውን የግብር መጠን መሰብሰብ አልቻሉም ነበር፡፡

**መልመጃ 6፡4**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. የንግድ ስራ ለሀገር ምጣኔ ሀብት ዕድገት የሚያስገኘውን ጥቅም አብራራ/ሪ
2. ግብር "ሰጥቶ መቀበል ነው" የሚባለው ለምንድነው?
3. ከንግድ ስራ የሚገኙ ውጤቶች ምንድናቸው?

# ማጠቃለያ

በሰሜን ኢትዮጵያ ከተመሠረቱ የጥንት ስልጣኔዎች ውስጥ አክሱምና ዛጉዌ ተዋቂዎቹ ናቸው፡፡ የአክሱም መንግሥት ስልጣኔ ከ100 ዓ.ዓ እስከ 1150 ዓ.ም ቆይቷል፡፡ ነገር ግን የአክሱም የመጨረሻ ንጉስ የነበረው ድልናዖድ በዛጉዌ በመሸነፍ የዛጉዌ ሥረወ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡ ይሁን እንጂ በ1270 በተመሳሳይ ሁኔታ የኩኖአምላክን የመጨረሻውን የዛግዌ ንጉስ ይትባረክን ድል አድርጎ የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥትን መልሶ አቋቁሟል፡፡

ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የሙስሊም ሱልጣኔቶች በምስራቅና ደቡብ ምሰራቅ ኢትዮጵያ ተመስርተዋል፡፡ እነሱም ሸዋ፤ ኢፋት፤ ፈጣጋር፤ ዳዋሮ፤ ባሊ፣ አዳል እና ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡ ከ13ኛ እሰከ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ግዛትን ለማስፋፋ እና የንግድ መሥመሮችን ለመቆጣጠር ካላቸው ፍላጎት የተነሳ የሙስሊም ሱልጣኖች እና የክርስትያን ነገሥታት የተለያዩ ጦርነቶችን አካሂደዋል፡፡

ለረጅም ዘመናት የተደረገው የህዝቦች እንቅስቃሴና መሰፋፋት በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ለጎነደርና የተለያዩ ከተሞች መመስረት ምክንያት ሆኗል፡፡ ህዝቦች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ያደረጉት እንቅስቃሴ የባህል፣ የሀይማኖት፣ የማህበራዊ ህይወት እና የተለያዩ እሴቶች ትስስር እንዲኖር አድርጓል፡፡የኦሮሞ ገዳ ስርዓት ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓት ፣ የተለያዩ አደራጃጅትና አወቃቀር አለው፡፡ በዚህ መሰረት የገዳ ስርዓት ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ወታደራዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ማህበራዊ አደረጃጀቶችን የካትታል፡፡

## የምዕራፍ 6 ማጠቃለያ ጥያቄዎች፡

### ክፍል I፡የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች "እውነት"ወይም "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ

1. የአክሱም ጥንታዊ ስልጣኔ በሰሜናዊ ኢትዮጵያ የተመሰረተ ነው፡፡
2. የአክሱም ጥንታዊ ምጣኔ ሀብት የተመሰረተው በግብርናና በንግድ ስራ ላይ ነው፡፡
3. የገዳ ስርዓት በ2016 ዓ.ም በአለም የቅርስ መዝገብ (UNESCO)ላይ ተመዝግቧል፡፡
4. የዛጉዌ ሥረወ መንግሥትን ያቋቋመው ድልናእድ ይባላል፡፡
5. ለዛጉዌ ሥረወ መንግሥት መውደቅ ምክንያት ስልጣን ለመያዝ የተደረገው የእርሰር በእርስ ሽኩቻ ነው፡፡
6. የህዝቦች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም የለውም፡፡

### ክፍልII.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን በመምረጥ መልስ/ሽ

1. የጥንታዊ አክሱም ስልጣኔ የሚገልጽ የቱ ነው?

   ሀ. የስነ- ፅሑፍ ስርአት　　ሐ. የስነ- ህንፃ ግንባታ

   ለ. የተለያዩ ሳንቲሞች　　መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የጥንታዊ አክሱም መንግስት የንግድ ወደብ ነው፡፡

   ሀ. ዘይላ　ለ. አዱሊሰ　ሐ. አሰብ　መ. ምጽዋ

3. ከአክሱም ነገስታት ውስጥ ሜሮኤን የተቆጣጠረው የቱ ነው?

   ሀ. ካሌብ　ለ. ኢዛና　ሐ. ድልናእድ　መ. ተክለአብ

4. ጥንታዊ የአክሱም ሳንቲሞች ከምን ከምን የተሰሩ ናቸው?

ሀ. ብር ለ.ነሃስ ሐ. ወርቅ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. የሲንቄ ስርዓት ጥቅምን የሚገልጽ የቱነው?

ሀ. ንግድ ሐ. የሴቶችን መብት ማሰከበር

ለ. ሰላምን ማውረድ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው

6. በምስራቅ አፍሪካ በተካሄዱት የህዝብ እንቅስቃሴዎች ዉስጥ ታዋቂ የሆነው የቱ ነው፡፡

ሀ. የአፋር ለ. የኦሮሞ ሐ. የሶማሌ መ. የአርጎባ

**ክፍልIII.ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ**

1. በገዳ ስርዓት ውስጥ በየስምንት ስምንት አመት በዴሞክራሲያዊና በሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚካሄዱትን የገዳ ክፍሎች ስም ዘርዝር/ሪ
2. የአክሱምና የዛግዌ ስልጣኔን በማነፃፀር ጻፍ/ፊ?
3. የገዳ ስርዓት ምንነት ቤተሰቦቻችሁን፣ አባገዳዎችን እና ሽማግሌዎችን በመጠየቅ ለክፍላችሁ ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

# ምዕራፍ 7

## ትኩረት የሚሹ ወቅታዊ የዓለም ጉዳዮች

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች**

- የአከባቢ ፅንሰ ሀሳብ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የሰዉ ልጅ በአከባቢ ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- በሀገርና በዓለም ደረጃ በተፈጥሮአዊ አከባቢ ላይ የሚደርሱ ትላልቅ ችግሮችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- በአከባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ላይ ከማህበረሰቡ ጋር ትሳተፋለህ/ሽ፡፡
- የህዝብ ቁጥር መጨመር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የሽብርተኝነት ምንነት፣ በሰዉ ህይወት፣ በማህበራዊና እኮኖሚ ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትናገራለህ/ሽ፡፡
- በህገ ወጥ ስደት ምክንያት፤ በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለትካ ላይ የሚደርሰዉ ተፅዕኖ ምን እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፡፡

## መግቢያ

ትኩረት የምሹ ወቅታዊ የዓለም ጉዳዮች ጋር ተያይዘዉ ከሚነሱ ነገሮች ዉስጥ በምንኖርበት አከባቢ የሚገኙ እንደ ስነ-ምህዳርና የተፈጥሮ ሀብቶች ይገኛሉ፡፡ የተፈጥሮአዊ አከባቢ ዋና ዋና ችግሮች እንደ የአከባቢ ብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመር፣ የኦዞን መሳሳት፣ የተለያዩ ቆሻሻዎች፣ ሥነ-ህይወት ቁጥር ማነስና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡ እነዝህን ችግሮች ለመፍታት ልናተኩርባቸዉ የሚገቡ ጉዳዮች አከባቢን ማልማት፣ በባዶ መሬት ላይ ዕፅዋት መትከል፣ ደን የጠፋባቸዉን ቦታዎች መልሶ ማልማት፣ ስለተፈጥሮ ሀብት ማህበረሰብን ማስተማርና የተፈጥሮ ሀብትን በቁጠባ መጠቀም የሚሉት ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ስለህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ህገ ወጥ ስደትና የአሸባርነት ምንነት የሚሉት ይገኛሉ፡፡

## 7.1. የምንኖርበት አከባቢ

ተማርዎች ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባቸዉ የመማር ብቃት

- በአከባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤
- በአከባቢያችሁ የሚገኙ ዋና ዋና ችግሮችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤
- የሰዉ ልጅ በአከባቢ ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትገልፃለህ/ሽ፤
- የአከባቢ ችግሮች የሚፈቱባቸዉ መንገዶችን ትዘረዝራለህ/ሽ፤
- የአከባቢ ችግሮችን ለመፍታት የህብረተሰብ ተሳትፎ ያለዉ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፤
- በምትኖርበት አከባቢ፤ በአከባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ላይ ተሳትፎ ታደርጋለህ/ሽ፤
- የህዝብ ቁጥር መጨመር በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ምን እንደሆነ ትለያለህ/ሽ፤
- የሽብርተኝነት ምንነትና በሰዉ ህይወት፣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትገመግማለህ/ሽ፤

- ህገ ወጥ ስደት በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለትካዊ ላይ የሚያደርሰዉን ተፅዕኖ ትገልፃለህ/ሽ

### 7.1.1. የምንኖርበት አከባቢን ማወቅ

**የግምገማ ጥያቄ**

1. የምትኖርበት አከባቢ ዉስጥ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?
2. በምትኖርበት አከባቢ ያሉ ትላልቅ ችግሮች ምን ምን ናቸዉ?

የምንኖርበት አከባቢ ማለት ተፈጥሮአዊ አከባቢ ሆኖ ህይወት ያላቸዉና የሌላቸዉ ነገሮች የሚኖሩበት ቦታ ማለት ነዉ፡፡ ህይወት ያላቸዉና የሌላቸዉ ነገሮች ከተፈጥሮ አከባቢ ጋር ጠንካራና ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አላቸዉ፡፡ በተፈጥሮ አከባቢ ዉስጥ የሰዉ ልጆች ኑሮአቸዉን ለማሻሻል ህይወት ባላቸዉና በሌላቸዉ ነገሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያደርሳሉ፡፡ አከባቢ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም ተፈጥሮአዊና ሰዉ ሰራሽ አከባቢዎች ናቸዉ፡፡

**ተፈጥሮአዊ አከባቢ** ማለት ህይወት ያላቸዉና የሌላቸዉ ነገሮች በዉስጡ የያዘ ሆኖ እነዝህም እንደ ዉሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ማዕድናት፣ እንስሳት እና ዕፅዋትን ያጠቃልላል፡፡

**ሰዉ ሰራሽ አከባቢ** ማለት ደግሞ በሰዉ ልጆች ተሻሽለዉና ተቀይረዉ የሚገኙ ናቸዉ፡፡ እነርሱም እንደ ቤት፣ መንገድ፣ ከተሞች፣ እርሻ ቦታዎች፣ እንዱስትርዎችና የመሳሰሉተን በዉስጡ ይይዛል፡፡ በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች ጠንካራ የሆነ ግንኙነት አላቸዉ፡፡ ይህም ማለት በአከባቢ የሚገኙ ነገሮች ሁሉ እርስ በርሳቸዉ ተደጋግፈዉ የሚገኙ ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ፡- በዕፅዋትና በአፈር መካካል ያለዉ ግንኙነት በሰዉ ልጅና በተፈጥሮ ሀብት መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለዝህ የምንኖርበት አከባቢ በጣም ሰፊና ዉስብስብ ነዉ፡፡ የምንኖርበት አከባቢ በደንብ ማወቅ ይጠበቅብናል፡፡ የሰዉ ልጅ ስለሚኖርበት አከባቢ በቂ እዉቀት

ካለዉ በውስጥ የሚገኙ ነገሮችን ማወቅ ከቻለ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀምና ማንከባከብ ይችላል፡፡

### 7.1.2. የተፈጥሮ አከባቢ ትላልቅ ችግሮች

ዓለም በሰዉ ቁጥር መብዛት፣ ከፋብሪካዎች ከሚወጡ ጭስና በደን መጨፍጨፍ ምክንያት ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ ይገኛል፡፡ እነዝህ ችግሮች የአየር ብክለት፣ የዓለም ሙቀት መጨመር፣ የበረሃማነት መስፋፋት፣ ድርቅ፣ የንፁ ዉሃ እጦት፣ የሥነ-ህይወት ቁጥር ማነስ፣ የኦዞን መሳሳትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

#### ብክለት

**ብክለት** ማለት የአከባቢ መበከል፣ ጥሩ ያልሆነ ሽታ መኖር የሚታወቁ የአየር ሁኔታ ስቀየር ነዉ፡፡ በተፈጥሮ አከባቢ ዉስጥ ልበከሉ የሚችሉ ነገሮች እንደ አየር፣ ወሃ፣ አፈርና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

#### የአየር ብክለት

**የአየር ብክለት** ማለት የአከባቢ አየር መቆሸሽ ማለት ነዉ፡፡ አየር በተፈጥሮ በውስጡ የነበራቸው ምንዝሮች ላይ የተለያዩ አዳድስ ነገሮች ስጨመሩበት ይበከላል፡፡ አየር በሁለት መንገድ ልበከል ይችላል፡፡ እነሱም በተፈጥሮና በሰዉ ተግባር ናቸዉ፡፡

#### 1. በተፈጥሮ አየርን የሚበክሉ ነገሮች

ሀ. የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፡- እሳተ ጎሞራ በሚፈነዳበት ወቅት እንደ ጭስ፣ አመድና አቧራ በብዛት ወደ አከባቢ አየር ስለሚቀላቀሉ የአከባቢ አየር ይበከላል፡፡

ለ. ሰደድ እሳት፡- ዕፅዋት በተፈጥሮ እርስ በራሳቸዉ በሚፋተጉበት ጊዜ አልፎ አልፎ እሳት ልፈጠር ይችላል፡፡ በዝህ ሁኔታ የተፈጠረዉ እሳት

**በሰፊ መሬት ላይ ያለዉን ደን ሊያጠፋ ይችላል፡፡ ከተቃጠለዉ ደን የሚወጣዉ ጭስ ወደ ከባቢ አየር በመቀላቀል አየርን ይበክላል፡፡**

### 2. የሰዉ ተግባር

**ሰዎች የዕለት ኑሮአቸዉን ለማከናወን የተለያዩ ተግባራትን ይፈፅማሉ፡፡ በተግባራቸዉ ውስጥ አየርን ልበክሉ የሚችሉ ነገሮችን ወደ አየር ይለቃሉ፡፡ ከእነዝህም ውስጥ ጥቅቶቹ ከፋብሪካና ተሽከርካርዎች የሚወጣ ጭስ፣ የአረምና የፀረ-ተባይ መድሀንቶች መጠቀም፣ ደኖችን ማቃጠል፣ ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ጭስና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡**



ሥዕል 7.1 የአየር ብክለት

በአካባቢያችን የሚገኝ ውሃ በተለያዩ የሰዉ ልጅ ተግባር ምክንያት ይበከላል፡፡ ከነዝህም ውስጥ ጥቅቶቹ፡-

- ከፋብሪካና ከመኖሪያ ቤት የሚወጣ ፈሳሽ፤
- በእርሻ መሬት ላይ ማዳበሪያን፣ ፀረ አረምና ፀረ ተባይን መጠቀም፤
- በዉሃ ዉስጥ የሚጣሉ የተለያዩ ቆሻሻዎችና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡


### የአለም ሙቀት መጨመር

የአለም ሙቀት መጨመር የሚከሰተዉ ካርቦንዳይኦክሳይድ($CO_2$) በተፈጥሮ ከነበረበት በላይ በአከባቢ አየር ዉስጥ ስከማች ነዉ፡፡ በተፈጥሮ የሚገኘዉ ካርቦንዳይኦክሳይድ በመሬት ላይ ያለዉን ሙቀት ያስተካክላል ወይም መሬት በጣም እንዳትቀዘቅዝ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን በተለየዩ ምክንያቶች የካርቦንዳይኦክሳይድ መጠን በተፈጥሮ ከሚገኘዉ በላይ ሆኖ አየር ዉስጥ ስከማች የአለም ሙቀት እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ይህ ሀደት የአለም ሙቀት

መጨመር (Green house effect) ይባላል፡፡ ለምሳሌ $co_2$ በእጥፍ ቢጨምር የአለም ሙቀት ከ$1^0c$-$3^0c$ ልጨምር ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በአለም ላይ ትልቅ ችግር ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ፡- በአየር መዛባት ምክንያት በዋልታዎች አከባብ የሚገኙ በረዶዎች መቅለጥ፣ የዉቅያኖስና የባህር ውሃ መጠን እንድጨምር ያደርጋል፡፡ ከከባቢ አየር ጋር በመቀላቀል የአለም ሙቀት እንድጨምር የሚያደርጉ ነገሮች ከመኖርያ ቤትና ከፋብርካዎች የሚወጣ ጭስና ፈሳሽ ነገሮች፣ ከተቃጠሉ ደን የሚወጣ ጭስ ናቸዉ፡፡ የአለም ሙቀት እንድጨምር የሚያደርጉ ጋሶች መጠናቸዉ እንደምከተለዉ በሰንጠረዠ ቀረበዋል፡፡

| ስም | ወካይ | በከባቢ አየር ውስጥ ያላቸዉ ፐርሰንት |
|---|---|---|
| ካርቦንዳይኦክሳይድ | $CO_2$ | 55 % |
| ሚቴን | $CH_4$ | 15% |
| ናይትሬስኦክሳይድ | $N_2O$ CLFC | 5% |
| ክሎሮ-ፍሎሮ-ካርቦን | CFC | 25% |

ሠንጠረዥ 7.1. የዓለም ሙቀት መጨመር ምክንያት የሆኑ ገሶች






ሥዕል 7.2 የዓለም ሙቀት መጨመር

### የኦዞን መሳሳት

ኦዞን ($O_3$) በከባቢ አየር ውስጥ ከሚገኙ ይዘቶች አንዱ ነዉ፡፡ የሚንኖርበት መሬት የከባቢ አየር ንብርብር ትሮፖስፌር ይባላል፡፡ የኦዞን ጋስ የሚገኘዉ በእስትራቶስፌር ንብርብር ውስጥ ነዉ፡፡ በአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት የሚሆነዉ የኦዞን መሳሳት ነዉ፡፡ የኦዞን መሳሳት ደግሞ መርዛማ የሆነዉ አልትራቫዮሌት ጨረር እየሾለከ ወደ ምድር እንድመጣ ያደርጋል፡፡ የአልትራቫዮሌት ጨረር ወደ መሬት መድረስ ደግሞ ህይወት ባላቸዉ ነገሮች ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ያደርሳል፡፡

### የተለያዩ ቆሻሻዎች

ቆሻሻ ማለት የተለያዩ የማያስፈልጉ ነገሮች እንደ የቤት ጥራጊዎች፣ የምግብ፣ ወረቀቶች፣ ጨርቆች፣ የዱረ እንስሳት አጥንቶች፣ የተለያዩ የግንባታ መሳርያዎች፣ የተለያዩ የብረት ስብርባሪዎችና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

**ብዘ-ህይወት ማነስ** ማለት በዓለም ወይም በመሬት ላይ ህይወት ያላቸዉ ዝሪያዎች ቁጥር እያነሰ መሄድ ማለት ነዉ፡፡ ይህም የሆነዉ የዕፅዋትና የእንስሳት ዝሪያዎች መጥፋት ነዉ፡፡ ህይወት ያላቸዉ ነገሮች መጥፋት ምክንያት የሆነዉ አንደንድ ዝሪያዎች ሌሎች ዝሪያዎችን በመውረር፣ ሰዎች ከመጠን በላይ በተፈጥሮ ሀብት መጠቀም፣ የአየር መቀያየርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 7.1.3. አከባቢን መንከባከብ

የግምገማ ጥያቀዎች

1. የአከባቢ እንክብካቤ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. አንተ/እንች የሚትኖርበት /ሪበት ማህበረሰብ አከባቢያቸዉን እንዴት ይንከባከባሉ?

እንክብካቤ ማለት በተፈጥሮ አከባቢ ውስጥ ለሚገኙ ነገሮች አስፈላጊ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ ዋና ዓላማዉም በተፈጥሮ የሚገኙ

የተፈጥሮ ሀብቶችን በቁጠባና በአግባብ መጠቀምና ለረጅም ግዜ በማቆየት ለብዙ ሰዎች አግልግሎት እንድሰጡና ለቀጣይ ትውልድ እንድተላለፍ ማድረግ ነዉ፡፡ የአከባቢ ማህበረሰብ በሚከተሉት ዘዴዎች የተፈጥሮ አከባቢን መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡

**ባዶ በታዎችን በደን መሸፈን፤** በደን መሸፈን ማለት ለእረሻ ሥራና ለሌሎች አገልግሎቶች የማይዉሉ ቦታዎችን እንደ ተራራዎች፣ ገደላማ ቦታዎች፣ ዕፅዋት የሌለባቸዉ በዶ ቦታዎች ላይ ዕፅዋቶችን በመትከል ወደ ደን መቀየር ማለት ነዉ፡፡

**መልሰዉ መትከል፡-** ደኖች ተጨፍጭፈዉ የጠፋባቸዉን ቦታዎች ዕፅዋትን መልሰዉ በመትከልና በመንከባከብ ተመልሰዉ ደን እንድሆን ማድረግ ማለት ነዉ፡፡ ይህም አፈር በቀላሉ በዉሃ እንዳይሸረሸር ለዱር እንስሳት መኖሪያነትና የአየር ንብረት ሚዛን ለመጠበቅ ያገለግላል፡፡

**ማህበረሰብን ማስተማር፤** መንግስታዊና መንግስተዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ ዕቅዶችን በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ መስጠት አለባቸዉ፡፡ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት የተለያዩ ስልጠናዎችን በመፍጠር፣ በትምህርት ቤቶች በኩልና በተለያዩ መንገዶች በማስተማር የማህበረሰብን ግንዛቤ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

### በተፈጥሮ ሀብት የአጠቃቀም ዘዴ

የተፈጥሮ ሀብት እንዳይባክን በሶስት የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንችላለን፡፡

1. **በቁጠባ መጠቀም** ፡-የተፈጥሮ ሀብትን የሚያስፈልጉትን ብቻ ሳናባክን በቁጠባ መጠቀምና ለቀጣይ ትውልድ እንድተላለፍ መድረግ፡፡ ለምሳሌ፡-የማይታደሱ የተፈጥሮ ሀብቶች እንደ ማዕድናት፣ የተፈጥሮ ጋስና የመሳሰሉትን በቁጠባ መጠቀም ነዉ፡፡
2. **እንደገና መጠቀም**፡- አንድ ግዜ የተጠቀምንባቸውን ሀብቶችን እንዳይበላሹ በመጠገን እንደገና አግልግሎት እንድሰጡ ማድረግ ነዉ፡፡ ለምሳሌ

የደኖችን ብክነት ለመቀነስ ለቤትና ለቢሮ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን መልሰን በመጠገንና በማደስ አገልግሎት እንድሰጡ ማድረግ ነዉ፡፡

3. **መልሰዉ መጠቀም**፡- የተጣሉ ዕቃዎችን በአድስ መልክ አሻሽሎ በመስራት አገልግሎት እንድሰጡ ማድረግ ነዉ፡፡ ዋና አላማዉ የተጣሉ ዕቃዎችን መልሰን በማደስ አገልግሎት እንድሰጡ በማድረግ ጥሬ ዕቃዎች እንዳይባክኑ ማድረግ ነዉ፡፡

**መልመጃ** 7.1

**ለሚከተሉት ጥያቀዎች አጭር መልስ ሰጥ/ጪ**

1. የሰዉ ልጅ በአከባቢዉ ላይ ምን ዓይነት ጉዳት ልያደርስ ይችላል?
2. በአከባቢያችሁ የተፈጥሮ ሀብትን የሚበክሉ ነገሮች ምን ምን ናቸዉ?
3. የምትኖርነት አከባቢ እንዳይበክል የሚጠበቅብህ/ሽ ድርሻ ምንድነው?
4. የአለም ሙቀት መጨመር እንዴት ይከሰታል?
5. የተፈጥሮ ሀብትን በቁጠባ በመጠቀም ለቀጣይ ትዉልድ እንድተላለፍ ምን ማደረግ አለበት?

## 7.2. የህዝብ ቁጥር መጨመር

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የህዝብ ቁጥር መጨመር ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት የሚመጡ ችግሮች ምን ምን ናቸዉ?

የህዝብ ቁጥር መጨመር ማለት በአንድ በተወሰነ አከባቢ የሚኖሩ የሰዎች ቁጥር ከሚፈለገዉ በላይ መጨመር ማለት ነዉ፡፡ ይህ ችግር ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ያደርሳል፡፡ የህዝብ ቁጥርና የተፈጥሮ ሀብት አለመመጣጠን የተፈጥሮ ሀብት ብክለት ያስከትላል፡፡ ለምሳሌ የደን መጨፍጨፍ፣ የአፈር መሸርሸር፣ ማዕድናትን ከመጠን በላይ መጠቀምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 7.3. ሽብርተኝነት

*የግምገማ ጥያቄዎች*

1. ሽብርተኝነት ማለት ምን ማለት ነዉ?

ሀ/ ሽብርተኝነት የሚያመጣዉ ጉዳት ምንድ ነዉ?

ለ/ ሽብርተኝነትን ለመከላከል የማህበረሰቡ ድርሻ ምን ልሆን ይችላል?

**ሽብርተኝነት** ማለት በማህበረሰቡ ላይ የሚፈፀም አስጠያፊ ተግባር ሆኖ በአሁኑ ሰዓት የአለም ህዝብ እያስጨነቀ ያለ ጉዳይ ነዉ፡፡ ሽብርተኝነት የማህበረሰቡ እሴትና የህግ ተቃራን ሆኖ ህዝብን የሚጎዳ ነዉ፡፡ በአሁኑ ሰዓት በአለም ላይ ሽብርተኝነትን ፖለትካዊ ስልጣንን ለማግኘት ይጠቀሙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ዋና ዓላማቸዉ ብዙ ሀብትን በማከማቸት በአጭር ግዜ ውስጥ መበልፀግ ነዉ፡፡

የቅርብ ግዜ ትውስታ የሆነዉ ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ ሽብርተኝነት በግለሰቦችና ማህበራዊ ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ ብዙ ጥፋቶችን ስፈፅም ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ እንደ አዉሮፓ አቆጣጠር መስከረም 19/2001 ዓ.ም በሰሜን አሜርካ የሚገኘዉ የአለም የንግድ ማዕከል የተደረመሰዉ በሽብርተኞች ድርግት ነዉ፡፡



ሥዕል 7.3 በሽብርተኞች የአለም ንግድ ማዕከል ላይ የደረሰው ጉዳት

በዓለም የንግድ ማዕከል ላይ ጥፋት ከደረሰ በኃላ በተለያዩ ሀገሮች ላይ የሽብርተኝነት ተግባር እየተፈፀመ ይገኛል፡፡ ሽብርተኞች ብዙዉን ጊዜ

ለማጥፋት ትኩረት የሚያደርጉት በማህበራዊ ተቋማት እንደ ትምህርት ቤት፣ የገበያ ማዕከል፣ መዝናኛ ቦታዎችና የመሳሰሉት ላይ ነዉ፡፡ በጎረቤት ሀገር በኬንያና በሶማልያ የሽብር ተግባራት በተደጋጋሚ ሲፈፀሙ ይታያል፡፡ ስለዝህ ሽብርተኝነትን መዋጋት የሁሉም ዜጎች ግዴታ ነዉ፡፡ ምሳሌ በትምህርት ቤት አከባቢ ዜጎች ችሎታን፣ አመለካከትን፣ ብቃትና ሙያን ለመማር መሆን አለበት፡፡ ዜጎች ሙያዊና አስተዳደራዊ ብቃትን የሚያጎለብቱበት ቦታ መሆን አለበት፡፡ በተጨማርም የሃይማኖት ተቋማትና የማህበረሰብ እሴቶች ዜጎችን አብሮ የመኖር፣ የጋራ ሰላም፣ የሰዉ ልጅ እኩልነትና ግልፀኝነት ላይ በተከታታይ ማስተማርና ማስገንዘብ አለበት፡፡ ዜጎች የባህል፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የአመለካከትና የመሳሰሉት ልዩነት እንዳላቸዉ እርስ በራሳቸዉ አዉቀዉ በመረዳዳትና በመቻቻል አብሮ መኖር አለባቸዉ፡፡ በአጠቃላይ የአለም ህዝብ በተላየዩ ማህበራዊ ጉዳዮች የተሳሰሩ መሆናቸውንና ልዩነቶች መኖራቸውን በመረዳት ለጋራ ሰላም የመቆም ግዴታ አለባቸው፡፡

**መልመጃ 2.7**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ሰጥ/ጪ**

1. ሽብርተኝነትን ለመከላከል ዜጎች ልወጡ ከሚገቡ ተግባራት ውስጥ ሦስቱን ፃፍ/ፊ?
2. ሀገሮች ሽብርተኝነትን ለመከላከል ምን ማድረግ አለባቸዉ?

## 7.4. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

የግምገማ ጥያቄዎች

1. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የሚያስከትለዉ ጉዳት ዘርዝር/ሪ?
2. በህገ-ወጥ ደላሎች ከሀገር መዉጣት የሚያስከትለዉ ጉዳት ላይ ተወያዩ?

ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ማለት ሰዎችን በማታለል፣ በመዋሸት በማፈንና በተለያዩ መንገዶች የተለያዩ ሰዎችን በመሰብሰብ የግል ጥቅም ለማግኘት በህገ-ወጥ መንገድ ከቦታ ቦታ፤ ከሀገር ሀገር በመዘዋወር ዘመናዊ የባሪያ

ንግድ ማካሄድ ነዉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሰዎችን ከቦታ ቦታ በህገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር ትኩረት ከሚሹ ከዓለም ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛዉ ችግር ሆኑዋል፡፡ በብዙ ሀገሮች ውስጥ ይህ ተግባር በተለያየ መንገዶች ከፍተኛ ችግር አድርሷል፡፡ በተለይ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰብ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ለህገ- ወጥ የሰዎች ዝውውር እየተጋለጡ ያሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ወጣቶችና ህፃናት ናቸዉ፡፡ በተለይ በሴቶችና በህፃናት ላይ በጣም የከፋ ነዉ፡፡ በህገ-ወጥ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ ደላሎች በቂ ግንዛቤ የሌላቸዉ የገጠሩን ማህበረሰብ በማታለል ለዝህ ችግር እንድጋለጡ ያደርጋሉ፡፡ እነዝህ ደላሎች የሚጠቀሙበት ዘዴዎች ሠራተኛና አሰሪ አገናኝ በማለት ሰዎችን ለተሻለ የሥራ ዕድልና ክፍያ እንደሚያገናኙ በማስመሰል ከገጠሩ ማህበረሰብ በመሰብሰብ ለሌሎች አካላት አሳልፎ ይሰጣሉ፡፡ እንደዝሁም ከሀገር በማዉጣት ለሌሎች ሀገሮች አሳልፈዉ ይሰጣሉ፡፡ በዝህ ሁኔታ ከሀገራቸዉ የወጡ ሰዎች ብዙ ችግር ይደርስባቸዋል፡፡ እነዝህም ችግሮች ከአካል ጉዳት እስከ ህይወት ማጣት ናቸዉ፡፡ በህገ-ወጥ መንገድ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ሰዎች ከሚደርስባቸዉ ጉዳቶች ዉስጥ ጥቅቶቹ፡-

- ሥራን በግዳጅ ማሰራት
- ከአቅም በላይ የሆነ ሥራን ማሰራት
- ጉዳት ልያደርሱ የሚችሉ ሥራዎችን ማሰራት
- በተለያዩ ወንጀሎች ላይ በግድ እንድሳተፉ ማድረግ
- በህፃናት ላይ ጉዳት በማድረስና እንድለምኑ ማድረግ
- በማስገደድ በወስባዊ ሥራ ላይ እንድሰማሩ ማድረግ
- የጉልበት ብዝበዛና ዝቅተኛ ክፍያ እንድያገኙ ማድረግ
- ህፃናት የመማርና የወደ ፍት ዕጣ ፋንታቸዉን ለመወሰን ዕድል ማጣትና የመሳሰሉት ናቸዉ፡፡

ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በአለም ደረጃ እንድቆም በወጣዉ ህግ መሠረት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፑብሊክ (ኢፌድሪ) ህገ መንግስት

አንቀፅ 18/2 ላይ ወቷዋል፡፡ ስለዝህ ዜጎችን ከእንደዝህ ዓይነት ህገ-ወጥ ተግባር ለመጠበቅ ለህብረተሰቡ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል ፡፡

**መልመጃ 7.3**

ለሚከተሉት ጥያቀዎች አጭር መልስ ሰጥ/ጪ

1. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ምን ጉዳቶችን ያደርሳል?
2. ለህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የተጋለጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን ዘረዝር /ሪ?
3. በህገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ ደላላዎች ማለት ምን ማለት ነዉ?
4. በህገ-ወጥ መንገድ ሰዎችን የሚያዘዋውሩ ደላሎች የሚጠቀሙት ዘዴዎች ምን ምን ናቸዉ?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- የምንኖርበት አከባቢ ማለት የሰዉ ልጅ፣ እንስሳትና ዕፅዋት የሚኖሩበት ቦታ ሆኖ ለሁለት ይካፈላል፡፡ እነሱም፡- ተፈጥሮአዊና ሰዉ ሰራሽ አከባቢዎች ናቸዉ፡፡
- የተፈጥሮ አከባቢ የሚያጠቃልለዉ ዉሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ማዕድናት፣ እፅዋትና እንስሳትን ናቸዉ፡፡
- ሰዉ ሰራሽ አከባቢዎች የሚንላቸዉ ደግሞ ትምህርት ቤት፣ መንገድ፣ ከተማ፣ የእርሻ መሬት፣ እንዱስትሪና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡
- የሚንኖርበት አከባቢ ህይወት ላላቸዉ ነገሮች ለመኖሪያነትና ለምግብነት ከፍተኛ ድርሻ አለዉ፡፡ ስለዝህ ሁሉም ሰዎች አከባቢን መጠበቅና ማንከባከብ ያስፈልጋል፡፡
- በአሁኑ ጊዜ የተፈጥሮ አከባቢ ለአየር ብክለት፣ ለአለም ሙቀት መጨመር፣ ለኦዞን መሳሳት፣ የተለያዩ ቆሻሻዎች፣ ብዘ-ህይወት ማነስና ለመሳሰሉት ችግሮች የተጋለጡ ናቸዉ፡፡ ለእነዝህ ችግሮች ምክንያት የሆኑ ደግሞ የህዝብ ቁጥር መጨመር፣ ከፋብሪካዎችና ከሞተሮች የሚወጣዉ ጭስና የደን

**መጨፍጨፍ ዋና ዋናዎቹ ናቸዉ:: ከላይ የተጠቀሱ ችግሮችን ለመቀነስ ህብረተሰብን ማስተማርና እፅዋትን መልሶ በመትከል የተፈጥሮ ሀብቶችን በቁጠባና በጥንቃቄ መጠቀም ወሳኝ ተግባራት ናቸዉ::**

- **በአሁኑ ጊዜ የአለም ወሳኝ ወቅታዊ ችግሮች የሚባሉት ሽብርታኝነትና ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ናቸዉ::**
- **ሽብርተኝነት በህብረተሰቡ ዉስጥ ጭንቀትንና ፍራቻን በመፍጠር የማህበረሰቡ የአኗኗር ሁኔታን ሰላምና ፀጥታን እንድያጣ በማድረግ የህዝቦችን ኑሮ ማወክ ነዉ::**

## የምዕራፍ 7 መልመጃ

**ክፍል I. የሚከተሉትን ጥያቀዎች ትክክል የሆነዉን እዉነት ትክክል ያልሆነዉን ሐሰት በማለት መልስ/ሽ**

1. የምንኖርበት አከባቢ ህይወት ያላቸዉንና የሌላቸዉን በሙሉ የያዘ ነዉ::
2. ሰዎች በህገ-ወጥ መንገድ ከኢትዮጵያ የሚወጣበት ምክንያት ስለሚቸገሩ ብቻ ነዉ::
3. የሚንኖረበት አከባቢ በደንብ ማወቅ የሚያስፈልገን አከባብዎችን በአገባቡ እንድናከባክበዉ እንድረዳን ነዉ::
4. ሽብርተኝነት በአሁኑ ጊዜ በአለም ላይ ወቅታዊና አሳሳቢ ችግር አይደለም::

**ክፍል II. በ"ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምድ/ጂ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ከአቅም በላይ አሣን ማስገር | ሀ. ኦዞን |
| 2. የአልትራቫዮሌት ጨረርን ይከላከላል | ለ. ካርቦንዳይኦክሳይድ($CO_2$) |
| 3. ሙቀትን የሚጨምር ጋዝ | ሐ. ህይወት ያላቸዉ ቁጥር ማነስ |
| 4. በተፈጥሮ ከባቢ አየርን የምበክል | መ. እሳተ ጐሞራ |
| 5. በሰዉ ተግባር ከባቢ አየርን የምበክል | ሠ. ደን ማቃጠል |

**ክፍል III. ለሚከተሉት ጥያቀዎች ትክክለኛዉን መልስ በመምረጥ ፃፍ/ፊ**

1. በተፈትሮ አከባቢ አየርን የምበክለዉ የቱ ነዉ?

   ሀ. የቤት ዉስጥ እሳት ለ. የሰደድ እሳት

   ሐ. ከከተማ የሚወጣ ጭስ መ. ከፋብርካ የሚወጣ ጭስ

2. ከባቢ አየርን የምበክል ሰዉ ሰራሽ የሆነ የቱ ነዉ?

   ሀ. አበባ ለ. እሳተ ጐሞራ ሐ. ከከተማ የሚወጣ ጭስ መ. የሰደድ እሳት

3. ለአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት የሆነዉ ጋዝ የቱ ነዉ?

   ሀ. ካረቦንዳይኦከሳይድ ($CO_2$) ሐ. ኦዞን

   ለ. ኦክስጅን($O_2$) መ. ናይትሮጅን